# ለዳዕዋ አካሄድ የስምምነት ሰነድ

# ميثاق الشرف الدعوي

هشام الطالب

አዘጋጅ

ሂሻም አል-ጣሊብ

ተርጓሚ

ዳር -አልፊክር የትርጉምና የህትመት ስራ

አዲስአበባ ጠ ኢትዮጵያ 2016

دار الفكر للترجمة والنشر والبحث العلمي في إثيوبيا

Dar Al-fiker for Translation Publication
and Scientific Research - Ethiopia

Addis Ababa - Ethiopia

# ለዳዕዋ አካሄድ የክብር የስምምነት ሰነድ

ዶ/ር ሂሻም ጧሊብ

ተርጓሚ፡-ዳረል ፊከር

DF-E-TrBs-16/02

# <u>መግቢያ</u>

በኢስላም ሀገራት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የኢስላማዊ ህሊናዊ ንቃት ተስፋፍቱዋል፡፡ ይህ መልካም አውንታዊና የተባረከ ክስተት ነው፡፡ ሙስሊሙ ኡማ ከማንገላጀ ወደ ንቃት እራስን ወደ ማወቅ ሂደት በሀይማኖትም መተማመንና እራስን ቀና ማድረግ ጀምᎄዋል፡፡

ይህም በቀጣይ ከኋላቀርነት ለመውጣት የሚደረግ ጥረትን ይወልዳል፡፡ ከአስተሳሰብ ባርነትና ከ እለት እለት ህይወት ምርኮኝነት ነፃነት ማግኘትም ነው፡፡ ይህ ንቃትና ለውጥ በዘመናዊው አጠራር (ሰህዋ ኢስላማዊ አገራት) ይባላል፡፡

የአላህ(ሱ.ወ) ፍቃድ በመሆኑ ይህ ኢስላማዊ ሰህዋ የኢስላማዊ ወዳልሆኑ አገራትም መስፋፋት ችሏል፡፡ለስራና ለትምህርት ብለው ወደ ምእራብ ሀገራት የተጓዙ ሙስሊሞች አሉ፡፡ እነዚህ ዲያስፖራዎች ከቅርብ አመታት ወዲህ የሚያስመሰግናቸው ስራ እየሰሩ ነው፡፡ የተደራጀና ተቋማዊስራዎችን መስራት ጀምረዋል፡፡

ይህም ስብስቦች ለዲያስፖራ አካላት በምድራዊ ህይወት ጉዳይ እንዲሁ ሀይማኖታዊ ጉዳይ ኢስላማዊ አቅጣጫዎችን ይጠቁማቸዋል አስተዳደራዊ ችግሮችን የሚያስተካክሉበት ማእከል ነው ሆኖላቸዋል፡፡ይህ የወደፊቱን አቅጣጫ (የማነበብ)በ አፍሴላዊ ቦታዎች ላይ ተወካይ ይሆናቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ ውጤትነው፡፡ (የማይነበብ) የዲያስፖራ ስብስቦች ከተማሪ ህልሞች፣ ከአገር አገር እየተጓዙ (የማይነበብ) የህይወቱን እለታዊ ወጪ ለመሸፈን ከሚኖር ይህ የተሻለ ከፍ ያለ እርከን ላይ መድረስ ችለዋል፡፡ ከላይ ያነሳናቸው ሰዎች የትኛውንም ያህል ችሎታ ቢኖራቸው ምርጥ ቢሆኑ ልፋታቸው መልካም ቢሆንም ችሎታቸው ውስን ጊዜያዊ ሚና ነው ሊኖራቸው የሚችለው፡፡

## የኢስላማዊ ሰህዋ(መነቃቃት) መገለጫዎች

ይህ የተባረከ ኢስላማዊ ሰህዋ የተለያዩ ገፅታዎች አሉት፡፡ እንደየአካባቢያቸው ሁኔታ ይለያያሉ፡፡ይህየሙስሊም ዲስፖራዎች ማዕከል ምዕራብ ሀገር ላሉት ለከፊሎች ማዕከል፣አልያም መስጅድ ወይም የኢንቨስትመንት ማህበር አልያም የገንዘብ ተቋም ለሚስኪኖች ብድር የሚሳጥ ፕሮጀክት፣መጽሄት፣የድርሰት የፅሁፍአገልግሎት የትርጉም የህትመት ስራ መስራት ፣ከአንድ ቦታ የኢስላም ጥሪ ለማድረስ የተላከ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም በኢስላማዊ አገራት የሸሪአን ህግጋትና የኢስላምን አስተምህሮ በ ህይወት ውስጥ ለመተባበር የሚፈልግ ቡድን ይሆናል፡፡ አልያም የሙስሊም ሀገርን ነፃ ለማውጣት የሚንቀሳቀስ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ አስደሳች ነገሮች መሆናቸው ላይ ጥርጥር የለንም፡፡ ለነዚህ ጥረቶች ዱአ ማድረግና ማስተባበር ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩልም ግምገማ ማስተካከያ እና አቅጣጫ መጠቆም ግድ ይላል፡፡

## ለሳህዋ አል ኢስላም መፈጠር ምክንያት የሆኑ ነጥቦች

ይህ ኢስላማዊ እንቅስቃሴ የተለያዩ ነጥቦች ውጤት ነው፡፡የብዙ ጥረቶች ፍሬ ነው፡፡የቡድን የግለሰብ በተደራጀ አልያም በተበታተነ በኦፍሴሊያዊ አልያም በህዝባዊ ጥረቶች የተገኘ ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ልፋት ይህ ውጤት ሙስሊሙ ኡማ መሰረታዊ፣ተፈጥሮአዊ አጋጣሚ በሆነ መልኩ የተከሰተ የኖረ አላህ (ሱ.ወ) ዲኑን እንደሚጠብቅ ያሳየ እውነታ ነው፡፡

ይህንን ኢስላማዊ ንቃት እንቅስቃሴ ተመልክቶ በዚህ ጊዜ ነው የተጀመረው ብሎ በዚህ መገደብ ለሚፈልግ ሰው በጣም ይቸገራል፡፡ ይህም የሆነው ይህ የኢስላማዊ እንቅስቃሴ መገለጫስሩ የራቀ፣ ብቅ እልም

ሲል የቆየ በመሆኑ ጥረቱ ቀጣይ የሆነ በግልፅ ሲታይ ሲሸሽግ የከረመ በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የኢስላማዊ ጥሪ እድሳት ቆሞ አያውቅም ነበር ወደፊትም ይቀጥላል፡፡ሊቆረጥአይችልም፡፡ ምን አልባትምሲደክም፣ሊጠነክር፣ሊሳሳት፣ሊስተካከለል፣ ሊታመም፣ሊሽር ይችላል፡፡ ይሆናል፡፡ግና ዘውታሪነት ግን የዩኒቨርሱ የማያወላዳ ህግ ነው አላህ(ሱ.ወ) ያስቀመጣቸው ፅኑ እና ቋዋሚህጎች አይወገዱም አይቀየሩም፡፡

## የ1967 ሽንፈት

ለኢስላማዊ ንቃትና እንቅስቃሴ ወሳኝ የታሪክ መዘውር የሆነው 1967ነው፡፡ አረቦች በኢስራኤል የደረሰባቸው የሽንፈት ፅዋ፣ በዛን ወቅት ከባድ የፀና፣ የስነልቦና፣የአስተሳሰብ፣የፖለቲካ፣የማህበራዊ የወታደራዊ መናወጥ ያስከተለ ከባድ ክስተት ነበር፡፡ይህ ከባድ ማፅበል ካስከተላቸው ነገሮች ውስጥ ለሽንፈቱ ምክንያት የሆኑ መሪዎች ላይ የህዝብ ቁጣን መቀስቀሱ ነው፡፡ መንግስታቱ ሲያራምዷቸው የነበሩት አብዮታዊ፣ሶሻሊስታዊ፣ ሌብራላዊ፣ ሀገራዊ፣ አስተሳሰባቸውንም ጭምር ህዝቡ መጠየቅ ጀመረ፡፡ ጥላቻና ከባድ ወቀሳ ሰነዘረ፡፡እነዚህን አስተሳሰቦች የመቀየሪያ ሀሳብ ማፈላለግ ጀመሩ ከዚህ በኋላ ወደ ኢስላም ፊታቸውን አዞሩ፡፡ ይህ የሚደንቅ ነገር አይደለም፡፡ እነርሱ ሲጀመርም መጀመሪያቸውም መጨረሻቸውም ሙስሊሞች ናቸው፡፡ እንደዚሁም ግለሰብ ችግር መከራ የሚደርስበት ጊዜ ወደ አላህ እንደሚመለስ ሁሉ ማህበራትና ፓርቲዎች ወደ አላህ(ሱ.ወ) ይመለሳሉ፡፡

ከዚህ ተነስተን የ1967 ሽንፈት ኢስላማዊ እንቅስቃሴ ሀይልና አቅም ሰጥቶታል ማለት እንችላለን፡፡ስለዚህም ይህ የሽንፈት አመት የታሪኩ አንኳር መዘውር ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአላህ ጥበብ ይገርማል በመጥፎ

ክስተት ውስጥ መልካም እንዲታሰብ ያደርጋል፡፡ በመልካም ክስተት ውስጥም ጥሩ ያልሆነ ነገር እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) «ቃኑን አተዳፉዕን» ቋሚና ቀጣይ ጥበብ አድርጎታል፡፡ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ሀይል ቢወድም ቢጠላም ቋሚ በሆነ  እንቅስቃሴ ውስጥ መጓዝ ግድ ነው፡፡ አሸናፊም ተሸናፊም ነው፡፡በዚህ ቋሚና እንቅስቃሴ ውስጥ ለመልካሞቹም ለክፉዎቹም ለሙስሊሞቹም ሙስሊም ላልሆኑትም እድሉ ክፍት ነው፡፡ ከምድር ተፈጥሮአዊ ህግ  ጋር የሚያደርጉት የነቃና ተተጣጣመእንቅስቃሴ መልካም ሊሰሩ አልያም አብሮ ፈዝዘውና ተሳክረው መጓዝ ተስኗቸው ሊጠፉ ይችላሉ፡፡

## <u>ቃኑን አተዳፉዕ</u>

ከአላህ(ሱ.ወ) ድንቅና ውብ ርህራሄና ፍትህ ውስጥ ሁሉንም የምድርና የህይወት ህግጋት «ቃኑን አተዳፉዕ» ጨምሮ ህግጋቱን ፍትሀዊና ሁሉንም የሚያዳርስና በእኩልነት የሚያስተናግድ መሆኑ ነው፡፡ለማንም አያዳላም፣ ለማንም ጠላት አይደለም የተጣላትን ግለሰብ ወይም ቡድን አልያም ዲን አታባብልም፡፡ የምድር ህግጋት ፊት ሁሉም እኩል ነው፡፡ ከእርሱ ጋር ጥሩ አድርጎ የሚሰራ ቢሆን ስኬታማ ይሆናል፡፡ ከህይወት ህግጋት ውጪ የሆነ ሰው ማንም ቢሆን ያሸንፋል፡፡ ከ «ቃኑን አተዳፉዕ» ቱሩፋቶች ውስጥ ለኢስላም የለውጥ ታጋዮች እድልን ያመቻችላቸዋል ህይወት ከማርጀትና ባለበት ከመቆም እንዲሁ ከመድረቅ ይጠብቀዋል፡፡በተጨማሪም ሙስሊምንምን ጊዜም ለዚህ ፍጥረት አለም እውነተኛው መሪ አላህ (ሱ.ወ)መሆኑን ያስታውሰዋል፡፡ ይህ ጉዳይ ለሙስሊም እምነቱ እንዲሰርፅ ጥንካሬ እና ፅናት እንዲዋሀደው ያደርጉታል፡፡ በአላህ  መመካትና  ሁሌም ንቁና ተንቀሳቃሽ ሰው እንዲሆን ያግዙታል፡፡ ልቦናው ውስጥም  በአላህ ላይ ያለው  እምነት እንዲፀና ያደርጉታል፡፡አላህ(ሱ.ወ)እንዲህ ብሏል

ۗ وَلَوْلَا دَفْعُ ٱللَّهِ ٱلنَّاسَ بَعْضَهُم بِبَعْضٍ لَّفَسَدَتِ ٱلْأَرْضُ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ ذُو فَضْلٍ عَلَى ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٢٥١﴾ سورة البقرة :251

አላህ የከፊሎቹን ሰዎች (እኩይ አድራጎት) በከፊሎቹ (መልካም ትግል) ባያስወግድ ሮ ምድር በ እርግጥም ትበከል ነበር፡፡ ግና አላህ ለ አለማት ቸር ነው፡፡» አልበቀራ፤251

ከ1967 ሽንፈት በኋላ የተከሰተብን ነገር ለማስታወስ የሚሞክር ማንም ሰው ኢስላማዊ ህብረተሰብ ይህንን ሽንፈት ለማለፍ ጥረት ማድረጉን እንዲሁም በዚህ ሙከራ የተሻለ ውጤት ተመዝቧል፡፡ከነዚህም ዋናው ውጤት በ1973 ኢስራኤልን ማሸነፍ ነው፡፡ በ 1989 የሶቪየት ህብረትን ክፍል በ1989 ማሸነፍ ነው፡፡

## <u>የሶቪየት ህብረት መሸነፍ</u>

ኢስላማዊ የንቃት እንቅስቃሴ በሁሉም ሀገራት ተንሰራፍቶ ተቀጣጠለ ይህ እንቅስቃሴ ቀድሞውኑ ከመኖሩ ጋር ከዘመን ዘመን ከቦታ ቦታ የዳእዋ እንቅስቃሴ የተለያዩ ህዝቦች ነበሩበት፡፡ ሆኖም እነዚህ ህዝቦች የእንቅስቃሴውን መልካምነት በዜሮ አያባዛውም፡፡ቀጣይነቱና ግስጋሴውን አያቅበውም፡፡ወደ ፊት የሚያሻግረውን እንቅስቃሴ በፍጥነትና በስኬት የበለጠ እንዲጓዝ የሚያደርግ ክስተት ተከሰተ፡፡እርሱም በ1991 የሶቪየት ህብረት መውደቅና መበታተን ነው፡፡ይህ የተንሰራፉ ትልቅ አገር በልጆቹ እጅ ተንኮታኮተ፡፡ ታላቅና አንድ ሀገር የነበረው የተለያዩ አገራት ሆኑ፡፡ የእርሱ መፈረካከስ አብሮት የሶሻሊዝም መውደቅን አስከተለ፡፡ ሶሻሊዝም በቁሳዊነት ብቻ የሚያምን አስተሳሰብ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት

በአጠቃላይ ሀይማኖቶችን በተለይ እስልምናን ይዋጋ ነበር፡፡ በሶቪየት መፈራረስ እስልምና እና ሙስሊሞችን ለረጅም ዘመናት ሲዋጋና ሲታገል የነበረው ሀይል ከሰመ ኢስላማዊ ጥሪ ለማድረግ ጥሩ የስራ እድል ተከፈተ፡ ፡ በዚህ በፈረሰ ሀይል ስር ዳዕዋው መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ ይህ ስር ነቀል ንዝረት የ «ቃኑን ኢንቲፋዳ» ውጤት ነው፡፡ በፊትም በኋላም ፍቃዱና ድርጊቱ የአላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡

## ሁለቱ መንትያ የኒዮርክ ፎቆች 9/11

ከአስር አመታት በኋላ ሶስተኛ ስር ነቀል ለውጥ መጣ፡፡ እሱም በ 2001 ሁለቱ መንትያ የኒዮርክ የንግድ ማእከሎች መመታት ነው፡፡ይህ ከባድ አደጋ ተከሰተ፡፡የብዙ መላምቶችና ትርጓሜዎች ተሰጡት፡፡ምን አልባትም ከታሪክ እንቆቅልሾች ውስጥ ሆኖ ይቀር ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህንን ተከትሎ አሜሪካ አፍጋኒስታንና ኢራቅን መውረå ይህንኑ ተከትሎ የነበረው የመገናኛ ብዙሀን የፖለቲካ የኢኮኖሚ የወታደራዊ፣ የባህልና የትምህርት ፕሮፖጋንዳ በኢስላም አገራት ባጠቃላይ በተለይ በአሜሪካና በአውሮፓ በሁሉም አብይ ርዕሰ ጉዳይ ሆነ፡፡ የቅርቡም የሩቁም አጀንዳ ፡፡ ብዙ ተናጋሪዎች በክፋት መነፅር አልያም ባለማወቅ ያወራሉ፡፡ ጉዳዩን በትክክል የሚያሥቀምጡ ተናጋሪዎች ቁጥራቸው ትንሽ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አደጋ በጥሩም ይሁን በመጥፎ ኢስላም የብዙሀን አጀንዳ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህ መልካምና ምርጥ እድል በዳዕዋ ሜዳ ላይ ላሉ ሰዎች ጥሩ ኢስላምን በትክክል ለማቅረብ ያስችላቸዋል፡፡ ይህም እንዲሁ መልካም የ «ቃኑን አተዳፉዕ» በረከት ነው፡፡ መጀመሪያም በኋላም የአላህ ፍቃድ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ባለፈው እንዲሁም ወደፊት በሚያልፈውእርሱ ብቻ ለሚያቀው ጥበብ በሚከሰቱ ከባባድ ክስተቶች ምድር ሙሉ በሙሉ እንድትዳረስ የሻ ይመስላል፡፡ በዚህም ምድር ሁላ ለእርሱ ትክክለኛ ዲን

እንድትገዛ ያደርገዋል፡፡ የሰው ልጅ ከጥሜት ወደ ቅን መንገድ ከበሽታና ስቃይ ወደ ሰላም እንዲሸጋገር ያደርገዋል፡፡

## አስፈላጊና ወሳኝ ግንዛቤ

ምንም ይሁን ነገሩ ኡማው(ማህበረሰቡ) እነዚህን ነጥቦች በትክክል መገንዘብ አለባቸው፡፡

1) ይህ ኢስላምን የማስተዋወቅ ብቸኛና የማይደገም እድል ፣ ብቃት ያላቸው ለአላህ ብቻ ብለው የሚሰሩ የዳእዋ ሰዎች በትክክል መጠቀም ካልቻሉ እድሉ መነሳቱ አይቀርም፡፡
2) የአላህ (ሰ.ወ) የምድር ህግ ሙስሊሙ ዑማ ሙስሊም ስለሆነ ኢስላምን ስለተከተለ ብቻ በነፃ የአሸናፊነት ዋንጫን አይወስድም፡፡
3) አቅሙና ችሎታው ያላቸው አስተዋይ ብቁ የዑማው ልጆች እራሳቸውን ለዳዕዋ ሰውተው ተራ በሆነና በዳዕዋ ዙሪያ የተፈጠሩ ስህተቶችን እየለቀሙ ሊያመላክቱና ሊያስጠነቀቁ ስህተቱ ከተከሰተ ደግሞ ከመስፋፋቱ በፊት በቀላል ኪሳራ እንዳይዛመት ማቀብ እንዲችሉ ሊቀሰቅሱ ይገባል፡፡

- አዳዲስ ስራ መስኮችን መጠቆምና የዳዕዋ ሜዳዎችን ማመላከት ማስተዋወቅ የዳዕዋ እንቅስቃሴ ደርቆና ከስሞ በሽንፈት ሙዳ ውስጥ እንዲቀርና እንዲሸነፍ ሊያደርገው አይገባም፡፡
- የዳዕዋን ስራ የማስተካከልና አቅጣጫ የመጠቆም ስራ መስራት፡፡
- የዳዕዋ ስራ ላይ በተሰማሩ ወገኖች መሀል የህብረትና የአንድነት ሜዳን ማስፋት በመሀከላቸው ያለውን ልዩነት ሜዳ ማጥበብ፡፡

## ችግሮችና አደጋዎች

ኢስላማዊ እንቅስቃሴ በአላህ ፍቃድ መጥቷል፡፡ ሰዎችም ተደስተዋል፡፡ መልካም ተስፋም ቀርቧቸዋል፡፡እዚህ እንቅስቃሴ ላይም እንዲያብብ ተስፋቸውን ጥለውበታል፡፡

ስዕሉ ምሉዕ እንዲሆን እርግጠኛ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ እርሱም ይህ መልካም እንቅስቃሴ ችግሮችና አደጋዎች አካበውታል፡፡ አሰናካይ ጎጂ ነገሮችም ቀርበውታል፡፡አንዱ ሌላውን ይቃወመዋል ፡፡ እንዲሁም ይዋጋዋል፡፡ ተንኮል ይጎነጉንለታል ግጭት ይፈጥራል፡፡ ጦርነቱ ይፋፋማል ልዩነቱ ይሰፋል፡፡ በሙስሊሞች መሀከል ያለ ልዩነት በጥቅሉ በተለይ በዳዕዋ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች መሀከል ያፈጠጠ ያገጠጠ ችግር አለ፡፡ ቋሚ በሽታ መድህኒት የሌለው ወረርሺኝ መስሏል፡፡ አላህ የጠበቀው ሰው ሲቀር ፡፡ ነፃ የማይሆንበት ችግር ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች አሉ፡፡

እነዚህ ላይ የሚጨመረው በዳዕዋ ዘርፍ የተሰማሩ ብዙሀኖች ጥሩነትና ነገሮችን አቅልለው የማየት ባህሪ አላቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ዝንጋቴ ደረጃ አድርሰዋቸዋል፡፡ እነርሱ ውስጥ ሰርጎ ለመግባትና መጠቀሚያ ለማድረግ አንዳንድ ተነኮለኞች ይመቻቸዋል፡፡ አደገኛ አረንቋ ውስጥ ይወሽቋቸዋል፡፡ አጥፊ ጀብደኛ ይሆናሉ፡፡ እነርሱም ይሰቃያሉ አገርና ሰውም ፍዳውን ያያል፡፡እነርሱም በሰው ይጠላሉ በእነርሱ ምክንያትም ኢስላም ይጠላል፡፡ እነርሱ የኢስላም ማስፈራሪያ ይሆናሉ፡፡ እንደዚ አይነት ሰዎች መሀይምነት ደምቆ የሚታየው የፖለቲካ ሜዳ ነው፡፡ እነርሱ በዚህ ሜዳ የመጀመሪያ ታጋዮች እና መስዋእትነት ከፋዮች ነበሩ፡፡ከዚያም እነርሱ እራሳቸው መስዋት ሆኑ፡፡ከባድ ዋጋ ከፈሉ፡፡ አገር ህዝብም ከባድ ዋጋ ከፈሉ የአገርና የህዝብ ከባድና አስቸጋሪው እርሱ ነው፡፡ እንህ አይነት ችግሮችን የአንድ ሰበብ ውጤት ነው ማለት አይቻልም፡፡ወደ ተለያዩ

ውስብስብ ችግሮች ልንከፋፍለው ግድ ይለናል ከፊሉ ግልፅና ቀጥተኛ ሲሆን ሌላው ውስብስብና ቀጥተኛ ያልሆነ ነው፡፡የዋህነት፣ ዝንጉነት፣ ችኩልነት ግብዝነት የችግሩ አይነት ናቸው፡፡ እንዲሁም በሌሎች ተንኮል በቀላሉ መውደቅናየተንኮል መረብ አስፈፃሚ መሆን፣ የአላህ (ሰ.ወ) የምድር ስርአትናየዩንቨርሱን የማይቀየሩ ስርአቶች መዘንጋት፣ በሀይማኖተኝነት ሽፋን የግል ሀብትን ለማደራጀት ስልጣን ለመያዝ ቂምን ለመወጣትና ለመበቀል የሚደረግ ጥረትም የችግሩ ክፍል ነው፡፡ ሌላው የሰዎች የግንዛቤና የመረዳት አቅም ነው፡፡ ኢስላም እያለፈበት ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ አለመረዳት፡፡ ይህም አደገኛና አስቸጋሪ የተደራረበና በተለያየ ጎን የሚንፀባረቅ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚያሳድረው አዋኪ ሂደትም ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ የኢስላማው የዳዕዋ እንቅስቃሴ ነው፡፡ አስቸጋሪና ውስብስብ ሁኔታ በዚህ መልኩ ስፋቱና ጥልቀቱ ከተገለፀ ይህንን ዘርፈ ብዙ መከራና ችግር መቅረፍ የሚቻለው አንድ መፍትሄ በማቅረብ ብቻ ሊሆን እንደማይችል መረዳት እንችላለን፡፡ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ምሉዕ የሆነ ሰፊና ጥልቅ እርስ በእርሱ የሚደጋገፍ ሁሉም በተለያየ መስመር የሚደጋገፉ ሲሆን ነው፡፡

## <u>መነሻ ነጥብ</u>

ምን አልባትም ከቀረቡት መፍትሄዎች ውስጥ ቅድሚያሊሰጠው የሚገባ የተለየ የመነሻ ነጥብና መፍትሄ አሉ፡፡እነርሱም በኢስላማዊ የዳዐውዋ መስክ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን አጠቃላይ ህጎች ማስተካከል ነው፡፡ ያም የሆነበት ህጎች በከፍተኛ ደረጃ የሰውን ጠቅላላ ግንዛቤ እና እርሱ ዘንድ ነገሮችን የማስተካከያ መንገዶችን ስለሚዳኝ ነው፡፡ የስራ ምክንያቶችና የአሰራር ዘዴዎችን በትክክል መረዳትና ማወቅ የዳዕዋ ስራ ዋና መሰረቶች ናቸው፡፡ቅድሚያ ሊያገኙም ይገባቸዋል፡፡ የተሳሳተ

የተንጋደደ አመለካከት ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራል፡፡ የተስተካከለ እይታ ወደ ትክክለኛ እይታ ያዳርሳል፡፡

መጀመሪያ ማንም ሰው መሰረታዊ አቅምን መገንባት ብቻ ሁሉንም ነገር ማስተካከል ነው ማለት እንዳልሆነ ይረዳል፡፡ ግና በከፍተኛ ደረጃ ችግሩ እንዲስተካከል ይረዳል፡፡ማለት ይቻላል፡፡

ይህን የዳዕዋ ንቃት እና እንቅስቃሴ በከፍተኛ ትኩረት ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ማስተካከያና አቅጣጫ መጠቆም ያስፈልገዋል፡፡ይህ ስራ የሰው ስራ በመሆኑ ስህተትና ትክክለኛነት ይኖረዋል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ከውጭ የሚመጣ አደጋ እንደሚያሰጋው ሁሉ የውስጥ ጥቃት ሊከሰትበትም ይችላል፡፡ውስጣዊ ጥቃት የሚያደርሰው አደጋ በጣም አደገኛ እና አፍራሽ ነበር ሁንም ነው፡፡

ከውጭ የሚሰነዘር አደጋ ከኢስላም ጠላቶች ከተለያየ መስመር ሊያጠቃ ይችላል፡፡የውስጥ አደጋ ግን ከዳዕዋው እንቅስቃሴ ማህፀን ውስጥ የሚወለድ የተሳሳተ ግንዛቤ የተንጋደደ አስተሳሳብ ያልተገራ ግለኝነትና ራስ ወዳድነት አልያም ከእውነታ ጋር የማይራመድ ችኩልነት ወይም ከተጨባጭነት ጋር የማይጣጣም ምናባዊነት ውጤት አደጋውና ችግሩን ሊፈለፍሉት ይችላሉ፡፡

ለዚህ ነው የተከበረ የዳዕዋ ስራ ስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት ያስፈለገው ይህ በዳዕዋ ውስጥ የተሰማሩ ሠራተኞችን ሁሉ የሚያቅፍ መሰረታዊ ነጥቦችን አጠቃልሏል ይህ የከብር ሥምምነት ሰነድ አስተዋጁችን ቀኖናዊነት ያላጨውን ወገኖች ሁሉ ሊያስተናግድ የሚችልጥልቅ እና ሰፊ ሰነድ ነው፡፡

በጋራ በሆነ ክልል ውስጥ ልዩነት ሊስተናገድ የሚችሉበት ተዘጋጅቷል ፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በሁሉም ነገር የሚመሳሰሉ ተደጋጋሚ ኮፒዎች

አይደሉም፡፡ይህ እንዲህ ተብሎ ሊጠራ የሚችል አርማ ነው፡፡ " በአንድነት ክልል ውስጥ የሚኖር ልዩነት ፡፡"

ለዚህ ሲባልና ሀላፊነት የመወጣት ፍላጎትና ጉጉት እንዲሁም ምክር የመስጠት የማስተካከልና አዳዲስ መስመሮችን የመጠቆም ግዴታን ለመወጣት ሲባል እነዚህን መሰረታዊ ዋና ዋና ነጥቦች ስናቀርብ ይህን መገንዘብ እንዲሁም ነዚህ መገልገል ለዳእዋ ንቃትና እንቅስቃሴና የወደፊት ግስጋሴ ላይ ስር ነቀል ለውጥ ይመጣል፡፡ በዚህም መልካምና ምርጥ ውጤት በአላህ ፍቃድ ያስገኛል፡፡

ሊታወስ የሚገባው ነገር እነዚህ መሰረቶች የተገኙት በጥረት፣ በመከራ ውስጥ በማለፍ፣ በማስተንተን፣ በመገምገም፣ ማንበብ ና በዳዕዋ መስመር ላይ የተገኙ ድክመቶችን እና ውጤቶችን ለረጅም ጊዜ በመከታተል የተደረሰበት ውዴታ ነው፡፡ እዚህ ውስጥ ከተካተቱት ነጥቦች ውስጥ ቃሉ እራሱ እዚህ እና እዚያ የተዘከሩ ቀደምት ጠቃሚ የተባሉ ነጥቦች አሉ፡፡

## የክብር ስምምነቱ አላማ

ይህ የክብር ስምምነት አላማ ሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አክብሮት የሚያገኝ ሰነድ እንዲሆን ታልሟል፡፡ይህ ከተሳካ ውጤቱ በጣም ብዙ ይሆናል ዋና ዋናዎቸሁ ፋይዳዎች ፡-

- በዳዕዋ ሰዎች ፍቅርና መተማመን ይነሳል፡፡
- በህዝባዊና በህጋዊ የዳዕዋ ተቋማት መሀከል መቀራረብ ይፈጠራል፡፡
- የስህተትና የግጭት ሜዳው ይጠባል፡፡
- የስምምነት እና የስኬት እርከኑ ይጨምራል፡፡
- ገንቢ የሆነ የግምገማ እና የሂስ መንፈስ ይጎለብታል፡፡
- የአመለካከት እና የአስተሳሰብ አድማስ ይሰፋል
- ያልተሄደበት ስልትና ፈጠራ አቅጣጫ ይዘረጋል

- የጋራና የአንድነት ነጥቦች ላይ መተጋገዝ
- በልዩነት ጉዳዮች ላይ መተላለፍ እና ይቅርታ መደራረግ
- ከስራ ፈትነት ሜዳ ወደ ተግባር እና እንቅስቃሴ ጎራ ይገባል፡፡

የዚህን የዳዕዋስራ የስምምነት ውል አላማ በአጭር አመላካች ቃላት መግለፅ ከፈለግን "የዳዕዋ ስራ አካሄድ ማስተካከል፡፡ በዳዕዋ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ማቀራረብ ለዳዕዋ ስራ አዲስ አቅጣጫ መጠቆም" ልንለው እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ይህ የስምምነት ውል ለሁሉም የተላከ ነው፡፡ግና በተለየ መልኩ የዳዕዋ ሰዎችን ይመለከታል፡፡በጣም ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡እነርሱ ይህንን ሰነድ ሊያስተካክሉት እንዲሁም ሊጨምሩበት አቅሙ አላቸው፡፡

## ልንደርስበት የምናልመው ታላቅ ግብ

ይህ የስምምነት ሰነድ "የተግባር ሰነድ " ነው፡፡ ከቁርአንና ከሱንና የተቀዳ፤ ከፅንፈኝነትና ከግትርነት የላቀ ሚዛናዊነትንና ልከኝነትን የሚገልፅ የተወሰነ ፓርቲን መልከ ወይም ስብስቡን፣ ቡድንን የዳዕዋ አቅጣጫና መስመርን የፊቂህ ጥናትና ምርምር ውጤትን የአህጉር ተቆርቋዋሪነትን ያልያዙ ለአንዱም ቡድን ወይም ግሩፕ የማይዘነበልና ሌሎችን የማያናንቅ ንፁህ የስራ አፈፃፀም ሂደት ነው፡፡

ሌላው የዚህ ሰነድ አላማ ለዳእዋ ሰዎች የአስተሳሰብ ሥነ-ምግባር የትምህርት የተግባር መተዳደሪያ ገዥ ውል እንዲሆን ነው፡፡ሁሉንም የሚገዛ የሚነሱበት እና የተቀበሉት በዘርፉ የተዘጋጁ ጠንካራና ፈዋሽ መፅሀፍቶች ጋር የሚደመር በአይነቱ ልዩ የሆነ ጭማሪ ነው፡፡

ይህ ሰነድ ሊያግዝ የሚፈልገው

- የምድራዊ የመጪው አለም የደስታ ምንጭ ለሆነው ለኢስላም፡፡

- የማንነታችን መገለጫና መጠሪያ ለሆነው ዑማ በዚህ የእኛ መጠሪያ እንደሰታለን እንኮራለን፡፡
- ለዳዕዋ ስራ በህይወት ወስጥ የተከበረ የነብያቶችና የመልዕክተኞች ሙያ
- ዲንን ቋንቋና ታሪክን፣ ፍጡራንን ትናንትን ዛሬን ነገን ጠቅልሎ ለያዘው አገር፡፡
- ለመጪው የዳዕዋ ትውልድ ብዙ ስኬትና ጥቂት ስህተት እንዲኖራቸው ስለዚም፡- እያንዳንዱ ነጥብ በአግባቡና በጥንቃቄ በታማኝነት በፍትሃዊነት በግልፅ ሚዛናዊ እና ግልፅ በሆነ ሚዛናዊ አቀራረብ ከፍተኛ የስርአት መንፈስን በያዘ በተገራ ቋንቋ በቁጥብ ምላስ የቀረበ ነው፡፡የሚያነበው ሰው ከዚ ሰነድ ኋላ ያለው መልዕክት እውነተኛ እንጂ ውሸት እንዳልሆነ እንዲረዳ፡፡እሩቅ ተመልካችና የመልካም ውጤት ጉጉት እንዳለው እንዲገነዘብ ሆደ ሰፊ ከልብ የመነጨ የዳዕዋ ሥር ጉጉት መኖሩን ያሳያል፡፡

## ማጠቃለያ

ይህ ሰነድ መሪ ብርሀን እንዲሆንና የዳዕዋ ሰዎችን የሚያገናኝ የሚያስተማምን ከራስ በመነጨ ውስጣዊ ፍላጎትና ምርጫ ላይ የተመሰረተ እውነተኛ እና የስኬት ጎዳና ላይ የሚያደርስ እንዲሆን ይታለማል፡፡
ስለዚህም ስያሜው "ሚሳቅ አሽረፋ አዳዕዊ" ተባለ፡፡ ምክንያቱም በዚህ ሰነድ ዙሪያ ለመሰብሰብና ለመተማመን በነፃ እምነት ላይ መመስረትና በፍቃደኝነት እራስን ማስገደድ ይሻል፡፡ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ታዛዥነት ወኔና ብርታት ውስጥ የጠለቀ እምነትና ይህ ሰነድ ጠቅልሎ በያዛቸው መልዕክቶች መማረክና መደሰት ይፈልጋል፡፡
ሌላው የሚፈለገው ነገር ይህ ፅሁፍ ቀኖናዊ የሆኑና ብቃት ያላቸው የዳዕዋ ሰዎች ትክክለኛና የምር የሆነ ጥናት አንዲያደርጉበት ከመልካም ነገሩና ከስኬቱ እንደማሩ ስህተቱን እንዲጠቁሙ አዳዲስ መሰረቶችን እንዲያሳዩ

እንፈልጋለን እያንዳንዱ ሕትመት ከበፊቱ የተሻለ እና የበለፀገ ይሆን ዘንድ አንተን የሚያስደስትህን ያህልም አንተ ከተደሰትክ በኋላ ምስጋና ይገባህ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

አምላካችን ሆይ! አንተ ዘንድ የሚያስወድደንን ሥራ እንድንሰራ አድርገን ለመልካም ተግባር አውለን ውስጣችን መልካም ነገርን ለአንተ ብቻ ብሎ እንዲያስብና ስኬትን ለግሰን፡፡ አንተን የማያስደስትህን ያህል ምስጋና ይገባህ፡፡

በአላህ መልዕክተኛ መህሐድ (ሰዐወ) ላይ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ የአንተ ሰላትና ሰላም ይስፈን፡፡

<u>የውል አንቀፆች</u>

1) <u>**ሙሉዕ ኢማን**</u>

በአላህ (ሱ.ወ) እናምናለን፤ እርሱ የፍጥረት አለሙ ፈጣሪና ገዥ ነው፡፡ በእውነት የሚመራ እርሱ ብቻ ነው፡፡ በሁልነተናዊ የበላይነት፣ሙሉዕነትና ውበት ይገለፃል፡፡ ከሁሉም አጥነት ጉድለት የፀዳ ነው፤ እንወደዋለን፡፡ በብቸኝነት እናመልከዋለን፤ እናከብረዋለን፤ እንፈራዋለን እንከጅለዋለን፡፡ ሙስሊሞችን በአጠቃላይ የዳዕዋ ሰዎችን በተለየ ሁኔታ የምናሳስበው ጉዳይ አለ፡፡ ይህም የኢማንን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ በሁሉም የግንዛቤ፣ የእምነት፣ የመንፈስና የስብዕና ጉዳዮች ላይ የኢማንን የበላይነት መጠበቅ ከሁሉም ነገር በተለየ ቅድሚያ መስጠት ኢማን የመጀመሪያ፡፡ ኢማን የመጀመሪያ ትልቁ መሰረት ነው ፡፡ የዲን ጉዳይ ዋናውም ዝርዝሩም የሚገነባው ኢማን ላይ ነው፡፡ ኢማን ሁሉንም ነገር ይጠቅልላል፡፡ የሙስሊም አቂዳ ሁለንተናዊነት በኢማን ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እንዲሁም የሙስሊም ህይወት ሁሉም ነገር በኢማን የተሳሰረ ነው፡፡

ዐቂዳ አንድ ኪታብ አንድ ርዕስ አይደለም፡፡ እንዲሁም ተነብቦ የሚዘጋና ወደ ሌላ ክፍል የሚራመዱበት አይደለም፡፡ አቂዳ በመጀመሪያ ክፍል

ሙስሊም የሚያነበው ከዚያም አብሮት እስከ መጨረሻ የሚዘልቅ ጉዳይ ነው፡፡ዐቂዳ ሙስሊምን በሀሳቡ በስሜቱ በተግባሩ የሚቆራኝ እስከመጨረሻው የህይወቱን የሚገዛው እምነት ነው፡፡

ይህ ከሚያመጣቸውና ከሚያስመዘግባቸው ውጤቶች አንዱ ሙስሊም በጥልቅ በጥንቃቄ በምሉዕነት የአቂዳን ተከታዮች ማወቅ አለበት፡፡ ዋናው፡

- አላህን አንድ አድርጎ ማምለክ
- የአላህን ህግጋት መፈፀም

የዐቂዳን ዋና ከዲን ሙሉዕ በሙሉዕ የሚያወጡ፣ አልያም በከፊል የሚያበላሹ ነጥቦችን መረዳት፡፡ በጣም ከሚገርሙ ነገሮች ውስጥ ህፃናት ውዱዕ የሚያጠፉ ነገሮችን ያውቃሉ፡፡ በአንፃሩ ዐቂዳን የሚያፈርሱ ነገሮችን አያውቅም፡፡ ለነገሩ ሁሉም አስፈላጊ ነው ሆኖም በዐቂዳ እና በውዱዕ መሀከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡
በሌላ ጎን ጥንቃቄ የሚያሻው ተውሂድ ጉዳይ እንደ ኮምፒዩተር ሸምደዳ ብቻ ሳይሆን መልዕክቱን በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የተውሂድ ተልዕኮ ሳይገባቸው የሸመደዱት ሰዎች እነርሱ በትክክለኛ ጎዳና ላይ እንዳሉ ይሰማቸዋል፡፡ በመሀከላቸው የመኩራራትና የበላይነት ትዕቢት ይወጥራቸዋል፡፡ከእነርሱ የተለየ ወገን ጋር ያላቸው ግንኙነት የኩራትና ሻካራ ይሆናል፡፡ የያዙት እውነታና ሀቅ መሆኑን መረዳትና በራስ መተማመን የሚፈልግና የሚያስመሰግን ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ግንዛቤ ለሌሎችም መልካም ግንዛቤ ማዳበርን ማከል አለበት፡፡ ይህ ሲሆን እነርሱ ተወዳጅነትን የሚያተርፍ ስኬታማ የዳዕዋ ሰዎች ይሆናሉ፡፡ተውሂድ በህይወታቸው ውስጥ በተሸለ አስተሳሰብ መንፈስና ተግባር እይታቸው ያሰፋዋል፡፡

## 2) ኢስላም የአላህ ዲን ነው

ኢስላም የአላህ(ሱ.ወ) ዘላለማዊ ጥብቅ ትክክለኛና የመጨረሻ ዲን መሆኑን እናምናለን፡፡ ኢስላም እኛ ዘንድ ዋና ቁም ነገር ማንነት፣ መፍትሄ፣ ትናንት ዛሬ ነገ ነው፡፡ኢስላም በምድራዊውም ሆነ በመጪው አለም የደስታችን ምንጭ ነው፡፡ አላህ(ሱ.ወ)የመረጠልን የህወይወት መመሪያችን የምናምንበት የምንመካበት ለእርሱ የምንታገልበት ያለንን ውዱና ከባድ ነገር ሁሉ የምንሰዋለት ዲን ነው፡፡

## 3) ወደ መሰረታዊ መነሻዎች መመለስ

እኛ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም ነገርን እንመኛለን ወደዚህ ምርጥና ድንቅ ዲንም ሰዎችን እንጠራለን፡፡ ኢስላምን በትክክለኛ ምንጩ በንፁህ ልቦና በፍትሀዊ አእምሮ ላይ ተመስርተው እንዲቀዱ እና እንዲማሩ ጥሪ እናደርጋለን ኢስላምን ከተማሩ በኢስላም ውስጥ ቅንን መንገድ ከጥሜት በኋላና ከፍርሀት በኋላ ሰላምን፣ ከስጋት ስክነትን ከበሽታ በኋላ ጤናን እንደሚያገኙበት እርግጠኞች ነን፡፡እነርሱ ከኢስላም ውስጥ ለሁሉም ችግሮቻቸው መፍትሄ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ያገኛሉ፡፡

## 4) የመጀመሪያው ሁለንተናዊ የሰው ልጆች ሰብአዊ መብት አዋጅ

ኢስላም የመጀመሪያው አለም አቀፋዊ እና ሁለንተናዊ የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብት ያወጀ ዲን መሆኑን እናምናለን፡፡ ኢስላም ለሰው ልጆች ሰብአዊ መብት የቆመ ዲን ነው፡፡ የእምነት ነፃነት፣ የሰው ልጅን ክብር፣ የመማር፣ የማግባት፣የሰላም፣ የምግብ፣የፍትህ፣ ንብረትየማፍራት መብቱን ሁሉ ያከብራል ፡፡ ለዚህ ሁሉ መነሻው ለሰው ልጅ ያለው አክብሮትና ቦታ ነው ሰው የአላህ (ሱ.ወ) የተከበረ ፍጡር ነው፡፡ የምድር ላይ

አስተዳደራዊ እና ተወካዩ ነው፡፡በዚህ ምድር ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ የሰው ልጅ መገልገያ ነው፡፡

## 5)<u>ኢስላም የአላህ ዲን ነው</u>

የሰው ልጅ አንድ ቤተሰብ መሆኑን እናምናለን፡፡ ሁሉንም የሚሰበስበው በሰውነት የሚያስተሳስረው ወንድማማችነት ነው፡፡ የሰው ልጅን የፈጠረው አላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡ የሰው ልጅ አባት አደም እናት ሀዋ ናት፡፡ የተፈጠርነው ከአፈር ነው፡፡ ወደ እርሷም እንመለሳለን፡፡ስለዚህም ሙስሊሞችን እንዲሁም ሌሎቹን ሁሉ የጋራ ትብብር እንዲያደርጉ ለሰው ዘር የሚጠቅም ነገር መፈጠም እንዲችሉ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡ ከዚህም ውስጥ ሰላምን መጠበቅና መፈጠር ነፃነትን ማበረታት ፍትህን ማንገስ ወንጀልን መዋጋት እውቀትን መርጨት፣ ህፃናትን መንከባከብ፣ አለጋውያንን መጦር፣ ጉርብትናን ማሳመር አካባቢን መጠበቅ ቃልንና ውልን ማክበር.......

## 6)<u>ቤተሰብን መጠበቅ</u>

የወንድና የሴት ጋብቻ መመስረት ብቸኛው ቤተሰብ የመፈጠሪያው ሸሪአዊ መንገድ ነው፡፡ ይህም የመጀመሪያው እና በጣም አስፈላጊ የሆነ የቤተሰብ መጠበቂያ ስልጠና የሚወሰድበት ማዕከል ነው፡፡ ቤተሰብ የህብረተሰብ ዋናው አስኳል ነው፡፡ ለህፃናት ለታዳጊዎች ተፈጥሮአዊ የእድገት ስፍራ ነው፡፡ ቤተሰቡን የማስተዳደር ዋና ሀላፊነት የሚወድቀው በአባትና እናት ላይ በጥምረት ነው፡፡ ስለዚህም የቤተሰቡን አስፈላጊነት ቤተሰብን እንዳይፈርስ የመጠበቅ፣ ታላቅነቱንም የማወጅ ፣ የተሳካ ቤተሰባዊ ግንኙነት ለመፍጠር አጋዥ ነገሮችን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ

እናሳውቃለን፡፡ ከየትኛውም በኩል የሚመጣ ቤተሰብን ለማፈረረስ ወይም አስፈላጊነቱን ለማቃለል የሚጥሩ ክሎፍችን በከፍተኛ ደረጃ እንቃወማለን፡

## 7) ሀላፊነትን ማጋራትና በሰላም መቀባበል

የዳዕዋ ሰዎች መዋቅሩ የተስተካከለ ፣ ግልፅና ቆራጥ አሰራር ውስጥ እራሳቸውን ማስገባትና ለመርህና ህግጋት መገዛት አለባቸው፡፡ይህም በዳእዋ ተቋማቸው ውስጥ ሀላፊነታቸውን የሚጋራቸውና በሰላም በፍቅር የሚተካና የሚሰሩበት ሁኔታን ይፈትርላቸዋል፡፡ ይህ አካሄድም አድሏዊነትን ፣ እራስን ብቻ ማበፀግን ፣ ኑዛዜያዊ አሰራርን ያግዳል፡፡ ስንፍናንና ፀረ- ለውጥ መሆንን ያግዳል፡፡ የእድሳትና የፈጠራ እድልን ያመቻቻል ፡፡ በትውልድ መሀከል ድልድይ ይፈጥራል፡፡ የተቻለውን ያህል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መሪዎችን ለመፍጠር ያግዛል፡፡ የቡድን ስራን ወደ ተሸለ ደረጃ ያሸጋግራል፡፡ የተቋማዊን ስራን ክብርና ስርአት እንዲከበር ያደርጋል፡፡

## 8)የመኖር አርማ

መልካም ነገርን ወንድማማችነትን መተጋገዝን ከሁሉም ጋር እንዲሰምርልን እንጥራለን ከእኛ ጋር ልዩነት ያላቸውን ወገኖች ልዩነታቸውን እናከብራለን፡ " የሸይክ ሙሀመድ ረሺድ ሪዷን" የመናር (መጽሄት) አርማ እናነግባለን፡፡ “በተስማማንባቸው ነገሮች እንረዳዳለን፤ ባልተስማማንባቸው ጉዳዮች ላይ እንተላለፋለን”

## 9)ምክክር

ወደ ምክክር ሀሳብን ወደ ማፍለቅና ወደ ፈጠራ ስራ ሰዎችን እንጠራለን፡፡ የሚቃወምንም ሆነ የሚስማማን ሀሳብ በእኩልነት ማክበር ፣ ለሁሉም ሰው የማሰብና ሀሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብቱን አንነፍግም፡፡ ሁሉም ግን መጨረሻ ላይ በምክክር የተወሰነን ውሳኔ የማክበር ግዴታውን መዘንጋት የለበትም፡፡ ይህም የሚሆነው የተወሰነው ውሳኔ ግልፅና አጠቃላይ የሆነውን የሸሪአ መሰረቶች አስካላፈረሰ ድረስ ብቻ ነው፡፡ውሳኔው ትክክል ወይም ለትክክልነት ቅርብ እንስኪሆን ድረስ ከታወቁ መሪዎቹና ሀላፊዎቹ በኩል ብቻ ውሳኔውን መተላለፍ አለበት ፡፡ ይህ እንዲሳካ የውሳኔ ሰዎቹ ዘንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሙሉዕ መቅረብ አለባቸው፡፡ እውነተኛ እምነት የሚጣልበት ፣ ነጥብ በነጥብ የሚወያይበት እድል ሊኖር ይገባል፡፡

## 10) አንድ ወሳኝ አካል

በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጉዳይ የዳዕዋ ስራ ሁለት ወሳኝ አካላት ሊኖሩት አይገባም፡፡ ይህም ማለት አንደኛው ግልፅና ይፋ የሆነ ውጫዊ ገፅታ ብቻ ያለው ፣ ሁለተኛ ድብቅና ትክክለኛ ሚናው በግልፅ የሚታየውን አካል እንዳሻው መዘወር የሚችል ማለት ነው፡፡
ግልፅ አካል ስዕል ሲሆን  ድብቅ ደግሞ ተፈፃሚ ነው፡፡ ድብቅ አካል ለብቻው ያሻውን የመወሰን አቅም አለው፡፡ግልፅን አካል እየቀደደ ይሰፋዋል ይህ አካሄድ ማጭበርበርና ማታለል ነው፡፡ መሰረታዊ የሆነውን የዳዕዋ አካሄድ ይፃረራል፡፡ በተለይ የሹራን መሰረት ያናጋል፡፡ ህጋዊና ሸሪአው የሆነን ውሳኔ ህጋዊ እና ሸሪአዊ ባልሆነ ውሳኔ መሻር ነው፡፡ ይህ ግልፅ የሆነ አምባገነንነት ነው፡፡ በሀይማኖታዊ ጉዳይ ላይ አምባገነንነት

በምድራዊ ጉዳይ ከሚታይ አምባገነንነት በጣም የከፋ ነው፡፡ ለሚፈለገው ጉዳይ የተጭበረበረ ዲናዊ ልብስ ማከናነብ ነው፡፡ እንዲህ አይነት የማይገባ አካሄድ ከሚያመጣቸው ጣጣዎች ውስጥ የድብቅነት ወሳኝ አካል የግልፅ ስብስቡን በንቀትና በበላይነት ይመለከተዋል፡፡ የግልፅ ወሳኝ አካላት የድብቅ አካላትን በቅሬታ እና በመበሳጨት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ይኖራቸዋል እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ዘንድ የተናቁ እና ደካማ ይሆናሉ፡፡ ይህ አካሄድ ጥላቻን ምቀኝነትንና ውድቀትና ውርደትን ይፈለፍላል፡፡ እንዲህ አይነት የሁለትዮሽ መሪ ያላቸው የዳዕዋ እንቅስቃሴዎች በዚህ ምክንያት መራራ ዋጋዎችን ከፍለዋል፡፡

## 11) <u>ተቋማዊ ስራ</u>

የተደራጀ ስራ ያለው ተቋማዊ ስራ እምነት አለን፡፡ በመጀመሪያ ኢስላማዊ አኽላቅን በመቀጠል የተቀመጡ ድርጅታዊ መርሆችን እና ስረትአቶችን የሚገዙትን ተቋም እንወዳለን፡፡ ተቋማዊ ስራዎች በመጨረሻ ለዑማው በጣም ጠቃሚ መሆናቸው ላይ በጣም እርግጠኞች ነን፡፡ ተቋማዊ ስራ ከግለሰብ ልፋትና እድሜ የተሸለ እርዝመት ስላለው ሁሉም ጥሩ ነገሮች አሏቸው፡፡

ተቋማዊ ስራ እራሱን ለመገምገም አቅሙና ችሎታው አለው፡፡ እንዲሁም ለማስተካከል ለመቆጣጠር ለማሻሻል የተሸለ እድል እንዳለው በጣም እናምናለን፡፡ ከዚህም ግለሰቦች ይጓዛሉ፡፡ ከእነርሱ በኋላ ቀጣይ የሆነው ተቋም ይቀጥላል፡፡

## 12) <u>የቡድን ስሜት</u>

የዳዕዋ ሰራተኞች መሀከል የቡድን ስሜት ስር እንዲሰድ እንዲገባ እንጥራለን ፡፡ በሰራተኞች መሀከል የጋራ ስራ ፣ ባኅል ሸርዖ መግባቱ

አስፈላጊ ነው፡፡ እንደዚሁም አንጋፋ ሰራተኞችን ማክበር ፣ ከተተኪ ትውልዶች ጋር የሚኖርን ግንኙነት ማጠንከር የአንጋፋዎች የሚከተሉት አርአያሊከተሉት የሚገባ ናሙና ይሰበስባል፡፡ የወጣቶችን የጋለ ስሜት በአግባቡ ማዋል መቻል፡፡ እንዲሁም የቡድንን መብትና ጥቅም ከግለሰብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ችግሮችንና ልዩነቶችን ከመከሰታቸው በፊት መከላከል የሚቻልባቸውን ሽሪአዊ፣ ሰለጠነ ፣ ዘዴዎችንና ስልቶች ላይ ቀድሞውኑ መስማማት፡ችግሩ ከተከሰተ በኋላ በተሸለ መንገድ ችግሮቹን መፍታት መቻል፡፡ በሰራተኞች መሀከል የገንዘብ የአስተዳደር ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ፡፡

## 13) ለጠንካራና ተሰጥኦ ላላቸው ሰዎች ትኩረት መቸር

ጠንካራ እና ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች የተለየ ትኩረት መቸር እንደሚያስፈልግ እናምንበታለን፡፡ እነርሱም የለውጥና የእድገት ፋና ወጊዎች ናቸው፡፡ ሀሳባቸውን አደራጅተውና አጠናክረው የተሻሉ አማራጮችን የወደፊት አዋጭ መንገዶችን መጠቆም ይችላሉ፡፡

## 14) ታላቅ አርአያ

የትኛውም የዳዕዋ ተቋም በመሰረቱ ፣ በአካሄዱ ፣ በዕቅዱና ፣ በተቋሙ የሚሰሩ ሰራተኞችን ስነ ምግባር ለተሳካለት ጥበበኛ የዳዕዋ ስራ ተምሳሌትነት መልካም አርአያ መሆን መቻል አለባቸው፡፡ ማለትም ሌሎች ሲመለከቱት ይደነቁበታል፡፡ የእርሱን አርአያ ተከትለው በእርሱ መንገድ ይሰራሉ፡፡

## 15) <u>አርቆ የሚተልም ለውጥ</u>

ተከታታይ የሆነ የዳዕዋ አካሄድና ለውጥ አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን፡፡ የማይነቀነቁ መሰረቶች ደግሞ እናከብራለን ፡፡ በዚህ አካሄድ ሁለት ነገሮች ይሰበሰባሉ፡፡ እርሱም የበፊት ጠቃሚ ቁም ነገር ይቀስማል በተጨማሪ አዲስ ለውጥን ያመጣል፡፡ በውስጡ ከዘመን ጋር መጓዝናየዘመንን ጉዳዮች መረዳትን ይሰበስባል ይህ አካሄድ ህያውነትን ያላብሰናል፡፡ ከስንፍና ከኋላ ቀርነት እና ከድርቅና ይጠብቀናል፡፡

## 16) <u>ራስን መቻል</u>

ራስን መቻልን ለማሳካት ጥረት መደረግ አለበት፡፡ በተቻለ መጠን በራስ አቅምና ችሎታ ልክ መራመድን እንመክራለን፡፡ ምክንያቱም እገዛና እርዳታ ስር መኖር ቀጣይነት የላቸውም ዋስትናቸውም ደካማ ነው፡፡ አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ለዚህ አካሄድ ዋናው ስልት ሁኔታዎችንና ችሎታዎችን ያማከለ የወቅፍ ተቋማትን መገንባት ነው፡፡

## 17) <u>ተፈጥሯዊ ህግጋትን ማክበር</u>

የአላህ ለባሮቹ ከሰጠው ፍትህ እዝነት ውስጥ አላህ (ሱ.ወ) የአላህ (ሱ.ወ) ለቡድን ለግለሰብ ወይም ለዲን የተለየ እገዛ ወይም ጠላትነት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ አላህ የፈጠረው አለም ውስጥ ሁሉም እኩል ነው፡፡ ይህንን የተፈጥሮ ህግ ተረድቶ በአግባቡ የሰራ ምንም ይሁን ይሳካለታል፡፡ ያጠፋ እና የማይረባ ስራ የሰራ ማንም ይሁን ይከስራል፡፡ ይህ ማለት አላህ ለሙስሊም ግለሰብም ሆነ ቡድን እስልምናን ስለተቀበለ ብቻ ነፃ ድልን

አያጎናፅፈውም፡፡ ምድራዊ ምክንያቶችን መጨበጥ እና ለስኬት የሚያበቁ መንገዶችን መራመድ ግድ ይላቸዋል፡፡

## 18) <u>አስፈላጊ የሆኑ ጨዋታዎች</u>

ጨዋታ ፣ ሳቅ ፈታ ያለ ግንኙነት አባላት ከድርጅታቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከሚያጠነክሩባቸው ዋና መሳሪያውች አንዱ ነው፡፡ ይህ ዘና ያለ ግንኙነት ለተቋማቸው ተቆርቋሪና ታማኝ እንዲሆኑ ለአስተሳሰቡም ቅርብና ታማኝ እንዲሆኑ፣ ቅርብና ጥሩ ተከታይ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ እኛ በተለያዩ ግንኙነቶች ጨዋታና ቀልድ መኖሩ ጠቃሚ ነው እንላለን፡፡ ከነዚህም ላይ ኢዶች ላይ የትምህርት የመጀመሪያና የመዝጊያ ጊዚያት ላይ፡፡ ዘና እና ፈታ ማለት መልካም ነው እንላለን፡፡ ስለዚህም በአላት እንዲኖሩ ግጥሞችና ዜማዎች እንዲዜሙ የእስፖርት ውድድሮች እንዲካሄዱ ሽልማቶችና ስጦታዎች እንዲበረታቱ .....እንመክራለን፡፡

## 19) <u>አላማዎችና ዘዴዎች</u>

መሰረታዊ አላማዎች ጽኑ ናቸው፡፡ የጎንዮሽ አላማዎች ደረጃዎች አሏቸው፡ አላማን ለመምታት የሚጠቅሙ ዘዴዎችና ብልሀቶች ሁሌም የሚታደሱና የሚለዋወጡ ናቸው፡፡ መቀያየር አይነታቸውን ማብዛት ሁሌም ሊቀጥል የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ ከሙስሊሞች እንዲሁም ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች መማርና ልማዳቸውን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ጥበብ የሙእሚን የጠፍ ሀብትና የትምህርት ማዕድ ነው፡፡ በተጨማሪም ሁሉም የዳዕዋ ስራ አካሄዶችና ዘዴዎች በሁለት መንገድና ስርአት ላይ የተገነቡ ናቸው፡፡

1) ችግር መኖሩ ሊቀረፍበት የሚችልበት ዘዴ አለመኖር ማጣት ፣ እውነተኛና ተጨባጭ ሊሆን ይገባዋል፡፡

2) የሚፈለገው ዘዴና ብልሀት በተግባር የሚለካበት ጊዜ ከጉዳቱ ይልቅ አትራፊነቱ ሊበዛ ይገባል፡፡

## 20)<u>ኢስላምና ኢስላማዊ ስራዎች</u>

በኢስላምና ኢስላዊ ስራዎች መሀከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ግድ ይላል፡፡ ኢስላም ዘላለማዊ እና ፍፁም ትክክለኛ ሀይማኖት ነው፡፡ ኢስላም ከፊቱም ሆነ ከኋላው ፍፁም ስህተት አይገኝበትም፡፡ ግና ኢስላማዊ ስራዎች የስራ ጥረት ውጤት ነው፡፡ ትክክልም ስህተትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡የአላህ (ሱ.ወ) ዲን የተቀደሰ ነው፡፡ ስህተት አይገባውም ፡፡ ኢስላምን ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚሰራ ስራ ግን ቅዱስአይደለም፡፡ ኢስላም ቅዱስ መሆኑ ኢስላማዊውን ስራና ጥረት ቅዱስነትን አያጎናፅፈውም፡፡ የኢስላማዊ እንቅስቃሴና ጥረት ድክመትና ስህተትም የኢስላምን ቅዱስነት አያጎድለውም፡፡

## 21) <u>አዋጭ ስልት</u>

ከዳዕዋ መስክ ላይ የተሸለው አካሄድ መጀመሪያውኑ ኢስላም የኢስላምን እውነታዎችና አንኳር መልእክቶች በትክክል፣ በግልፅና፣ በሙሉ ፅናት ማስተማር ነው፡፡

ይህ አካሄድ ትምህርቱን ለሚቀበለው ሰው አእምሮና መንፈስ አሳማኝ አርኪ ያደርገዋል፡፡ ኢስላምን ለመቀበል ያቀርበዋል፡፡ ስለዚህ ኢስላምን የምናቀርብላቸውን ሰዎችን አሻሚ በሆኑ ጉዳዮች ትምህርትን መጀመርና ለአዳሚ ነጥቦች መልስ መስጠት አግባብ ያለው አካሄድ አጥደለም፡፡ እኛም በአሻሚና በአጠራጣሪ ጉዳይ ትምህርት መጀመር የለብንም በሙስሊሞች መሀከል የተከሰተን ልዩነትና የአስተሳሳብ መራራቅን አልያም የጥናትና

የምርምር ውጤት የሆኑ (ኢጅቲሀዳዊ) ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰንቆ ይህ እንዲህም ነው፤ እንዲህ ነው ማለት አስፈላኢ አይደለም፡፡ እነዚህ ነጥቦችን ማሰማት የማይቀር ግዴታ ከሆነ በቀላሉና በትንሹ ማብራራትና መጨረስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም አካሄድ ዋናውንና መሰረታዊ የሆነውን የዳዕዋ አካሄድ ሊያናጋው አይገባም፡፡

## 22)ከሙግት መራራቅ

ከፅንስ ሀሳብ ክርክርና ሙግት መራቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጨባጭ አለም የሌሉ ምናባዊ መላምቶችን ማድረግም፣ ዘመን የረሳቸውን የጥናትና የምርምርውጤቶችን አጠራጣሪ መላምቶችን ውጤት አልባ ክርክሮችን መራቅ ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሂደት ጊዜን ገንዘብንና ቁም ነገርን ያባክናል፡፡ ከእውነተኛና ተጨባጭ ሀላፊነቶች ያርቃሉ፡፡ ሊለፋባጨው ከሚገቡ የእድገት ክርክሮች ያርቃሉ እንዲሁም (ብዙ ጊዜ ) ወደ ጥላቻና መራራቅ ውጤት እንዲሁም ወደ ከፋትና ቂም ያዳርሳል፡፡

## 23)በኢስላማዊ ተቋሞች ያለ ግንኙነት

በኢስላማዊ ተቋሞች ያለ ግንኙነት ፣ በመሰረቱ አንዱ የሌላውን ክፍተት የመሙላትና የመገንባት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ካልተቻለ መተጋገዝና መቻቻል ነው፡፡ ሌላኛው አራተኛ አማራጭ መጠፋፋት ነው፡፡

## 24)የግምገማ አስፈላጊነት

የግምገማ መነሻ ሀሳብ መሰረታዊ ምንጩ ኢስላም ነው፡፡ ግምገማ ከፍተኛ የስልጣኔ መገለጫና ስሌት ነው ስለዚህ እኛ ልንተጋና በተከታታይ

ልንፈፅመው ይገባል፡፡ ያም በግልፅነትና በይፋነት ከራስ በመነጨ ትችትና ዘወትር በሆነ ጥናት ቀጣይ በሆነ ግምገማ ነው፡፡ አውንታዊ ነገሮችን አውቀን እንድንጠብቃቸውና ከነርሱ ነፃ እንድንሆን ምክንያቱም የሰው ልጅ ስራ ለስህተትም ለትክክለኛነትም የተጋለጠ ነውና፡፡

## 25)<u>ለሙያና ለእውቀት አክብሮት መስጠት</u>

በሸሪአዊ ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ መጠይቆች የሸሪአ ሊቃውንትን መጠየቅ አለብን፡፡ ሙያዊ ቴክኒካዊ ጉዳችን ሊገጥሙን የረጅም አመታዊ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች እናማክራለን፡፡ ዘይድ የሚባል ሰው የተሳካለትና ስመ ጥር የዳዕዋ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ በተወሰኑ ሙያዊ ጉዳዮች ላይ የምርምርና የጥናት ጥረትና አቅም የለውም፡፡

## 26)<u>መልካም መንፈስ</u>

መልካም ነገሮች ላይ ትኩረት እንድናደርግ ተስፈኞች ፣ አብሳሪዎች ፣ አግራሪዎች መሆን ይገባናል፡፡ በአንፃሩ ከቀውፀ ተስፋ ፣ ከጨለምተኝነት ሰው ከማራቅ ፣ ከማካበድና ፀለምተኛ ከመሆን መራቅ አለብን፡፡

## 27)<u>የሚፈለግ መረጋጋት</u>

ከመቻኮልና ከግብታዊነት ጥበብን ፣ ግጭትና እረብሻ ከመፍጠር እርጋታን ፣ የህይወትን ክህሎቶችን ከመርሳት ችሎታና ክህሎትን በመካንና መፍትሄ በመፈለግ ፤ የህይወት ውስጥ ዋና እና ግንባር ቀደም ገንቢና አልሚ መሆንን እንመርጣለን፡፡

## 28)ሁለንተናዊ ዲን

ኢስላም አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጆች የላከው የመጨረሻው ዲን ነው፡፡ ይህም በመሆኑም ኢስላም ሙሉ የህይወት መርህ ነው፡፡ ለሁሉም የህይወት ጉዳዮች አቅጣጫ ያሳያል፡፡ ግለሰብን ህብረትን አገርን ይዳስሳል፡ ፡ ኢስላም ዲን ነው፡፡ አገር ነው ህግና ስርአት ነው ኢባዳ ነው ኢኮኖሚን ይዳስሳል፡፡ ስነምግባር ጤንነትን ፣ የቤተሰብን ግንኙነት ፣ ማህበራዊ ትስስርንና ፡፡ አለማቀፋዊ ግንኙነቶችን ይመለከታል ከዚህም ሌላ ያሉ የሂይወት ሂደቶችን ይመለከታል፡፤ኢስላም ሰውን ከውልደት ጀምሮ የህይወት ቆይታውን አክሎ ሞቱ ድረስ ፡፡ ከሞተ በኋላም አላህ ፊት መቆምን ይመለከታል፡፡ ስለዚህም የዳእዋ ሰዎች የኢስላምን ሙሉዕነትን መሰረታዊነት ሊያስገነዝቡ ይገባል፡፡ በዚህም ልበ ሙሉእነት ሊሰማውና ሊያምንበት ኢስላምን በአምልኮአዊ ተግባራት ብቻ ማሳጠርን ሊቃወም ይገባል፡፡ ሁለንተናዊነት ከሚያስፈልጋቸው ነጥቦች የተወሰኑት በቅርንጫፍና በሁለተኛ ደረጃ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው ፡፡ ቅርንጫፋዊ ነጥቦችህይወታቸውን ሊወስዱባቸውና መሰረታዊ እና አንኳር የሆኑ የዲን ጉዳዮችን ሊጨፈልቁ አይገባም፡፡ በቅርንጫፋዊ እና በሁለተኛ ደረጃ ሊታዩ የሚገባው ጉዳዮች ግንባር ቀደም ሆነው በግድ ከመጡ በተወሰነ ቦታ ጊዜና ሁኔታዎች በልካቸው ስር ታጥረው ብቻ ሊታዩ ይገባል፡፡

## 29)የውይይት ስርአት

የውይይት ስርአትና ጥበቦች መማር ያስፈልጋል ብለን እንመክራለን፡፡ ምክንያጡም ውይይት ለስኬታማ የዳእዋ ስልት ታላቅ ሚናይጫወታል፡፡ ከፍተኛ የውይይት አቅም ያጎለበተ ሰው ለቆመለት አጀንዳ የተሳካለት

ጠበቃ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ውይይት ክህሎት የሌለውም ሰው እንዲሁ ጉዳዩን ያቀጭጨዋል፡፡

30)<u>የጋራ ጎዳና</u>

የዳዕዋ ስራ አላማዎች ፣ ስልቶች ፣ ቅድመ ሁኔታዎችን አንገብጋቢ ጉዳዮች ሁሉም ዘንድ አንዳይነት እንዲሆን መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡ ትልቅም ይሁን ትንሽ ልዩነቶች መኖራቸው የማይቀር እውነታ ነው፡፡  በቁም ነገርና በትኩረት ከተጤነ ግን፣ ብዙ የኢማን ፣ የኢባዳ ፣ የመልካም ስነምግባር ፣ የማህበራዊ ህይወት ፣ ሂደቶች ፣ የንግድ ልውውጥ ብንመለከት፣ የአንድነት ፣ የህብረት ሜዳውን ሰፋትና ብዛት እናገኛለን፡፡ አስቸጋሪ ነጥብ ግን የግጭት ግንዛቤ ድርቅናን ስሜታዊነትን እና የበላጭነትን ስሜት ፤ ስለሚወልድ የአክብሮነቱን ሂደት ያውከዋል፡፡ ምክንያቱም የልዩነት ነጥብ በአስር ይባዛና በማጉያ መመልከቻ ደምቅና ግዙፍ ይሆናል፡፡ የአንድን የአክብሮነት ሜዳውን ዳግምበአስር ይከፍልና በጣም ትንሽ ብናኝ ይሆናል፡ ፡ ስለዚህም በለውጥ ሀዋሪያት ዱአቶች መሀከል የአንድነት የአብሮነት ሜዳው ሰፊና ግዙፍ መሆኑን በርግጠኝነትና በልበ ሙሉዕነት መግለፅ እንችላለን፡፡ ሁሉም ሊያውቁት ሊገነዘቡትና ሊደሰቱበት እንዲሁም ህዋወታቸውን ችሎታቸውን ሊሰዉለት የሚገባ ነጥብ እንዳለ ሊያምኑበት ግድ ይላቸዋል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የዳዕዋ ሰዎች የዚህ እምነት አንፀባራቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ትዕግስት ፅናትና ብርታትን በከፍተኛ ደረጃ ይጠይቃል፡፡

## 31) የሚስጥራዊ እንቅስቃሴ አደገኝነት

ልዋጭ ትርጉም ካላቸው ፣ ከሚስጥራዊነት ድብቅነትን በከፍተኛ ደረጃ እንቃወማለን፡፡ ኢስላም ሙሉዕና ግልፅ ዲን ነው፡፡ ሁሉም መነሻዎቹና አስተሳሰቦቹ ግልፅ ናቸው፡፡ ኢስላም ውስጥ ሚስጥር የለም ጭማሪም የለም፡፡ የዐቂዳ ይፋነት የኢስላም የጥንካሬው ምንጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው የሚያምንበትን አጀንዳ በልበ ሙሉዕነት ግልፅ ያደርጋል፡፡ ልጆች ግልፅና ለመረዳት የሚያስቸግሩ ቀጥተኛ ነገሮችን በተፈጥሮአቸው የመረዳት ባህሪ አላቸው፡፡ በተፈጥሮአቸው ድንግዝግዝ ያለ ድብቅ ገዳዳ ነገሮችን ይጠላሉ፡፡ የሚስጥራዊነት ስህተቶች ጠላቶችን ከመጉዳቱ በላይ ባለቤቶቹን በከፍተኛ ሆኔታ ያጠቃሉ ፡፡ ድብቅነት ስህተቶች በአደገኛ ሁኔታ እንፍለፍሉ እድል ይሰጣል፡፡ ያለ አቅሙ መስራት የሚሞክር ሰው መንገድም አይቆርጥም ወገቡም አይተርፍም፡፡ ምክንያቱም ጨለማ ውስጥ ስለሆነ አያይም የማይታይን ድብቅ ነገር ከማደጉና ከመጎልበቱ በፊት ማስተካከልና ማረም ያዳግታል፡፡ በይፋ እንቅስቃሴ ውስጥ ድክመቶችን ማረምና ማቃናት ብዙም አይከብድም በብርሀን ላይ ስለሆነ፡፡

## 32) የአመለካከት አንድነት

በኢስላም የዳእዋ ሰዎች ካሉ የልዩነት ምክንያቶች ውስጥ ትንሽ እንኳ የጋራ የሚያደርጋቸው የአስተሳሰብ አንድነት በመካከላቸው አለመኖሩ ነው፡፡ ይህም ጉዳይ በእነርሱ መሀከል የአላማ የስልት የቅደም ተከተል ልዩነቶች እንዲበዙ አድርጓል፡፡ እያደረገም ይገኛል፡፡ ከዚህም ባለፈ ጥላቻና ቂም መትከል ጀምሯል፡፡ ስለዚህም የአመለካከት መቀራረብና አንድነት በአጠቃላይ ሁኔታ በዳእዋ ሰዎች መሀከል በተለየ ሁናቴ በወጣቶች መሀከል እንዲኖር የማያቋርጥ ትግል ያስፈልጋል፡፡ ይህም እንዲሆን

የሸሪአን የእውቀት አድማስ በቁርአንና በሱንና ላይ ተንተርሰን ማስገንዘብ የሚዘናዊነትን የመተጋገዝን ይቅርታ የመለዋወጥና የወንድማማችነትን የፍትሀዊነትን ሀሳቦች ማስረፅ ያስፈልጋል፡፡ የቅድመ ሁኔታዎችን አስፈላጊነት ምክንያታዊነትም ማስረዳት የውይይት ክህሎትን ማሰልጠን ልዩነት የማስተናገድ ጥበብን ማመላከት፣ የኢስላም ሁለንተናዊነትን እና የሸሪአን ዘላለማዊነትና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ለሰው ልጅ በየትኛውም ጊዜና ቦታ መተዳደሪያ መሆኑን ማስገንዘብ፣ ይህን ሂደት ውጤታማ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ፣ ከዚህ አላማ ጋር የሚጣጣሙ ፅሁፎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ መምረጥ፣ የዳእዋ ሰዎችና ወጣቶች እንዲያነቡ ማድረግ፣ በተለያዩ ጊዜያቶች መገምገምና መልሶ ማየት ፣ የተለያዩ ትምህርት መስጫ መፅሀፍቶችና ካሪኩለሞች እንዲገመገሙ ከዘመን ጋር እንዲራመዱ እንዲጎለብቱ ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ባለ ሙያዎች እንደሚሰሩ ሁሉ ዕነዚህም የዳእዋ መፅሀፍቶች ሊታዩና ሊገመገሙ ይገባል፡፡

## 33)<u>አክብሮት እንጂ ቅዱስነት የለም</u>

አንድ የሙስሊም የዳዕዋ መሪውን የትምህርት አባቱን የመስጂዱን ኢማም መውደድ ማክበሩ ተፈጥሮአዊ የሚደገፍና የሚፈለግ ነገር ነው፡፡ ግና ይህ ፍቅር ድንበሩን ሊያልፍ አይገባውም፡፡ የቀደምት ነብያት ተከታዮችና ሀይማኖት አማኞች ከእምነት ያወጣቸውና ወደ ሽርክ ያስገባቸው ነብያቶቻቸውንና ደጋጎቻቸውን ወልዮቻቸውን ከአላህ በላይ ለነሱ ታዛዥና አፍቃሪ መሆናቸው ነው፡፡ ለአደጋ ያጋለጣቸው፡፡
በሙስሊሞች መሀከል ከተስፋፉና ከተሰራጩ ነቀርሳ በሽታዎች ውስጥም ይኸው የተራው ህዝብ የዳእዋ ሰዎችና መሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ልክ ያጣ ትስስር ነው፡፡ መሪዎቻቸውን የሀቅና የስህተት መለያ መለኪያ አድርገዋቸዋል፡፡ መሪዎቻቸውን ፍፁም አድርገዋቸዋል፡፡ ይህንን መሰረት

ዘንግተዋል “ሰዎችን በሀቅ እንለካቸዋለን ሀቅን ግን በሰው አንለካውም። ” ይህ ልክ ያጣ “የመሪዎች” ፍቅር በሙስሊሞች መሀከል ልዩነትን ለማምጣት ትልቅ ስተዋፅኦ አለው። አሁንም ቀጥሏል። ዳእዋ መስመር ውስጥ በገቡ ሰዎች መሀከል ቂምና ጥላቻ ፈጥሯል። መፍትሄው ሰዎች መሪዎቻቸውን በልኩ ሊያፈቅሩ እነርሱ ሰዎች መሆናቸውን እንያምኑ ሊሳሳቱም ትክክል ሊሆኑም እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። ለነርሱ የሚኖር ፍቅርና አክብሮት በያዙት ሀቅ ልክና ባስመዘገቡት ውጤት መጠን ሊሆን ይገባዋል። ሙስሊም ሀቅን አሳዳጅ ፈላጊ ነው መሪዎችንና አስተሳሰባቸው ወደ ሀቅ ሚያደርስ ድልድይ ነው። ድልድዩ ይሰበራል ሀቅና ትክክለኛ አስተሳሰብ ግን ዘላቂ ነው።

## 34)<u>ሌሎች ካቆሙበት መጀመር</u>

የስራ ልምድን መቅሰምና የተጀመረን ነገር ላይ ማከል እንዲጎለብት እንመክራለን። ተቋም ወይም ማእከል አልያም ትምህርት ቤት ወይም የዳእዋ ስራ ከአልቦ ሊጀምር አይገባም። እርሱ የአላህ ዲን ለማገልገል እራሱን የሰዋ የመጀመሪ ያ ሰው አይደለም። ለዚህ ክብርና ተወዳዳሪ ለሌለው አላማ እራሱን የሚሰዋ የመጨረሻ ሰውም አይሆንም።

## 35)<u>ደረጃን ያማከለ እድገት</u>

ድንገተኛ ለውጥን ሳይሆን ደረጃን የጠበቀ እድገት እንዲመጣ እንጥራለን። በእቅድ ላይ የተመሰረተ ልማትን እንጂ ያጋጣሚ እድገትን ፣ ግብዝነትን ሳይሆን ጥበብን ችኮላን ሳይሆን ስክነትን የተረጋጋና ዘላቂ ስራን ከችኩልና ቶሎ ከሚረግፍ ስራ አናስቀድምም። በተከበረው የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲስ እንዲህ ተብሏል። በሌላ ሀዲስ « አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው ስራ

ብዙም ባይሆን ዘውታሪ የሆነው ነው፡፡» በሌላ ሀዲስ የዲን ትዛዞችን ከአቅም በላይ ለመፈፀም የሚሞክር ዲኑ ለረጅም ጊዜ መቀጠል አይችልም፡፡»

ስለዚህም ውድ የሆነን ምምክርና ጥበብ ማስታወሱ ይጠቅመናል «ጊዜ እራሱ የመፍትሄ አካል ነው፡፡»

## 36) አላማዎችን በተለያየ ሰአት ማከፋፈል

አላማዎችን በተለያዩ እርከኖች መከፋፈል እንዳለብን እናምናለን፡፡ ማለትም አላማዎችን ከልብ ለማድረስ እንዲያስችሉ የሚያሥፈልጉ እርከኖችንና ደረጃዎችን መግለፅ፡፡ ተቀዳሚው ለተከታዩ አመቻችቶ ያልፋል፡፡ ሁለተኛው በመጀመሪያው ላይ ይቀጥላል፡፡ የምናስቀምጣቸው ግቦች በእኛ አቅም ስር ያሉና አጠቃላይ ከሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ ሊሆኑይገባል፡፡

## 37)የተቀናጁ የኢጅቲሀድ ተቋማት

ከምራችን እናምናለን፡፡ በተደጋጋሚም እናረጋግጣለን፡፡ ኢስላም ለሁሉም ዘመን እና ቦታ መፍትሄ ያለው ዲን ነው፡፡ መጤ የሆኑ ችግሮችን የመፍታት አቅም አለው፡፡ ለኢስላም ሊቃውንት ለፊቂህ ጠቢቦች የምናቀርበው ጥሪ አለ፡፡ ይህም ኢስላም ያሥቀመጣቸውን መፍትሄዎች ለህዝቡ ማቅረብ መቻል አለባቸው፡፡ የተቀናጀ የኢጅቲሀድ ተቋሞች መኖራቸው ይሁን ይበል የሚያስብል ጉዞ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የኢስላም ጥናትና ምርምር ተቋም ግብፅ፣የኢስላማዊ ፊቂህ ተቋም የአለም አቀፍ ኢስላማዊ ጥምረት ስር የኢስላማዊ ፊቂህ ተቋም በካርቱም የፊቂህ የፈትዋና እርምጃ ነው የአውሮፓ የፍትህ የምርምር ምክር ቤት የሰሜን

አሜሪካ የኢስላማዊ ፍትህ ም/ቤት፡፡ አለም-አቀፍ የሙስሊም ሊቃውንት አንድነትና  ድርጅት (ሀገር አቀፍ የኢስላም ተቋሞች) ሌሎችም እነዚህ ድርጅቶች መመስረታቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በህብረትና በመተባበር የሚሰሩበትን ጊዜ እንናፍቃለን፡፡ የእነርሱ መተሳሰርና መረዳዳት ፋይዳውን የላቀ ያደርገዋል፡፡ እንደዚሁም እነዚህ ተቋሞች ቴክኒካዊ የሆኑ ስራዎቻቸውን ለባለሙያዎችና ከፍተኛ ልምድ ባካበቱ ባለ ድረሻ አካላት ቢሰጡ የእነርሱን ተቀባይነት ከፍ ያደርገዋል፡፡ ቅልጥፍናና ውጤታማነቱንም የተሸለ እርከን ላይ ያደርሰዋል፡፡

## 38)<u>አንድ የሙስሊሞች ቡድን</u>

ማንኛውም ቡድን (ጀመአ) ወይም ፓርቲ ወይም የዳእዋ እንቅስቃሴዎች ቡድኖች ውስጥ አንዱ ቡድን ነው፡፡ ብቸኛ የሙስሊሞች እንቅስቃሴ አይደለም፡፡ የቡድኑ ወይም የፓርቲው ዋጋ እና በላጭነት በአስተሳሰቡ ትክክለኛነትና በተግባር ሜዳ ላይ ያለው ስኬትና አፈፃፀም የሚወስነው ይሆናል፡፡

## 39)<u>ጠቅላይ የሆነ ፍረጃ አደገኝነት</u>

በዳእዋ ዘርፍ የተሰማሩ ወገኖች ዘንድ ጠቅላይ እና ጎጂ ገለፃዎችና ፍጃዎች ተባዝተዋል፡፡ ለምሳሌ ሙስሊም ያልሆኑ ሀይሎችን አንድ የሚያደርገው ነጥብ ኢስላምን መዋጋት ብቻ ነው፡፡ የሁዳዎች የአለም ገዢዎች ናቸው፡፡ ሁሉም ነገር በቁጥጥራቸው ስር እንደሆነ የሚያሳይ ሪፖርት ተገኝቷል፡፡ ሁሉም በግልፅና ህጋዊ ሰውነት ያለው ኢስላማዊ ስራ ሴራ ያለው፣ ማታለያና መጨፍለቂያ ነው፡፡ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ህዝባዊ ኢስላማዊ እንቅስቃሴ ፍፁም የሆነ መልካም ስህተት የማይደርስበት

ሙሉእ ነው፡፡ አንድ ቡድን (ጀመአ) የሚሰራበት ጊዜ የሙስሊሙ ኡማ ከፍና ዝቅ ይላል፡፡ ሌላው ቡድን የሚሰራበት ጊዜ ዝቅና ክንብል፡፡ ይላል አልያም ሌላው ጀመአ እስከ መጨረሻው ፍፁምና የተሳካለት ነው፡፡ በአንፃሩ ሌላኛው የውድቀት መንስኤ ነው፡፡ የሚሉ ሚዛናዊነት ፍትሀዊነት የጎደላቸው አስተያየቶች ይሰጣሉ፡፡

ይህ ትንታኔ ምክንያታዊነት ያላማከለ ግልብና ስሜታዊ ድምዳሜ ነው፡፡ ለወቀሳና ከንቱ ፍረጃዎች ለማድረግ የቸኮለ አስተያየት ነው፡፡ ሀሳቡን የሚያራምዱ ሰዎች መፍትሄና የስራ ፕሮጀክት ከማቅረብ የሚገላግላቸው ነጥብ ነው፡፡ እነርሱ ለመረጡት የስንፍናና የጨለምተኝነት ጉዞ በቂ ምክንያት የሚያላብስሀሳብ ነው፡፡ ይህ በእነርሱ እይታ ወይም ብዥታ ከባድ የሆነ የማይነቃነቅ የበሽታ ማዕበል አለ፡፡ ስለዚህም የማይረቡ ትንታኔዎችን በማቅረብ እጃቸውን አጣምረው በቀቢፀ ተስፋ መኖርን መርጠዋል፡፡ እነዚህ አመለካከቶች በመሰረቱ የአላህን (ሱ.ወ) ሱነተ ተዳፋዕ አንዱ ሌላውን የማቆምና የመታገል ብሎም የመርታትን የምድር ህግ ይፃረራል፡፡

ሙስሊም ጎጂና ከንቱ ከሆኑ አጠቃላይ ፍረጃዎች መጠበቅ አለበት፡፡ የአእምሮው የማሰብ አቅም ተበርትቶ ውስጣዊ ወኔውን አነሳስቶ ፣ ነገሮችን በአግባቡና በትክክል ተረድቶ በሚገባውና በትክክለኛ ስፍራ ማስቀመጥ መቻል አለበት፡፡ የነገሮችን መነሻና መድረሻ case &effect ምክንያትና ውጤት አመክሮአዊነትና ማጤንና መረዳት አለበት፡፡ ሚዛናዊ ትንተናና መፍትሄዎች ማቅረብ መቻል አለበት፡፡

የብዥታና የስጋት ምርኮኛ መሆን የለበትም፡፡ ጥቁር ወይም ነጭ መላኢካ ወይም ሸይጣን ቀላል አልያም በፍፁም የማይቻል በጣም ማክበድ ወይም ማጣጣል ከነዚህ የተለዩ አማራጮችን መኖራቸውን ማስረገጥ ይገባል፡፡

## 40) <u>የሰው ልጅ ሀላፊነት</u>

አላህ(ሱ.ወ) ዲኑን እንደሚጠብቀውና እንደሚንከባከበው ገልጿል ፡፡ ግና (እርሱ ለሚያውቀው ምክንያት) ይህንን ከባድ ሀላፊነት እንዲወጡ ሙስሊሞችን አዘዘ፡፡ ይህ ዲን ግልፅ ያለ እውነት ቢሆንም የአላህ ውሳኔ የማይቀር ከመሆኑ ጋር ከሰው ልጅ የሚጠበቁ ሀላፊነቶጭ አሉ፡፡ ነብያቶች ሀዋርያዎቻቸው ሰሀቦቻቸውና የነርሱን መንገድ የተከተሉ ይህንየከፈሏቸውን ዲን ከግብ ለማድረስ ታላላቅ መስዋዕትነቶች ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እኛም የነርሱን ፈለግ እንከተላለን፡፡ በተጓዙበት መንገድ እንጓዛለን፡፡

## 41) <u>መልካም አርአያ</u>

የዳዕዋ ሰዎች ሊያውቋቸው ግድ ከሚሉ ዋና ዋና ነገሮችና የስኬት ሚስጥር አብዩ የዳእዋ መስሪያ መልካም ተምሳሌት ነው፡፡ የኢስላም የለውጥ አብሳሪዎች በተለያዩ መንገዶችና ስልቶች ኢስላምን አስፋፍተዋል፡፡ ዋናው ስልት ግን ተምሳሌትነት አርአያነት ነው፡፡ ከዳእዋ ሰዎች የሚጠበቀው ዋና ነገር ለሰዎች ለሚጠሯቸው ወገኖች አርአያና ተምሳሌት መሆን ነው፡፡

## 42)<u>የመግቢያ ኮዶች</u>

የኛ ብቻ የሆኑ መገለጫዎችና ቃላቶች እንዲኖሩን መጣር አለብን፡፡ እነዚህ መገለጫዎችና ቃላቶች ግልፅና እራሳቸውን የቻሉ ሊሆን ይገባቸዋል፡፡ በጥበብና በትኩረት ልንመርጣቸው ይገባል፡፡ በተለያዩ ጊዜያቶች ብቅና ጥልቅ የሚሉ ያአስተሳሰብ ማዕበሎችን ከማራገብና በእነርሱ ከመዋጥ ልንታቀብ ይገባል፡፡ ሶሻሊዝም በሚገንበትና በሚጮህበት ጊዜ ኢስላም

ሶሻሊዝም ነው፡፡ ካፒታሊዝም ሲነግስ ኢስላም ካፒታሊዝም ነው፡፡ የዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ በሚለፈፍበት ወቅት ኢስላም ዲሞክራሲ ነው፡፡ ከማለት ልንታቀብና ኢስላምን እንደ ሸቀጥ ከማራገብ ልንርቅ ግድ ይለናል፡ ኢስላም ሁሌም እራሱን በራሱ መለኪያዎች በቋሚ መገለጫዎቹ በመነሻዎቹና በመድረሻዎቹ ልንገልጸው ይገባል፡፡ የኢስላም ከፊል ባህሪው ከሌሎች ፅንሰ ሀሳቦችና እይታዎች ጋር ቢገጣጠም የኢስላምን ምሉዕነትና ጠቅላይነትን ነው የሚያሳየው እንጂ የተወሰኑ ፅንሰ ሀሳቦች ከኢስላም ጋር መገጣጠም ኢስላምን ከዚህ ወይ ከዚያ አስተሳሰብና ፍልስፍና ልንገልፀው ይገባል ማለት አይደለም፡፡

ምክንያቱም ኢስላም መሰረታዊ ነው፡፡ ሌላው ቅርንጫፍ ነው፡፡ ኢስላም ቋሚና የማይለወጥ ነው፡፡ ሌላው ተቀያያሪ ነው፡፡ ኢስላም ፍፁም ትክክል ነው፡፡ ሌላው አስተሳሰብና ፍልስፍና በየደረጃው ከእውነት ጋር ያለው ቅርርብ ይራራቃልም ይቀራረባልም፡፡

## 43)<u>ግልፅ ፅሁፎች (ድርሳናት)</u>

የዳዕዋ ፅሁፎቻችን ግልፅና የታሰበበት የተቀመረ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አንድ ትርጉምና ተልዕኮን የያዘ መሆን አለበት ከፀሀፊው ወደ አንባቢው በግልፅ የሚተላለፍ ሁለት ሰዎች ዘንድ አንድ ትርጉምን የሚያሥጨብጥ ሊሆን ይገባዋል ይህም ሁለት ዋና ዋና ጥቅሞችን ያመጣል፡፡

1- የዳዕዋ ስራ ላይ ያሉ ሰዎች ዘንድ ተመሳሳይ የአስተሳሰብ የአመለካከት የባህሪና የስብዕና መልክ ይፈጥራል፡፡
2- የዳዕዋ ስራ ላይ ያሉ ሰዎችን በተለይም ጀማሪዎች ዘንድ የአስተሳሰብ መረበሽና መናጋት እንዳኖር ያግዳል፡፡ የተሳሳቱ ትረጓሜዎችና ማብራሪያዎች እንዳይሰጡ ይከለክላል፡፡ ግልፅነት የጎደለው የተንጋደደ ፅሁፍ የተለያየ ግንዛቤን ይፈጥርና ውጤቱም

እርስ በእርስ የሚጋጭ ይሆናል፡፡ ድክመት ወይም ፅንፈኝነት ይኖርበታል፡፡ ግጭትና ፅንፈኝነት እንዲያባብስ ያደርጋል፡፡

## 44)<u>የሌሎችን ልፋት ቦታ መስጠትና መቀበል</u>

የእኛ መነሻዎችና መሰረቶች የግል ሀብቶቻችን አይደሉም፡፡ እኛ የመነሻዎቻችንና የመሰረቶቻችን የመርሆቻችን ታዛዦች ነን፡፡ መርሆቻችንና መሰረቶቻችን ላይ ተመስርተው ለሚሰሩ ሰዎች ውስጣችን ሊረበሽና ሊታወክ አይገባውም፡፡ ምንም እንኳ የተለየ አካሄድና የተለየ ውጤት ለማስገንዘብ ቢሞክሩ ውስጣችን ሊታወክ አይገባም፡፡ እንዲሁም በዚህ ልንደሰትና ልንረካ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የእነርሱ ጥረት የኛ ትጋት የዳዕዋ ግልጋሎት በመስጠት መንገድ ላይ ይገጣጠማል ፡፡ ልንወዳቸውንና ጥረታቸውንና ትጋታቸውን ዋጋ ልንሰጠው ይገባል፡፡ የሚቻለውን ያህል ልናግዛቸውም ይገባል፡፡ በዳዕዋ ቆይታ ላይ የምናያቸውን የግል ወይም የቡድን መልካምና ስኬቶች ትንስም ቢሆን ወስደን ልንማርባቸውና ልንጠቀምባቸው ምንም እንኳ የተወሰነ ስህተት ቢኖርባቸው እንኳ መጠቀም መቻል አለብን፡፡

## 45)<u>መጥምር ማንነቶች</u>

የዳዕዋ ሰዎች አገርን ለመጠበቅና ለማገልገል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ የአገርን ደህንነት፣ምርት፣ አካባቢያዊ የአየርና የኢኮኖሚ ፣ የመጪውን ትውልድ የወደ ፊት አቅጣጫ በተመለከተ ለአገሩ ሊሰራ ይገባል፡፡ ይህም ተፈጥሮአዊ የሆነውን የዘገር የህዝብ ማንነትና በምርጫ ላይ የተመሰረተውን ዲንን የዲን መርሆች ግንኙነቶች የመደጋገፍና የመዋሀድ እንጂ የመጋጨትና የመቃረን ባህሪ ሊኖራቸው አይገባም፡፡

## 46) ትክክለኛነት የኛ ብቻ ነው አይባልም

እኛ በግልፅና በተደጋጋም በቁርጥ የምንገልፀው ትክክለኛነት የኛ ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ ሌሎችንም የምናስበው ሀቅ የኛ ብቻ ነው ከሚል ብዥታ  እንዲወጡ እንመክራለን፡፡ እኛ አላማችንን ስልታችንን ጥሩ ነው የሚል ግንዛቤ አለን ግና ፍፁም ነው አንልም፡፡ ያለብንን ስህተትና ድክመት ለሚያሳየን ወገንን ደስታችንና ምስጋናችን የላቀ ነው፡፡
በተጨማሪም እኛ የሌሎችን የአላማና የስልት ምርጫዎች እናከብራለን፡፡ ከእኛው ከሁላችንም የሚጠበቀው ነገር ንያችንን ለአላህ(ሰ.ወ) ንፁህ ማድረግ ነው፡፡ ትክክለኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ መጣር፣ ለለውጥና ለእድሳት በልበ ሙሉዕነት መነሳት ስህተት ከፈፀምን ስህተትን በግልፅ መቀበል ሌሎች ዘንድ ትክክለኛነትና ስኬት ከመጣ በሙሉነት ልንደሰት ይገባል፡፡ ይህም ከሚያመጣው መልካም ነገር ውስጥ የልምድ ልውውጥ ማድረግ ፣ ይህም የዳዕዋ ሰውንና ተቋምን በመረጃ ለማጎልበት አይነተኛ መንገድ ነው ፡፡ ይህም ተቋሙንም ሆነ ግለሰቡን ከሌሎች የመማርና ለሌሎች የማካፈልን ክህሎት ያዳብራል፡፡ ማንም ሰው ከምክርና ከትችት በላይ የሚሆን የለም፡፡ አልያም እርሱ ፍፁምነትን ጠቅልሎ ይዞ ሌሎች ስህተትን ተከናንበው ሊኖሩ በፍፁም አይችሉም፡፡

## 47)ልክ ያጣ ወገንተኝነት

የተለመደ እና ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ አንድ የዳዕዋ ሰው የመረጠውንና የሚጓዝበትን የዳዕዋ አቅጣጫ ከሌሎች በተለየ ሊወድና ሊያስበልጥ ይችላል፡፡ ምክንያቱም እርሱ የመረጠው የዳእዋ መስመር በእርሱ ሚዛን ከሌሎች የሚሻሉባቸው ነጥቦች ስላሉት ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሰው እርሱ

የመረጠውን የዳእዋ መስመር ፍፁምና ሙሉዕ ነው ሊል አይገባም፡፡ ሌሎች የዳእዋ መስመሮች ላይ ግፍ ሊሰራ አይገባም፡፡ይህ የሚያስኬድና የሚፈቀድ በኢስላም ተቃውሞ የማይቀርብበት መሆኑ ሚዛናዊ ወገንተኝነት ነው፡፡

ይህንን አካሄድ ከለቀቀ የተከለከለ ወገንተኝነት ውስጥ ገብቷል፡፡ ይህም ኢስላም ጨለማ አለም ውስጥ ይከተዋል፡፡ ጃሂሊያ ( አስከፊ መሀይምነትና አውሬነት) ነው፡፡ በማለት ወደ ገለፀው ሁሌም ልንረሳው የማይገባው ነገር የመበላለጫው የሻለ የመሆኛው ሚዛን አላህን መፍራትና መልካም ስራ መሆንን መዘንጋት የለብንም፡፡

የዚሁ አካልና መሰረታዊው ነጥብ ከጃሂሊያ ወገንተኝነት ፅንፈኝነን መራቅ ግድ ይላል፡፡ ከየትኛውም አይነት የአገር የጎሳ የፓርቲ አልያም የቡድን ፅንፈኝነትና ወገንተኝነት መራቅ ግድ ነው፡፡

## 48) የቅደም ተከተል ምክንያታዊነት

የቅደም ተከተል ምክንያታዊነትን አስፈላጊነትና አይቀሬነትን ልንገልፅ እንወዳለን፡፡ ወደ እርሱም እንጠራራለን፡፡ የኢስላም መርሆች ሁሉም እኩል አይደሉም፡፡ ለምሳሌ የኢማንና የተውሂድ ደረጃ መንገድ ላይ ሰውን የሚያደናቅፍና የሚያውክን ነገር ከማስወገድ ጋር እኩል አይደለም፡፡ የዳዕዋ ነጥቦችና አጀንዳዎችም እንደዚሁ እኩል ደረጃ ላይ አይደሉም ፡፡ ስለዚህም የቅደም ተከተልን ጉዳይ በደንብ ልንረዳ ይገባል፡፡ ሁሉንም ጉዳዮች በየ ቦታቸው ማስናገድ አለብን፡፡ በተቸማሪም የቅደም ተከተል ደረጃዎችንም በየጊዜው እንደየአስፈላጊነቱ መገምገምና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የቅደም ተከተል መዳረሻዎቹ በኢስላም ቋሚ ነጥቦች ናቸው፡፡ ግና በዳዕዋ ስራ ላይ እና በህብረተሰብ ግንባታ ሂደት ላይ እንደየ ቦታውና ጊዜው እንዲሁም እንደየ ማህበረሰቡ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

ከቅደም ተከተል ጋር ከሚያያዙ ነጥቦች ውስጥ አደጋና ችግር በሚከሰት ጊዜ የተከሰቱ ችግሮችን የምናመዛዝንበትና የምንለካበት ክህሎት ማደበር ያስፈልጋል፡፡ እድሎችና ሁኔታዎች በሚመቻቹበት ጊዜ ጥቅሞችን ማወዳደርና መለካት መቻል ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኘውን መምረጥ መቻልም ይገኝበታል፡፡

## 49) <u>የሸሪአን አላማና ግብ መረዳት</u>

የዳዕዋ ሰዎች በትክክል አላማና ግብ መገንዘብ እንዲሁም በዘርፉ ጥቅል እውቀት ማዳበር አለባቸው፡፡የቁርአንና የሱንናን ግርድፍ መልዕክት ይዘው የሸሪአን አላማና ግብ ሚስጥርና ጥበብ ሳይረዱ ዳር ላይ ሊቆሙ አይገባም፡ ፡

ይህ ማለት ግን የቁርአንና የሱናን ደረጃ ዝቅ ማድረግ አይደለም፡፡ እነሰውም በተሸለ መልኩ የሸሪአን አንኳር መንፈስና መልእክት መረዳት ነው፡፡ የሸሪአ የአንድነት መስመሮችንና የልነት አጀንዳዎችን ማመዛዘን መቻል፤ የሸሪአን ዝርዝርና ቅርንጫፍ ትዕዛዞች ከአጠቃላይ የሸሪአ ብርሀንና መልዕክት አንፃር መገምገም የሸሪአን መልእክቶች በዚህ መሰረት ላይ ተንተርሶ መመልከት፡- "አልኢብረቱ ቢልመቃሲድ ወልመአኒ ላ ቢልአልፍዚ ወልመባኒ" "ቁም ነገሩ ያለው በሸሪአ ግብና አላማ እንጂ በቃላትና በግርድፍ መልዕክቱ ላይ አይደለም፡፡" ይህንኑ የሚመስል መልዕክት አለ፡፡ "አልዑሙሩ ቢመቃሲዲሀ" "ነገራት የሚለኩት በአለማቸው ነው"

በግልፅ እንደሚታወቀው ይህ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሊቃውንት ጀሮአችንን ልናውሳቸው ይገባል፡፡

## 50)<u>ውሳኔዎች የሚኅትቱትን ውጤት ማጤን</u>

የዳእዋ ሰዎች የፊቅህን ባህሪና ተግባር ግብና ውጤት መረዳት አለባቸው፡፡ ማለትም በነርሱ ውሳኔ ላይ ተመስርቶ የሚመጡ ነገሮችን መረዳት አለባቸው፡፡ ይህ እውቀት የአላህን (ሱ.ወ) የዚህ ምድር ህግጋት ጠንቅቆ ማወቅ አይቀርም ፡፡ አገራዊ አህጉራዊ አለማቀፋዊ ሁኔታዎችን በሰፊውና በጥልቀት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም የትኛውንም ውሳኔ ከመወሰናቸው በፊት ውሳኔው የሚያመጣውን የሚኅትተውን ውጤት ማጤን አለባቸው፡፡ በእርሱ እና በእነርሱ ዙሪያ የሚያመጣውን ጣጣም ሆነ ትርፍ ማስላት ይገባቸዋል፡፡
ስሌቱን ሲቀምሩና ሲፈትሹ በጥርጣሬና በምናብ በመላምት ላይ ተመስርተው ሳይሆን ፤ በተጨባጭ መለኪያዎች ሊለኩ በችኮላና በፍጥነት ሳይሆን በስክነትና በእርጋታ፣ በግልፍተኝነት ሳይሆን በአቅም ላይ ተመስርተው ፤ ሊወሰኑ ይገባል፡፡ ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ታሪክ እንደታየው በችኩልነትና በግብታዊነት የተወሰኑ ውሳኔዎች አሉ፡፡ ውሳኔውን ያስተላለፉት ሰዎች መልካምና የተሻለ ነገር አስበው መጥፎና አደጋን ለመመከት ብለው ቢሆንም የውሳኔቸው ውጤት ግን ከፍተኛ አደጋና ደም አፍሳሽ ብዙ ተከታታይ መከራዎችን ኅታች ሁነዋል፡፡

## 51) <u>ተጨባጭ አለምን ማገናዘብ</u>

የዳዕዋ ሰዎች ተጨባጭን የሚኖሩበትን ከባቢ ሊያጤኑ ይገባል፡፡ ከተጨባጭ አለም ጋር የሚተሳሰሩ ሁኔታዎችን ከፊትና
ከኋላቸው ያመቁትን አደጋ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ሊያደርስበት የሚታለመው ግብና ግቡን ለመምታት ያለን አቅምና

ችሎታ መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ይህም የዳዕዋ ሰዎች የሚናግፆቸው እሴቶች አላማዎችና እቅዶች በተግባራዊ አለም ሊፈፅሙ የሚ
ችሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡(የዳዕዋ ሰዎች ከውጤቶች ጋር የተያያዙ እውቀቶችን ማወቅ አለባቸው፡፡የቀረፁት ስራ ሰዎችንም ግልፅና የታሰበበት ፕሮግራምን በማቅረብ በራስ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስሜታቸውንና አስተሳሰባቸውንም ይገዛል፡፡ ይህም መሰረታዊ ለሆኑ ነገሮች ቅድሚያ በመስጠት ሁሉንም በየደረጃው ለማስተናገድ ይረዳል፡፡

## 52)<u>ሌሎችን ስለ አደጋ ማንቃት</u>

ሙስሊሞች ሁሌም አደጋ ያንጃብብባቸዋል፡፡ ምክንያቱም የኢስላም ተልዕኮ ሁለንተናዊው የሰው ልጅ ህይወት ስለሚዳስስ ነው፡፡ ስለዚህ ጠላቶች አደጋ ለማድረስና ለማጥቃት ተግተው ይሰራሉ፡፡ ምክንያቱም ብዙዎች እውነትን ይጠላሉ፡፡ ይዋጋሉ፡፡ የኢስላም ተከታዮች ዘንድ ይህንን ግንዛቤ ልናዳብርና ልናሳውቅ ይገባል፡፡
ይህ ያንጃበበ አደጋን ማወቅ እርስ በእርስ የሚደረግ ሽኩቻ አርቆ የአንድነት መስመር ላይ እንዲሳተፍ ያደርጋቸዋል፡፡ ምክንያቱም የሙስሊሞች የተልዕኮና የዳዕዋ ዑማ ስለሆኑ ፡፡ሁሉም በአንድነት የዚህ አደጋ አላማ ናቸው፡፡ ይህንን አደጋ አለመገንዘብ ሁሌም ሀይልን በእርስ በእርስ ግጭት እንዲጨርስ ያደርጋል፡፡

አደጋዎቹ ሁለት አይነት ናቸው፡፡

1. ከውጭ የሚመጣ አደጋ
2. ከውስጥ የሚመጣ አደጋ፡፡ በጣም ከባድና አውዳሚው ነው፡፡ ከታሪክ እንደተቀሰመው ትምህርት እነዚህ አደጋዎች ብዙ ጣጣ አላቸው፡፡

## 53)ኢስላማዊ ወንድማማችነት

ኢስላማዊ ወንድማማችን በኢስላም ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ የዳዕዋ ስራ ዋና ምሶሶ ነው፡፡ ወንድማማችነት መስፋፋቱና መብዛቱ አላህን ያስወድዳል ምድር ላይም ድል ያጎናፅፋል፡፡ ወንድማማችነት አለመኖር ከአላህ ያጣላል፡፡ ለውድቀት አደጋ ይዳርጋል  የዳዕዋ ሰዎች ኢስላማዊ ወንድማማችነት እንዲጠናከር ምክሮችንና ማስታወሻዎችን ሊዘክሩ በተግባርም በህይወታቸው ሊያውሉት ይገባል፡፡ ወንድማማችነት ከሚያፈርሱ ነገሮች ሊሸሹም ይገባል፡፡ ወንድማማችነትን መፍጠርና ግንኙነትን ማጠናከር የኢማንን ግለት የሚጨምር የአላህን እዝነት እገዛና እርዳታ የሚያመጣ ተግባር ነው፡፡  ስኬትን ጅምር የሚጠቁም ማስረጃም ነው፡፡ወንድማማችነት አለመኖሩ የዚህን ተቃራኒ ውጤት ያመጣል፡፡ ቅያሜን የስሜት መቆሸሽን አድሎአዊነትን፣ ራስ ወዳድነትን ይወልዳል የውርደትና የሽንፈት  መቃረብን የሚጠቁሙ ደውል ነው፡፡

## 54)ዳእዋ የጋራ ሀላፊነት ነው

ወደ ኢስላም የሚደረግ ጥሪ የሁሉም ግዴታ ነው፡፡ የሸሪአ ጥናት የወሰዱን የሀይማኖት አዋቂዎች ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ምንም እንኳ የሸሪአ ተማሪዎች ላይ ያለው ሀላፊነት በአንፃሩ ከሌሎች የበለጠና የጎላ ቢሆንም ፡ ፡ ልንረሳው የማይገባ ሁሌም ልናስታውሰው ግድ የሚለን ነጥብ ቢሆን ኢስላም ሁሉንም የሚጠቀልል የሚያስተናግድ ሀይማኖት ነው፡፡ ጀግንውን ፈሪውን ንፉጉን ቸሩን ንቁውን ገዛዛውን ፤ ሆኖም ግን የዳዕዋ ተልእኮ ታላቅነት አስፈላጊነትና አሳሳቢነት ታላላቅና ፅኑ ሰዎችን ይፈልጋል፡፡ትህትና ያላቸው ቸሮች ጀግኖችና ትእግስተኞችን ቆራጥና ጠንካሮች ፍትሀዊና የራሳቸውን ጥቅም ለሌሎች አሳልፈው የሚሰጡ ወገኖችን ይፈልጋል፡፡

እነዚህ ማዕድኖችና ባህሪዎች ያሏቸው ሰዎች ትኩረት ችረን የኢስላምን ተልዕኮ እንዲሸከሙና ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል አለብን፡፡ እነርሱ የምቾት ጊዜ ጌጥ የችግር ጊዜ ስንቅ ናቸው፡፡ በነዚህ አይነት የባህሪ ባለቤቶች የዳእዋ መሰረቶች ይተከላሉ፡፡ ይህ ማለት እነርሱ ከስህተት የፀዱ ናቸው ማለትአይደለም፡፡ ሁሉም ሰው ከስህተት አይጠፋም፡፡ ግና እነርሱ በአጠቃላይ የመልካም ተልእኮ መሰረቶች ናቸው፡፡ ቢሳሳቱም መስተካከላቸው አይቀርም ፡፡
በዳእዋ መስክ ላይ ያሉ ትልልቅ ሰዎች በዳእዋ ተልእኮዋቸው ላይ ዋና ዋናን ነገር ከዝርዝር ነጥብ ፤ ተጨባጭን ነገር ከሀሳብ ያስቀድማሉ፡፡ የትኛውንም አይነት አደጋ ቢያመጣ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ፅኑ ናቸው፡፡ ቆራጥነታቸው አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ እስኪገናኙ ድረስ ይቀጥላል፡፡ በዳዕዋ መስክ የታላለቅ ስብእናና ስነምግባር ባለቤቶች እስከበዙና እስከጠነከሩ በአንፃሩ ደካማና ሰነፍ ሰዎች ቁጥራቸው እስካነሰ ድረስ የዳእዋ ስኬት መቃረቡን የሚያመለክት ነው፡፡ በተቃራኒ ከሆነም እንደዛው ነው፡፡

## 55)<u>ልክ ያለው፡- የጋለ ስሜት</u>

የጋለ ስሜት ጥሩ በረከት ነው፡፡ ቆራጥነትን የስራ ተነሳሽነት ግንባር ቀደምነት መስዕዋትነትን የመልካም ስራ ፉክክርን የራስን ጥቅም ለሌላ አሳልፎ መስጠትን ፈጠራን የማለምለምና የማሳደግ አቅም አለው፡፡ የመልካም ባህሪ መፍለቂያ ነው፡፡ይህ የጋለ ስሜት የዳእዋ ስራ ወደፊት በማራመድ ረገድ የሚጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡
ስለዚህም የዳእዋ ሰዎች የስሜት መግነጢስ በመጫር ግለትና ሙቀትን የጨምራሉ፡፡ መልካም አድርገዋል ግና ከጋለ ስሜትና ሙቀት ጋር ሊስተዋሉ የሚገባቸው ሁለት ነጥቦች አሉ፡፡

1ኛ- የግለት ስሜት የመፍጠሪያ መለኪያው በቁም ነገር ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ልክ ሀኪም ለበሽተኛ እንደሚሰጠው መድሀኒት ልኩንእንዳያልፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ ሀኪሙ የበሽተኛውን ሁኔታ እየረሳ በአዲስ ተመን መድሀኒት እንደሚያክለውና እንደሚቀንሰው የዳእዋ ሰዎችም የተከታዮቻቸውን ስሜትና ግራት በጥንቃቄ እየረሮጡ አቅጣጫ ማሳየት መቻል አለባቸው፡፡ በትክክል ያልተያዙ ስሜትና ሙቀት በተለይም ወጣቶች ዘንድ ሊፈጠር የሚችለው ውጠየት መልካም ላይሆን ይችላል፡፡ምናልባትም ከባድ ውድመት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2ኛ- ጥበበኛ የዳእዋ ሰው የእርሱ ተከታይ ለሆኑ አጃቢዎቹና ተከታዮቹ የዲን ስሜታቸውን ሊያስተናግዱበት የሚችሉበትን አትራፊና አዋጭ መንገድና ሁኔታ ሊያመቻችላቸው ይገባል፡፡ ዋጋና ቁም ነገር ያለው ተግባር እየፈፀሙ እንደሆነ እንዲሰማቸው በአቅማቸው ልክ መትጋታቸውን እንዲያስቡት ማድረግ አለበት፡፡
አለያ እነርሱ የከንቱነት ዋጋ ያለው ጉዳይ አለመፈፀም፡፡ ስሜት ሊፈጥርባቸው ከሚችላቸው የህሊና ወቀሳ ያተርፋቸዋል፡፡ የተቻላቸውን ማድረጋቸው በራሳቸው ተጠቃሚና የሰጡት አገልግሎት ውጤት ማስመዝገቡን ይረዳሉ፡፡

## 56) ህጋዊ ሰውነት ያለውና ህዝባዊ የዳእዋ ስራ

ህጋዊ ሰውነት ያለው የዳዕዋ ስራ የሚባለው ከመንግስት አካል ጋር የተሳሰረና የመንግስት ይሁንታ ያገኘ የዳእዋ ስራ ነው፡፡ ህዝባዊ የዳእዋ ስራ የምንለው በመንግስት ስር ያልሆነ ህዝቡ የሚያንቀሳቅሰው የዳዕዋ ስራ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የተለምዶ ነገር ሆኖ በነዚህ ሁለት አይነት የዳእዋ አካሄዶች መሀከል አለመተማመን መዳባት መወነጃጀል አልፎ አልፎም

ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለት ነገሮችን ማስተዋል መቻል አለብን፡፡

1ኛ - ሁለቱም የዳዕዋ አካሄዶች ሙሉ በሙሉ ስህተት አልያም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሁለቱም ዘንድ ትክክልነትም ስህተትም አለ፡፡

2ኛ - የአካሄድ አቅጣጫው መቀያየር ሊገጥመው ይችላል፡፡ ህዝባዊው የዳእዋ ስራ ወደ መንግስታዊነት ፤ መንግስታዊው ስራ ወደ ህዝባዊነት ሊቀየር ይችላል፡፡ መሆን የሚገባው ጉዳይ ሁለቱም አይነት ቡድኖች በቋሚነት መስራት ያለባቸው በመሀከላቸው በመተማመኛ የመተጋገዝ የመግባቢያ ይቅር የመባባያ ድልድይ ለመገንባት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡

ምክንያቱም ዳዕዋ የሁሉም ሀላፊነት ነው፡፡ ይህንን የአብሮነት ጎዳና ከገነቡ ብዙ መልካም ፋይዳዎች ይገኛሉ፡፡ በተቃራኒው ከሆነ መንግስታዊውም ህዝባዊውም የመከራ ሰንሰለት ውስጥ ይቀረቀራሉ፡ ምናልባትም የመጠፋፋት ሰቆቃ ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ ጉዳዩ ተራ አይደለም አብሮነቱንም መፍጠር ቀዝቃዛ አይደለም፡፡ በጣም አሳሳቢና ትልቅ ቁም ነገር ስለሆነ ፤ ከፍተኛ ጥረትና ቆራጥነት ይፈልግብናል፡፡

## 57)<u>የኒያ ጥራትና ስኬት</u>

የንያ ጥራት አኸላስ በኢስላም ውስጥ ከባድ ቦታ አለው፡፡ ኢኽላስ የስራ አስኳል አላህ ዘንድ ተቀባይነት የማግኛ ሚስጥር ነው፡፡ ኢኽላስ የሌለው ስራ ከንቱና ንፋስ የበተነው ዱቄት ነው፡፡ ግና ኢኽላስ መኖሩ ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡ ምን አልባትም ስራው ኢኽላስ ሊኖረው ግና ትክክለኝነትና ስኬት ሊጎድለው ይችላል፡፡ ኸዋሪጆች የኢኽላስ ማማ ላይ ነበሩ፡፡ ግና የፈፀሙዋቸው ጥፋቶች አደገኛ ነበሩ፡፡ ስለዚህም ለኢኽላስ

የሚደረግ ጥሪ ትክክለኛነትና ስኬትን ሊያጣምር ይገባዋል፡፡ ሁሉቱ ሲዋሀዱ ግቡን ይመታል፡፡የዳዕዋ ሰዎች ለኢኽላስ ጥሪ የሚያደርጉትን ያህል ለትክክለኛ ስራ እና ለስኬት የሚጠቅም መንገድን መፈለግ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ይህም ለሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው፡፡

1ኛ - የትክክለኛነት ታላቅ ዋጋ ስላለው እሱም የስኬት መንትያና መስፈርቱ ግማሹ ስለሆነ ነው፡፡ (የኒያ ጥራትና የተግባር ትክክለኛነት) ውጤታማነት የስኬት መነሻዎች ሌላው ገፅታ ነው፡፡

2ኛ - ብዙ ጊዜ በዳእዋ መስክ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች ገራገርነትና ሁሉንም በመልካም ጎን ብቻ የማየት ዝንባሌ አላቸው፡፡ ስለዚህም ከበፊትም እነርሱ ለአደጋ የሚመቻቹበትና የተረጋገጡበት ጊዜ አለው፡፡ አሁንም ይመቻቻሉ በሌሎች ሰርጎ ገቦች አቅጣጫቸውን የማስቀየር የማታለል የአደጋ ቀለበት ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ የተደረጉም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም በጣም አስፈላጊና አሳሳቢ ሁኔታዎችና ጉዳዮች እያሉ ተራና አሳሳቢ ባልሆኑ መስኮች ጉልበታቸውን ያባክናሉ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአላስፈላጊ ቦታና ጉልበትና ገንዘባቸውን ፋይዳ በሌለው ጉዳይ ያጠፋሉ፡፡ ሌላ ጊዜ የሞኝነትና የመሀይምነት መግለጫ ጥግ በሆነ በስህተትና ጥፋ ሜዳ ላይ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ይከፍላሉ፡፡ እነርሱ የለውጥ አቅጣጫውና ዋና ተዋናኝ ነበሩ ግና ለውጡ ያቃጥላቸዋል እነርሱኑ ነው የመታው ለውጥ ከቀድሞው የከፋና ውስብስብ ይሆናል፡፡

## 58)<u>ከፍተኛ ድክመት</u>

የብዙ ሙስሊሞችና በዳዕዋ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ያስመዘገቡዋቸው ውጤቶች ሲመረመሩ ዲናቸውንም ሆነ ምድራዊ ህይወታቸው ጋር ያላቸው ትስስር ከፍተኛ ክፍተት ተስተውሎበታል፡፡ ይህ ነገር አላህ

(ሱ.ወ) እነርሱን በዕጬነት ላቀረበበት የሰው ልጅን የማቃናት ስልጣኔን የመገንባት ተልዕኮ ጋር በፍፁም የሚቃረን ተግባር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሰጣቸውን ለስራ የሚነሳሳ ትክክለኛ ኢማን ፣ ሰፊ ሀብት በጣምትኩረት የሚስብ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በከፍተኛ እድገት ላይ ያለ የሰው ሀብት የጠሰጣቸው ሰዎች ቀሽም ክፍተት እየተመዘገበባቸው ነው፡፡

ስለዚህም የሙስሊሙ አለም መሪዎችና አስተዋዮች ይህንን ችግር በትክክል አጥንተውና አስልተው ሙስሊሞች ከስራ ፈትነትና ተመልካችነት ወደ ተሳትፎና አምራችነት ከኋላ ቀርነት ወደ መሪነት የሚያሸጋግራቸውን ዘዴዎች ሊተልሙላቸው ይገባል፡፡

ለዚህ አጋዥ የሚሆን ዋና ዋና ነገሮች ቆራጥነትና ፣ ፈጠራ ፣ ግምገማ ፣ እድገት ተኮር የሆነ ፉክክር ፣ ደረጃውን የጠበቀ የተሳካ ስራ ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የስራ እድል ፣ ተቋማዊ ስራ ፣ የተሳካላቸውና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን መሸለምና ማበረታታት ደካሞችንና አጥፊዎችን መቆጣጠርና መግለፅ ፣ የስራ ፍቅርን መትከል ፡፡ ወዘተ......

## 59 ) ስለ ሴራ

ከአስርት አመታት ወዲህ የሴራ ጉዳይ አወያይ ነው፡፡ ሴራን ሁሉ አቀፍ በማድረግ ጭራሽ የለም በሚል እንዲሁም ሀሳብ ለመስጠት የሚቆጠብ አለ እውነታው ግን ሴራ ከሰው ልጅ መገኘት ጋር አብሮ የተገኘ ጉዳይ ነው፡፡ ወደፊትም ይቀጥላል ግና በደንም ሆነ በእውቀት ላይ ከተመሰረትን ሁሉንም ነገር ከሴራ አንፃር መገምገም አግባብ አይደለም፡፡ ልናውቅ የሚገባው ነገር ሴራ አልፎ አልፎ ይሳካለታል፡፡ ሌላ ጊዜ ሴራውን የጎነጎነው ላይ ተቃራናዊ ውጤት ያመጣል፡፡

ስለ ሴራ ስናስብ ከሁለት ተቃራኒ የተሳሳተ ጠረፍና ጫፍ አርቀን ማስተዋል አለብን፡፡ እነርሱም በጣም ሴራን ማግዘፍና አልያም ማጣጣል

ናቸው፡፡ ስለዚህም በትክክለኛ መርህ ላይ ማስቀመጥ አለብን፡፡ ሊገዛን የሚገባው ህግ የትብብርና የትግል መርህ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በዝርዝር ጉዳይ ልንባክን አይገባም፡፡ የኛን ጉዳይ ድክመትና ስንፍና ሁሉ በሴራ ላይ ልንደፈድፍ አይገባም፡፡

የሴራን መኖር መዘንጋትና ማናናቅ አልያም በጣም ማግዘፍ ሌላው ከባድ አደጋና አሳሳቢ ፈተና ነው፡፡ ሴራን በማይሆን መንገድ ማስተናገድ አልያም አላህ (ሱ.ወ) አዘጋጁ ያለንን ዝግጅት እርግፍ አድርጎ መተው ከባድ ትፉት ነው፡፡

## 60) <u>ተፅዕኖ እና የትኩረት ጉዳይ</u>

ሙስሊም በህይወቱ ሁለት አሳሳቢ ቁምነገሮች አሉበት፡፡ የተፅእኖ ስፈራና የትኩረት መቻር ናቸው፡፡

1ኛ - **<u>ተፅዕኖ ማሳደር፡-</u>** የሚመለከተው በእርሱ አቅም ስር ያለ ሊንቀሳቀስበት የሚገባ ለእነሱም ሆነ ለሌላው ሊጠቅም የሚችልበት ቦታ ፤ የራሱን ጤና ፣ መተዳደሪያ ፣ ዘመዶቹንና ጓደኞቹን የሚጠቅምበት ፣ በዙሪያው ያሉትን የሚመክርበትና የሚያቀናበት ፣ የራሱን አቅምና ክህሎት የሚያጎለብትበት ለቤተሰቦቹ የሚተጋበትና የሚጥርበት አገሩን የዕርሱን ስራ የሚገዛውን የአገሩን ህግና ስርአት ጠንቅቆ ማወቅ ወዘተ.....

2ኛ - **<u>ትኩረት መቸር ፡-</u>** አገራዊና አለማቀፋዊ ጉዳዮችን መከታተል ማለት ነው፡፡ እርሱ ግን በአገራዊና አለማቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ትልቅም ሆነ ጥቂት ተፅእኖ ማሳረፍ አይችልም፡፡ ለምሳሌ የዶላር መጨመር ፣ የሌላ አገር ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ፣ የአየር መበከል ፣ የአየር መቀያየር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

አስተዋይ ሙስሊም ትልቁ ትኩረቱን ሊቸር የሚገባው በመጀመሪያው ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ ተፅእኖ ማሳረፍ የሚችልበትና

ትርጉም ያለው ቁም ነገር ሊከውን ይችላል፡፡ እንዲሁም ሸሪአዊ ተጠያቂነቱ በዚሁ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ሁለተኛው መስክ ግን በተወሰነ ደረጃ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ፣ ዘመኑ ላይ እየተካሐየዱ ያሉ ነገሮችን ለመረዳት ያህል የሚከተለው የሌሎችን አኗኗር የሚቃኝበት ነው፡፡ በትኩረት ሜዳ ላይ በሰፊው ከገባበት አደጋ ውስጥ ተነክሏል ጉልበቱን ጊዜውን ስሜቱን ዝም ብሎ የሀዘን ስሜት ውስጥ መንከር ብቻ እንጂ አርሱ ሊያስተካክለው በማይችለው ውቅያኖስ ውስጥ ይባዝናል፡፡ ሁሌም በስጋት በውድቅትና በሀዘን ህይወት ውስጥ ይዋዥቃል፡፡ ምናልባትም ሊሰራቸው የሚችሉ ስራዎችን መፈፀም ይከብደዋል፡፡ በራሱ አለም ይኖራል ፡፡ ለራሱም ከንቱ ምክንያቶችን ያቀርባል፡፡ እርሱ ላይ ለጠመጠመው መከራና ችግር የአላህን ፍርድ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ ይህ የጥበባዊ ንግግር እንዴት ያምራል፡፡ « ስኬታማዎች ውጤታማዎች መፍትሄ የሚፈጥሩ እና የተሸለ መንገድ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ሽንፈታሞች ወዳቂዎች ምክንያት የሚደረድሩና ፈተናን ማለፍ የተሳናቸው ናቸው፡፡»

## 61) <u>የአረብኛ ቋንቋ አስፈላጊነት</u>

ቋንቋ የዕውቀትና የባህል ማዕድ ነው፡፡ የግንኙነትና ትስስርም መሳሪያ ነው፡፡ ከማንነት ዋና መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡ ስለዚህም ቋንቋ በሰዎች ህይወት ውስጥ ዋናውን ስፍራ ይይዛል፡፡ አረብኛ ቋንቋ እንደ ሌሎቹ ቋንቋዎች የሚያደርገው እነዚህን ነጥቦች ይጋራል፡፡ ከሌሎች ቋንቋዎች የተለየ የሚያደርገው አላህ (ሱ.ወ) የቁርአን ቋንቋ ስላደረገው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ( እራሱ ለሚያውቀው ጥበብ)ከእርሱ ዳእዋና ተልዕኮ የሚወክለውን ዘመን ፣ ስፍራ ፣ ሰውና ቋንቋ አላህ ያውቃል ፣ ቁርአንን ሱንናንና የኢስላምን የታሪክ የእውቀት የባህል ክምችት አረብኛ ቋንቋ ላይ

አደረገው፡፡ የኢስላማዊ ታሪክ ሲጠናና ሲመረመር እስልምና እና አረብኛ በጥምረት የተስፋፋባቸው ሁኔታዎች እንደሚያሳዩት ኢስላምን በትክክል ለመረዳትና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ አረብኛ ታላቅ ሚና ተጫውቷል፡፡፡ ሙስሊሞች ፖለቲካ ስልጣናቸው በተዳከመ አልያም በጠፋ ጊዜም እንኳ ቢሆን የአረብኛ ቋንቋ ሀይማኖቱን ለማስፋፋትና ለመጠበቅ የተጫወተው ሚና እጅግ የበዛ ነው፡፡

ስለዚህም ኢስላምን ለማስፋፋት በሚኖር የትኛውም እንቅስቃሴ አረብ አገራት ላይ ባይሆንም ሙስሊሞች ከአረብኛ ቋንቋ ጋር እንዲተዋወቅ የምንችለውን ያህል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ግድ ይላል፡፡

## 62)<u>አላማን ማስቀመጥ</u>

የትኛውም አይነት የዳዕዋ ስራ ከግብ ሊያደርሰው የሚሥበው አላማ አለው፡፡ ይህንን አላማ ወስኖ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በሆነ የዳዕዋ መስክ ሰዎች አስበውና አስልተው በጥንቃቄና በግልፅ ሊደርሱበት የሚያልሙትን ግብና አላማ በፅሁፍ ሊኖሩ፤ እያንዳንዱ አረፍተ ነገር እያንዳንዱ ቃላት ታስቦበት የታሰበውን አላማ በትክክልና በግልፅ መቀመጡን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የተፃፈው አላማ ሊመታው የፈለገው ግብ ሊዳስስ ይገባዋል፡፡

በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን ደረጃ የሚያማልል ደስ የሚያሰኝ ግን ሊደርስበት የማይችልን በተግባር ለመድረስ የሚሥቸግረን ነጥብ ማስቀመጥ ፣ የውድቀትን እና የሽንፈትን ፅዋ ለመቅመስ እንጂ ለስኬት የሚያቀርብ አይሆንም፡፡ ምን አልባትም ለበለጠ ጥፋት ይዳርጋል፡፡እንዲህ አይነት ስህተት በግለሰብ ደረጃ ከተፈፀመ ከባድ አደጋ ነው፡፡ ስህተቱና ጥፋቱን የተደራጀ ቡድን ከፈፀመው አደጋውና ችግሩ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡

በኢስላማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጓዙ ሰዎችን በጠንካራ ሁኔታ በተደጋጋሚ በሚተቹበት ጉዳይ እነርሱ በደንብ የሚያውቁት « የሚፈልጉትን» ነገር በትክክል አያውቁትም፡፡ የዳዕዋ ስራ የተሳሳተ አላማ ካነገበ ወይም ትክክል ሆኖ ተጨባጭና ሊሳካ የማይችል ከሆነ እንቅስቃሴው እራሱን ይጎዳል፡፡ ምክንያቱም በህልም እንጀራ ውስጥ እየገዙት ነውና፡፡ የእነርሱን መልካም ሀሳብና ንያ እንዲሁም ኢኽላስ በምድራዊ ጉዟቸው ላይ ምንም አይነት ፋይዳ አያመጣም፡፡ በመሰረቱ ኢኽላስ ለዳዕዋው ስኬት የሚፈልግ ቢሆንም ትክክለኛ እቅድና አላማ አለመቀመጡ ስራውን በግማሽ እንዳይሳካ ያደርገዋል፡፡

የዳዕዋ ሰዎች በትክክል ሊያውቁት የሚገባቸው ዋናው ቁም ነገር « እነርሱ ማን ናቸው?» « ምን ይፈልጋሉ?» ከዚህም ላይ ተመስርተው ስትራቴጂያቸውንና እቅዳቸውን ሊገነቡ ይገባል፡፡ በዚህም እነርሱ ከራሳቸው ጋር እውነተኛና ታማኝ ለእነርሱ ተከታዮችና ወዳጆችምሀቀኛና ታማዕ ይሆናሉ፡፡ ይህንን ካደረጉ በእርግጥ ታላቅ ኩም ነገር ፈፅመዋል፡፡ በተቃራኒው ከሆነ ከባድ ውድመት ያመጣሉ፡፡

## 63) <u>ታላቅ ጀግንነት</u>

ጀግንነት ታላቅ ስብዕና ነው፡፡ የዳዕዋ ሰዎችሊካኑን የሚገባ ባህሪ ነው፡፡ በዳዕዋ ስምሪታቸው ወቅት ዋናው ስንቃቸው ነው፡፡ የዳዕዋ ስራ በጀግንነት ከተወለደ የስኬት መንገዱን ጀመረ ማለት ነው፡፡ ከጀግንነት ከራቀ ግን የውድቀት ዋዜማ ላይ ነው፡፡ ግና ሌላ አይነት ጀግንነት አለው እርሱም መስመር መቀየርና አዋጭ መንገድ መፈለግ ፡፡ መረጋጋት /ስክነት/ እንደየአስፈላጊነቱም ማፈግፈግ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ በሚያስፈልግበት ጊዜ የእንቅስቃሴው ዋና መዘውሮች በሚያምኑበትና በግልፅ በሆነ ሀላፊነት በተሞላውና በነፃነት ላይ ሆነው ሊወሰኑ፤ ወደ ኋላ ማርሽ መቀየሩ ታላቅ

ጀግንነት ነው፡፡ ይህ ጀግንነት ፊት ለፊት ከመጋፈጥና ወደፊት ከሚሄድ ጀግንነት በላጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህንን ውሳኔ ያስተላለፈው ሰው ሰዎች የእርሱን ውሳኔ ማናናቃቸው በፍርሀት መጠርጠራቸው አያሰጋውም፡፡ ምክንያቱም እርሱ የሚተልመው አላማና ራዕይ ሩቅ ፤ ነገሮችን የሚመዝንበት መንገድ ጥልቅ ፣ ውሳኔው የሚመነጨው ከእራሱ ውስጥ የሚፈልቅ እምኔ ላይ ተንተርሶ ነው፡፡ የካሊድ ኢብኑ ወሊድ የሙዕታ ዘመቻን ጥሎና ለቅቆ መምጣቱ ለተነሳው ሀሳብ ግልፅ ማስረጃ ነው፡፡

## 64) <u>የሚሮጡለት ክብር</u>

የዳእዋ ስራ በህይወት ውስጥ ታላቅ ተልዕኮ ነው፡፡ ምክንያቱም የነብያቶችና የአላህ መልዕክተኞች ተልዕኮ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንደተለመደው በዳዕዋ ስራ የተሰማራ ሰው የሰዎችን ክብርና ፍቅር ይጎናፀፋል፡፡ ሰዎች ዘንድ ልዩ የሆነ የክብር ዘውድ ይደፋለታል፡፡ ለአላህ (ሱ.ወ) ብሎ የሚሰራ ሰው ይህንን ክብርና ዝናን ፍለጋ ሊተጋ በፍፁም አይገባም፡፡ እንደውም የእርሱ ጥረት የአላህ (ሱ.ወ) ክብር መቀዳጀት ነው፡ ፡ እርሱ የሰዎችን ክብር ለማግኘት ሳይጥርና ፍቅርንና አክብሮትን ከተጎናፀፈ ለአላህ (ሱ.ወ) ለዋለለት ውለታ ምስጋና ሊያደርስና የተጎናፀፈውን ክብርና ውዴታ የሚመጥን ሰው ለመሆን ሊጥረና ሊተጋ ይገባዋል፡፡ እርሱም ሰዎችን በመውደድ ለእነርሱ ትሁትና አክባሪ በመሆን የእነርሱም ደስታና ምቾት ሊያሳካ በሚችልበት መንገድ ላይ መበርታት በሌላ ጎንም የእነርሱን ንብረትና ሀብት ክብር ላለመንካት ሊጥር ይገባዋል፡ እነርሱም በሌላ ጎንም የእነርሱን ንብረትና ሀብት ክብር ላለመንካት ሊጥር ይገባዋል፡፡ ዕነርሱም ይህን የተቀናጀው ክብርና ሀላፊነት መሆኑን የተሸከመው እዳ መኖሩን ተልዕኮው ረጅም መሆኑን ተረድቶ በዝና

ሳይኮፈስ በድሎት ሳይታለል በምድራዊ ህይወት ሳይማልል የተጫነበትን ሀላፊነት በአግባቡ መወጣት አለበት፡፡

**65)<u>ተልዕኮ እንጂ ሹመት አይደለም</u>**

የዳዕዋ ስራ ከተልዕኮነት መሰረት ወጥቶ ወደ ሹመትነት ነተቀየረ (ብዙ ጊዜ የሚከሰት ነገር ነው፡፡) ከቁም ነገርነቱ ይልቅ ባዶነት አልቦነት ይበዛል፡፡ ከስራ በላይ ወሬ ከመስጠት ይልቅ መቀማት ከሰራተኞች ይልቅ ቀማኞቹ ይበዛሉ፡፡ ከእውነተኞቹ ይልቅ ሙናፌቆቹ ይበዛሉ ፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከባድ ፈተናዎች እና አዋኪዎች ናቸው፡፡ በአንድ ወይም በሌላ የዳዕዋ መስክ ውስጥ በተለያየ ደረጃ ይከሰታሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ዳዕዋ ከተልእኮነት ወደ ስራነትና ሹመትነት ሊለወጥ ነው፡፡

ይህ አካሄድ ሙስሊሞች በዳእዋ መስክ ሊኖራቸው የሚችለውን ተሳትፎ ያቀጭጨዋል፡፡ በአንፃሩም የኢስላም ጠላቶች ይህንን ዳዕዋ ለማጥቃትና ለማጥፋት ብርቱ መጠሪያ ያገኛሉ፡፡

**66) <u>ኢስላምና የተቀበሉ አዲስ ሰዎች</u>**

ኢስላም የተቀበሉ አዲስ ሰዎች ሲመጡ በደስታ መቀበልና ማስተናገድ የማንም ሙስሊም ተፈጥሮአዊ ድረጊት ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ደስታ አልፎ አልፎ ልንከላከለው ከምንችለው ስህተትነት በለጠ ስህተት ውስጥ ይከተናል፡፡እስልምናን ከተቀበለው አዲስ ሰው ሰላም ሆኖ መዝሀቦች የፊቂህ ሊቃውንቶች አርመውታል አስተካክለውታል ከፍለዘመናትም ወልውለውታል፡፡ለእኛ አዋጭ የሆነው መንገድ ሊከሰት ከሚችለው ስህተትም ለመጠበቅ አዲስ እስልምናን ከተቀበለው ሰው ንያ አስተሳሰብ ፅናት ስክነትና ጥበብ በእርጋታ መመዘንና እርግጠኛ መሆን መቻል አለብን፡፡ ለጥቀንም አላም ውስጡ ሰርዖ እንዲገባ ንያው እንዲስተካከል

ግንዛቤው ሚዛናዊ እንዲሆን ስብዕናው እንዲገነባ በተረጋጋ ሁኔታ ልናግዘው ይገባል፡፡

ይህ አካሄድ አዲሱ የኢስላም እንግዳ በተፈጥሯዊ አካሄድ በእርጋታ ይገራበታል፡፡ ወደ ኢስላም የገቡ ሰዎችን በሙሉ በቁስም ሆነ በደስታ ግነትና ድምቀት ያለው አቀባበል ካደረግንላቸው አዲሱን የኢስላም እንግዳ ንዋይ አሳዳጅ እናደርገዋለን ፡፡ እርሱም እንዲኮፈስና እራሱን የእኛ አስተማሪ አድርጎ ይቆጥርና ምንም የሚማረው እንደሉለው ይሰማዋል፡፡

## 67)<u>የፊቅህ መዝሀቦች</u>

የፊቅህ መዝሀቦች ፤ በአጠቃላይ ብዙ ተከታዮች ያሏቸውን አራት የፊቅህ መዝሀቦች በተለየ ሁኔታ ስንመለከት ፤ ውድ የታሪክ ሀብት በጣም የደረጀና የተለፋበት ድንቅ ክምችት መሆኑን እንደርስበታለን፡፡ ፊቅህ ሊቃውንቱ ብዙ ከፍለውበታል፡፡ ክፍለ ዘመናትም አደራጅቶና አጎልብቶታል፡፡ የሙስሊሙ ህዝብ የኩራት ምንጭ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም የሚከተለውን መዝሀብ / መስመር ይመርጣል፡፡ የመረጠውን መዝሀብ ማስረጃዎችና ማጣቀሻዎች ማወቁ የተሻለ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል የሌሎቹንም የመዝሀብ ምርጫ ማክበር አለበት፡፡ እንደየ አስፈላጊነቱም ከሌሎች ጋር ሊወያይ ውይይቱም በስርአት ውይይትና በተወሰነ ነጥብ ዙሪያ መሽከርከር አለበት፡፡በነዚህ ሁላ የፍቅህ መዝሀቦች ቢሰጥ ትክክለኛነቱና ስህተቱ በላጭነትና ተበላጭነት አንዱ ከሌላው ይለያል፡፡ ይህንን ውሳኔ የሚያሳልፉት ሊቃውንትናየማነፃፀር የማበላለጥ የመምረጥ አቅምና ክህሎት ያላቸው እውቀታቸው የደረጀ ሊቃውንቶች ናቸው ፡፡ እነሱም ሽሪአ ከዘመን ዘመን እንዲሻገር ተራማጅ የሆኑ የኢስላም ሽሪአዎችን የሚያፈልቁ ናቸው፡፡ለፊቅህ መዝሀቦች ወገንተኛ መሆን በጣም አፀያየፍና ጎጂ ተግባር ነው፡፡ በአንፃሩም የመዝሀቦቹን ጠቃሚነት ማናናቅ

መዋጋት ህዝበ ሙስሊሙ በመዝህቦች እንዳይጓዙና እንዳይጠቀም ከቁርአንና ከሱንና የፊቅህ ህግጋትን በቀጥታ እንዲቀዳ ማስተማር ከባድ አደጋና ጣጣ ያመጣል፡፡ ከነ ጭራሹም የፊቅህ መዝህቦችን ነቅሎ መወርወር የተሻለ ነው የሚል ጥሪ በዕውነታው አለም ውስጥ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ይህንን እንፈፅማለን ብለው ጥሪ የሚያደርጉ ሰዎች እነርሱ እራሳቸው የፊቂህ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን እናመጣለን ብለው የሚሞከሩ ሰዎች አልምያም እራሳቸው በመረጡት ወይም የእነርሱ አስተማሪዎች በመረጡት መንገድ አውቀውም ይሁን ባለማወቅ ሌላ የፊቂህ ትንታኔዎች መቀበላቸው አልቀረመረም፡፡ እንደውም የፊቂህ መስራችነት አካሄድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እራሳቸው ቀድሞውኑ ሌሎችን የተቀናቀኑበትን ችግር ውስጥ ተዘፈቁ ማለት ነው፡፡

## 68) <u>ሙስሊም ሴት</u>

ሙስሊም ሴት በሁለት ፅንፈኛ ቡድኖች መከራዋን እያች በደል እየተፈፀመባት ትገኛለች፡፡

**1ኛ**)<u>ፅንፍ የወጣው የሴኩላሪስቶች ቡድን ነው፡፡</u>ይህ ቡድን ጥረት እያደረገ ያለው ሙስሊሟን ሴት ከተፈጥåዊ ባህሪዋ ፣ ከዲንዋ ፣ ከክብሯ አላህ (ሱ.ወ) ከሰጣት መለያዋ ፣ አውጥቶ ማበላሸት ዋና ዋና ጥረቱ ነው፡፡

**2ኛ**)<u>ሀይማኖታዊ ፅንፍ ነው፡</u>- ይህ ፅንፍ ጥረቱ ሙስሊም ሴትን በሆነ ጠባብ ክልል አጥሮ ግዑዝነትና ሚና የራስ ፍጡር ማድረግ በህይወት ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎ እንድታደርግ ማገትና መዝጋት ዋናው ድርጊቱ ነው፡፡

የዚህ ፅንፈኝነት አላማዎች የተወገዙ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ የተነሱበት መልካም ሀሳብ ነው ቢባልም የእነዚህ የሴት እይታ

የተጠራጣሪነት የአለማመን የንቀት እይታ ነው፡፡የነርሱ ስህተት የሚጀምረው “ቀዋማ” የሚለው የቁርአን አንቀፅ የተወላገደ ግንዛቤ መያዝ ነው፡፡ የዚህ እይታ እሳቦት መነሻው የሴቶች መብትና ስብዕና በኢስላም ምን እንደሆነ አለማወቅ በዘመን ሽግግርና ሂደት የተጠራቀሙ የባህልና የወግ ጫና ነው፡፡ በቆይታና በሂደትም ባህሉና ወጉ የዲን ካባ አለበሰው ፡፡ ዲን ከዚህ የጠራና የራቀ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሙስሊሞች እንዲሁም የዳዕዋ ሰዎች በተለየ ሁኔታ በሴት ላይ እምነት ሊጥሉ ይገባል፡፡ በሚዛናዊነት ሊመለከቷት ሀቅ አላት፡፡ በህይወት ውስጥ ያላትን ሚና እንድትጫወት እድሎች ሊመቻቹላት ይገባል፡፡

የመጀመሪያው ሚናዋ የዳእዋ ሚና ነው፡፡ ይህ መሳካቱ ብዙ ፍይዳዎች ይኖሩታል፡፡ ዋናው ፋይዳ ፍትህ መስፈኑ ነው፡፡ ፍትህ በኢስላም መሰረታዊ ነጥብ ነው፡፡ የእርሷን ጥረትና ትጋት በዳዕዋ መስክ ቦታ መስጠትና መጠቀም መቻል ነው፡፡ በተለይም

ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ስኬታማ የሚሆኑባቸው መስኮች ላይ የሴቶቹን ልምድና የስኬት ጥበብ መቅሰም አስፈላጊ ነው፡፡

ሴትን ለማታለል የጥሜት ጥሪዎችን ተስፋ ማስቆረጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ከዚህና ከዚያ ሴት ላይ የሚደርሱ ግፎችንና በደሎችን እንደ ናሙና በማቅረብ ሙስሊምን ሴት ከሀይማኖቷ ለማጋጨት የሚጥሩ “ የነፃነት” አታላዮችን መግታት ያስፈልጋል፡፡ኢስላም ሴትን ፍትሀዊ እና ሚዛናዊ የሆነ ነፃነት አጎናፅፏታል፡፡ መብቷን ፣ ክብሯን ፣ ነፃነቷን ተፈጥሮአዊ የሴትነት መለያዎችን ጠብቆላታል፡፡ አስጠብቆላታል፡፡ ኢስላም ሴትን የህብረተሰብ ግማሽ የወንዶች አጋር አብሮነት የትውልድ አምራችናአላቂ አድርጓታል፡፡

## 69 )<u>የኢባዳ ትርጉም ሁለንተናዊነት</u>

የሰው ልጅ የመኖር አላማ ሙሉ በሙሉ አላህን (ሱ.ወ) ማምለክ ነው፡-

وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ۝٥٦ سورة الذاريات:56

« ጋኔንንነና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡» አል ዛሪያት፤ 56

ይህ ሙሉዕ የሆነ የኢባዳ ግንዛቤ ሰው ልጅ በአላህ (ሰ.ወ) በታማኝነት ሁሌም እንዲያመልከው ያደርገዋል፡፡ ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር ያለው ቋሚ ግንኙነት በደስታ እንዲሞላ ያደርገዋል፡፡ ይህም ስራ ለስራም ለአገርም ትጉህ እንዲሆን ያግዘዋል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ይህ ሙሉዕ የሆነ የኢባዳ ግንዛቤ ተቆንጥቦ ተቆንጥሮ በአምልኮታዊ (በሰላት ፣ በፆም...” ላይ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ብዙሀን ዘንድ ይወሰዳል ፡፡ እነርሱ ዘንድ አምልኮታዊ ተግባራት ብቻ ነው፡፡ ኢባዳ የሚመስላቸው፡፡ እዚህ መነሳት ያለበት ዋና ጉዳይ፡- በኢስላማዊ የዕውቀትና የታሪክ ማዕድ ውስጥ በተለመደ ሁኔታ በተለያ መግለጫና መጠሪያ የተለያየ ስያሜ እየተሰጣቸው የሚጠሩ እንደ አቂዳ አባዳ ሙአመላት የሚባሉ መጠሪያዎች፡፡

ለትምህርታዊ ገለፃ እንዲመቹና በእውቀት መስክ ላይ ለሚደረግ ጥናት መገለጫነት የሚያገለግሉ ለትምህርት አሰጣጥሲባል የተፈጠሩ ስያሜዎች እንጂ ሌላ ምንም አይነት የተለየ ከፍም ዝቅም ያለ ትርጓሜና መልእክት የላቸውም፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ትምህርታዊ የስያሜ ክፍፍልና አካሄድ የኢባዳ ግንዛቤ በአምልኮአዊ ተግባራት (ሰላት ፣ ፆም ) ውስጥ ብቻ ከሌለው ኢባዳን እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል፡፡ይህ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ይህ ግንዛቤ እንዲስፋፋና እንዲሰራፋያደረገው ነገር አንድም የተሳሳተ ግንዛቤ በሌላ

በኩል አምልኮታዊ ተግባራት ከሌላው የተሌ ናቸው፡፡ የሚያሰኝ ባህሪ ስላላቸውና እነርሱም መላበሳቸው የአስተሳሰብ ምህዳሩን የሰፋ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ከዚህም በመነሳት እኛ የኢባዳን ሰፊ ትርጉምና ሰለፎች (ቀደምቶች) በተረዱበት መልክ እንረዳለን፡፡ ሁሉንም ሙስሊሞች ይህንን ግንዛቤ እንዲረዱ ጥሪ እናደርጋለን፡፡ ኢባዳ እያንዳንዱ ሙስሊም ዘንድ ሁሉንም ነገር የሚያጠቃልል አቂዳ ፣ ፖለቲካ ፣ አምልኮታዊ ተግባራት የንግድ ልውውጥ ምድርን ማዕድኗን መጠቀም በአግባቡ ማልማትና ማበልፀግ የኢስላምን ተልዕኮ ማድረስ በሀላል ነገር መጠቀም መዝናናት ስራን በተሳካ ሁኔታ መከወን ምርታማ ስራ መስራት.........ወዘተ

## 70)<u>የመጭውን ጊዜ መተለም/ማቀድ</u>

ዘመን በአላህ(ሰ.ወ) ትዕዛዝ ያለማቆም በቀጣይነት መጓዙን ይቀጥላል፡፡ የዛሬው ኗሪ የትናትን ልጅ የወደፊተ አባት ነው፡፡ ስለዚህም የዳዕዋ ክንውን የቀደምት ልምዶችን ሊቀስም ግድ ይለዋል፡፡ ዛሬን በአግባቡ ሊገለገልበት ይገባል፡፡ ለመጪው ዘመን ይዘጋጃል፡፡ በአቅሙናችሎታው መጠንም ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡ ለምክንያቶች ሁሉ ፈጣሪ ጉዳዩን ሊያቀብልና በአላህ ላይ ያለው እምነት ሊጠነክር በእርሱም ሊመካ ይገባል፡፡

ስለዚህም የወደፊትን ዘመን መተለም ለእርሱም ዝግጅት ማድረግ ዕቅድ መንደፍ የዳእዋ ስራ ግዴታ ነው፡፡ አርቆ ተመልካችነትን ያሳያል ፣ ለስኬትና ለድልም ያደርሳል፡፡ ይህንን ያደረገ በእርግጥ መልካም ሰርቷል፡፡ ይህንን ካላደረገ እራሱን ግዑዝ እና የለውጥ አጋርነትን የተነፈገ ያደርገዋል፡ ከጊዜ በኋላ ያለፈ ወሬ ይሆናል ታሪኩ ይዘጋል ይረሳል፡፡

ኢስላም የወደፊቱን የሚተልም ሀይማኖት ነው፡፡ ይህንን የኢስላምን የወደፊት ተመልካችነት በብዙ ነገሮች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ኢስላም ሁሌም አላህን እንድንፈራ ለሂሳቡ ቀን እንድንዘጋጅ ያዘናል፡፡ ምክንያቱም የኛ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወነሰው እዚያ ስለሆነ ነው፡፡ ሁላችንም የነብዩላህ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) ታሪክ በደንብ እናውቃለን፡፡ እርሳቸው ግብፅን የሰባት አመት ቸነፈር ተጋርጦባት እራሳቸው በነደፉት ጥበብ ያለው እቅድ ግብፅ ከረሀቡ ድናለች፡፡

የኛ ነብዩ የአላህ መልዕክተኛ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለወደፊቱ ማቀድ በሁሉም መስክ ትልቅ ቦታ ይቸሩ ነበር፡፡ ዝርዝር የሆኑ ረቂቅ ነገሮችን እንኳን ችላ አይሉም ነበር፡፡ ይህንን ፕላንና እቅድ ወደ ሀበሻ በተደረገው ስደት ላይ ቁልጭ ብሎ እንመለከተዋለን፡፡ እንዲሁም ወደ መዲና በተደረገው ጉዞም ላይ እንመለከተዋለን፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና ላይ ከየሁዶች ጋር ያደረጉትን ስምምነት ይህን ያሳያል፡፡ እርሳቸው ያሰማፅቸው ትናንሽ ቁጥር ያላቸው ጦሮች እርሳቸው የመፅቸው ጦርነቶች የላኳቸው መልዕክቶች በአለም አቀፍ ደረጃ እና ግንዛቤ መዲና ላይ የነበሩ ሙስሊሞችን የህዝብ ቁጥር ማወቃቸው ከዚህም ሌላ ላሉ የነብጠዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዝርዝረና ረቂቅ እውቀት የወደፊቱ አቅጣጫና ሂደት የመመዘን ብቃት በነብዩ (ሰ.ዐ ወ) ታሪክ እና ችውቀት የወደፊቱን አቅጣጫ ህይወት ላይ የሚያጠነጥኑፅሁፎች በስፍራው አትተዋል፡፡

## 71) <u>የተሳሳቱ የመልስ ምቶች</u>

አንዳንድ "የለውጥ ፋና ወጊዎች " የተመለከቱትን ችግርና ስህተት ለመመለስ በማረም የሚወስዱትን የመልስ ምት ልናሳሳስብ እንወዳለን፡፡ የአስተሳሰብ አልም የባህሪ መወላገድና መበላሸትን ሲመለከቱ ከሚገባው በላይ ያጋኑታል፡፡ እነርሱም በሌላ አቅጣጫ ልክ ያልፋሉ፡፡ አልያም

ሰፊውንና የሚፈቀደውን ሜዳ ያጣብቡታል፡፡ ( ለውጥ አልማጁ) ሙህመድ አብዱ የተተበተና ቡትቶ አስተሳሰቦችና ድርቅናን ሲመለከት ስጋትና ፍረሀት መጣባቸውና በጣም በበዛ ሁኔታ  የአእምሮን አቅም አጋነነው፡፡ ሙስሊሞች ዘንድ የተንሰራፋው የቀዷ እና የቀድር አስተሳሰብ በጣም በመስፋፋቱ ሙስሊሞች ዘንድ የተፈጠረው የስንፍና የድክመት እና የተወኩል ግንዛቤ ያሳዘነው (ገጣሚው) ሙህመድ ኢቅባል ሙስሊም ግለሰብ በተግባር እና በስራ ላይ ያለውን ችሎታ ግነት ያለው ከፍታ ላይ አስቀመጠ፡፡

ልክ እንደዚሁ የበቢድአ ግንዛቤ ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ የሰጡ የጥሜት ቢድአ  በሀይማኖቱ ላይ ያደረሰውን ጥቃት የተመለከቱ ሰዎች ሀይማኖቱ ከቢድአዎቹ ጋር ሊገናኝባቸው በማይችሉ ነጥቦች ላይም አስፍተውታል፡፡ በመዝሀብ ወገንተኝነትን ያስተዋለና የተማረረም ሰው መእሀብ የሚባል ነገር ይሰረዝ ማለት ደረጃ ደርሷል፡፡ የምቾትና የንዋይ ስፋትንና ድንበር ያጣ አባካኝነትን በአካባቢው ላይ የተመለከተም ሰው መልካም ውጤት ወደ ማያስመዘግብ መጥፎ ውጤት ወደ ሚጎትት ምድራዊ ህይወትን ወደ መተውና ወደ መራቅ ምርጫውን አድርጓል፡፡

## 72)<u>ድሎችና ሽንፈቶች</u>

በአስተዳደራዊ ታሪክ ብርታትንና ጥንካሬን የሚፈጥር ብዙ ድሎች አሉ፡፡ በተጨማሪም በኢስላማዊ የዳዕዋ ስራ መዝገብ ውስጥ በራስ ለመተማመን የሚያነሳሱ በርካታ ገድሎች አሉ፡፡ እነዚህ ገድሎች ወደ ስራ ለመነሳሳትና ለማነቃቃት የጥንካሬ ምንጮች ይሆናሉ፡፡ የወደ ፊቱን የስኬትና የድል በር ለመቆርቆር የሚያነሳሱ ጠቃሚ ሞተሮች በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በአንፃሩም ለጉራና ለሽለላ አገልግሎት ብቻ ከዋሉ ጎጂና አሳናፊ ሰነፍና ደካማ ያደርጋሉ፡፡

የዚሁ አይነት ሂደት በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥም ይንፀባረቃል፡፡በኢስላም የስራና የዳዕዋ መስክ ውስጥ የተከሰቱ ስህተቶችና ድክመቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህን ስህተቶች ከተማርንባቸውና የወደፊቱን አቅጣጫ ከተለምንባቸው ለውጤትና ለግንባታ ከተጠቅምንባቸው መልካም ሚና የማግኘት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ እንዲሁም ስህተቶቻችን ላይ ካለቀስንና ስህተታችን ተስፋ ካስቆረጠንና ለመወቃቀስ ለመጠላላት ከተጠቀምንበት የውድቀት ጉዞአችንን የሚያፋጥን ነዳጅ ይሆናል፡፡

## 73)<u>በምድር ላይ መኖር በላጭ ሲሆን</u>

በአላህ መንገድ መሰዋት (ጂሀድ) አላህ(ሱ.ወ) ከሰዎች መሀከል ለመረጣቸው ብቻ የሚሰጠው ሽልማት ነው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ቀልባቸውን የሰራ ሰዎች አላህ ሸሂድነትን (ሰማዕትነትን ) እንዲያሳካላቸው ይመኛሉ፡፡ ሆኖም ግን በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ህይወትን መኖር በአላህ (ሱ.ወ) ጎዳና ከመሞት እኩል ነው፡፡ የሚፈለግና የሚወደድ የትግል ሜዳ ነው፡፡ ምናልባትም በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ መኖርና መታገል ለሙስሊሞች ያለው ፋይዳ በጣም ትልቅ ነው፡፡ እንዲሁም በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ከመሰዋት ለሙስሊሞች የሚጠቅማቸው በአላህ መንገድ መኖር ነው፡፡ ይህም ማለት በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ላይ ያሉ የለውጥ አላማዎች የአላህን ዲን ለማገዝ ጉልበታቸውን ሲያፈሱ ሙስሊሙን ህዝብ ሲያግዙ ከርሰምድሩን የያዘውን ማዕድን በአግባቡ አውጥተው ለህዝቡ ሲያውሉ መልካም አርአያ ሲሆኑ የነርሱን አርአያነት ለመከተል ለሎቹ ሊቀኑባቸውና የነርሱን መንገድ ለመከተል ሲታትሩ ይህ እራሱ ትልቅ ጀሀድ ነው፡፡

## 74)ጥፋትና ታዛዥነት

ቀልብ ወንጀልንም መልካም ነገርንም ትፈፅማለች፡፡ አካላዊ ስውነትም እንዲሁ የቀልብ ስራ ከአካላዊው ስራ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም አካል ከቀልብ ጋር ትስስር አለው፡፡ ቀልብ የሰው ዋና አስኳሉ ነው፡፡ ቀልብ ወደ መልካም ነገርም ሆነወደ ወንጀል የሚመራው እርሱ ነው፡፡ ከቀልብ ወንጀል መሸሽና መራቅ ከአካባቢው ወንጀል ከመራቅ በጣም የሚከብድና የሚያስቸግር ነው፡፡ የቀልብ መልካም ስሜቶችን ማፍራትና በእነርሱ መካን ፤ በአካል መልካም ስራዎች ከመስራት በላይ ይከብዳል፡፡ ሙስሊም ከወንጀል ሊርቅና በቀልቡም በአካሉም መልካም መስራትን መላመድ አለበት፡፡  በዚህ ሂደትም ስራ በውጫዊና በውስጣዊ ማንነቱ መሀከል ሚዛናዊ ትስስርና ድርጊት ስለሚኖረው የተሳካለት ሰው ይሆናል፡፡ የውስጣዊ እውነተኛና ታማኝነት በአካላዊ ታዛዥነትና ፍፃሚነት ይዋሀዳል፡

## 75)ሁለት አይነት ዲነኝነት

ትክክለኛ ዲነኝነት ማለት የአእምሮ ነቃት፣ ሰውየው በሰዎች መሀከል አርአያ የሆነ ሁሉም ጣቱን በመልካምነት የሚቀስሩበት ተወዳጅ የሆነ እርሱን ተምሳሌት አድርገው የሚይዙት ሲሆን ነው፡፡ እኛ ይህንን ዲነኝነት የምናበረታታው ሲሆን ፣ የዚህ ተቃራኒ የሆነውን ሸዋጅ ዲነኝነት እንቃወማለን፡፡ ይህም ግራ ከገባው አእምሮ ከበሽተኛ ቀልብ ፣ አልያም የተበላሸ ቀልብና የተመረዘ አእምሮ ብዥታ ከሚፈጥረው ቅዠታዊ ህይወት ቅዠትና ጥቅም አሳዳጅነት ተደምረው ከሚፈጥሩት የማይረባ ስብዕና ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ የዚህ አይነት ባህሪ ያለው ሰው ሰዎች ዘንድ የተጠላ ነው፡፡ የአስከፊነትና የመጥፎ ባህሪ አርአያ ነው፡፡ የዚህ አይነት ሀይማኖተኝነት ነበረ አሁንም አለ፡፡ ይህ ሰዎችን ከአላህ ዲን ያባርራል፡፡

እንዲህ አይነት ወንጀሎች ዲነኛ ነኝ ብሎ ከሚያስበው ስራ ትፋቶችና ወንጀሎች በእጅጉ አደገኛና አጥፊ ናቸው፡፡
የተምታታና ፎርጅድ ከሆነ ሀይማኖተኝነት መገለጫዎች ውስጥ ውጫዊ ገፅታን ማሳመር ውስጣዊ ቀልብን መዘንጋት ፤ ግዴታ ነገሮችን እርግፍ አድርጎ በመተው ፣ በተጨማሪ ነገሮች እራስን መጥመድ ፤ በግል ጥቅም መጠመድ የህዝብን ግልጋሎት መዘንጋትና መተው የዚህ አይነት በሽታ የተጠናወታቸው ሰዎች የራሳቸውን ድክመቶች ስሜቶችና ስንፍናዎች ዱኒያዊ ልብስ አልብሶ መሸፈን የሚገባቸውን ቦታና ስፍራ ለመቆጣጠር መስገብገብ፡፡ በአግባቡና ባቅማቸው ብቃት የተሸለና የተከበረ ቦታ የያዙ ሰዎችን ማናናቅና ማጣጣል ዋናዎቹ መገለጫዎቻቸው ናቸው፡፡

## 76)<u>የመከራና የፈተና ሀዲሶች</u>

ኢስላም በአላህ እገዛና ጥበቃ ስር ያለ ዲን ነው፡፡ ጠላቶቹ ቅር ቢሰኙም የወደፊቱ ስኬት የኢስላም ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አላህ (ሰ.ወ) ንግግር ቁርአን ላይ ተገልፆአል፡፡ የተከበረው ሀዲስም ዘክረውታል፡፡ የተጨባጩም አለም እውነታም ይህንኑ ያሳያል፡፡ የወደፊቱን የምድር ህይወትም ለሙስሊሞች መልካም እንደሆኑየሚገልፁ ነገሮች አሉ፡፡ የዳዕዋ ሰዎች የወደፊት የኢስላምን ስኬት ላይ ያላቸው እምነት እርግጠኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪውም ኢስላም ትክክለኛ ዲን ነው፡፡ የዳዕዋ ሰዎች ይህ አስተሳሰባቸው ዕምነታቸው ለኢስላም የሚያወጡት ጥረትና ሊያሳኩ የሚሞክሩት ተልዕኮ ሊያስከትሉት የሚተጉት ህዝብ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡ እዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ ብዙዎቹ ስለ መከራና ፈተና የሚያትቱት ሀዲሶች በሰነዳዊ አወራረዳቸው ደካማዎች ናቸው፡፡ ከሀዲሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆኑና የሰነድ ችግር የሌለባቸው ህዝበ ሙስሊሙ ሁሌም ከድጡ ወደ ማጡ ነው የሚጓዙት ነው የሚሉ ሀዲሶች

አሉ፡፡ እነዚህ ሀዲሶች የጠቆሟቸው አደጋዎችና ፈተናዎች በዘመንና በስፍራ ገደብ ስር ያሉ፤ አጠቃላይነትና ተሻጋሪነት የጎደላቸው አልያም በግለሰብ ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ጠቋሚዎች ናቸው ፡፡ የእነዚህን ሀዲሶች መልዕክት ጠቅላይና ተሻጋሪ አድርጎ ማየት ከባድ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህን ግንዛቤ ስህተት ላይ ይጥላል ከበርካታ ጠንካራና ግልፅ ከሆኑ የድልና የስኬትን ብስራት ከሚያስተላልፉ የቁርአንና የሱንና አንቀፆች ጋር ይጋጫሉ፡፡ የአላህ (ሰ.ወ) የምድር ላይ ህግጋትና ጠፈጥåዊ ዑደት ይቃረናል፡፡ ዘመናዊና ጥንታዊ ከሆነው የታሪክ ክስተቶችን እንዲሁም የአላህን ፍትህዊነትን ይፃረራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሰዎች እንዲረዱ እና እንዲያግዙ እያዘዙ በሌላ በኩል ድልንና ስኬትን ይከለክላቸዋል፡፡ እነርሱም ሁሌም ጠሸንፈትና የውድቀት ስሜት ውስጥ ሆነው እንዲኖሩ አላህ በፍፁም አያደርግም፡፡

እነዚህ ሀዲሶች ቁንፅል መልዕክት በዋናው ጠቅላይ በሆነው የኢስላም መልዕክት ውስጥ ተደምረው እርግጠኛ መልዕክታቸው ይታያል፡፡ የያዙት ልዕክቶች በትክክል ይመዘናል፡፡

እኛ ስለ መከራ የሚያትቱ ሀዲሶችን በመልካቸውና በትክክለኛ ስፍራቸው እናስተናግዳቸዋለን፡፡ በእርግጠኝነት የምናምነው ነገር ኢስላም የአላህ ዲን መሆኑንና የአላህ እገዛና እርዳታ እንደማይቋረጥበት ነው፡፡

## 77)<u>ሁለት አይነት ቅንጦት</u>

ሁለት አይነት ቅንጦት የገንዘብ ጥፋትን ያስከትላል፡፡ በሂደትም ሁሉንም የሂደት መስኮች ወደ ማበላሸት ይመራል፡፡ ስለዚህም ኢስላም መስመር የለቀቀ ገንዘብ አጥፊነትን ተቃውሟል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መሰራጨቱንም ወደ ጥፋት የሚያመላክት አስጠንቃቂ አድርጎታል፡፡

ስለዚህም የዳዕዋ ሰዎች የገንዘብ ውድመትና ጥፋትን ሊዋጉና ሊያስጠነቅቁ ይገባል፡፡

ሌላ አይነት ብክነትና የምቾት ጣጣ አለ፡፡ ይህኛው ከሁሉም አስከፊና አጥፊ ነው፡፡ ይህም የዳእዋ ሰዎች የአስተሳሰብ ብክነት ነው፡፡ ለምሳሌ ይህንን የአስተሳሰብ ብክነት የምንምለከትበት ቦታ አለ፡፡ ይህም በሆነ በታሪክ ሂደት ውስጥ ተፈጥሮ የነበረና ያመጣውንም መልካም ነገር የመጣበትንም አደጋ የማይታወቅ የጠፋ የከሰመ ቡድንን (ፊርቃን ማጥናት)፣ በዛሬ ዘመን እዚህ ዑማ ላይ ምንም አይነት የአደጋ ስጋት ያልሆነን ያለፈን  ታሪክ ከቀብር ማንሳት በዚህ ጉዳይ ላይ ሙሉ ርዕስ አልያም መፅሀፍ የሚከትብ አለ፡፡ ስታነበው ሊያስተላልፈው የነበረውን መልዕክት ምን እንደሆነ ሊገባህ አይችልም፡፡  እንዲሁም የግድ አስተሳሰቡን የማይደግፉ መረጃዎች የሚሰበስብ ሰው ዘንድ እናየዋለን የዚህ መመለሻ አስተሳሰቡ እራሱ ዘንድ የጨገገ ነው፡፡የዚህ ሰው አላማ እርሱ ከሌሎች የተለየ እንደሆነ መንገር እንጂ ሌላ ትርፍ የለውም፡፡ ሌሎች ደግሞ የተዟዘረና የማይገባ  ነገር ይፅፋል፡፡  እርሱ እራሱ ምን እያለ እንደሆነ ይገባዋል፡፡ ወይም በግልፅ ለመናገር የከለከለው የሆነ ምክንያት ይኖረዋል ይህ እና አምሳያ ምሳሌዎች የአስተሳሰብና የአእምሮ ብክለት መገለጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ልክ እንደ ገንዘብ ብክነትና ጥፋት የአስተሳሰብ ጥፋቶች ናቸው፡፡ ከዛ በላይ የከፋ ነው ካላልን፡፡ ትክክለኛና ታማኝ የዳዕዋ ሰዎች ከዚህ አደጋ እራሳቸውን ማቀብ አለባቸው፡፡ይህ አይነት የሀሳብ ብክነት ጊዜን ጥረትን፣ ገንዘብን እንዲሁም የአላህን ሽልማት ያሳጣል በጫንቃ ላይ የተከመረን ሀላፊነት ላለመወጣት የሚደረግ ማምለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ ወይም ከዚያ በኩል የተጐነጐነ ተንኮል ጊዜን ለመቀማትና በሰው ህይወት ለመጫወት የተበጀ ደባ ሊሆንም ይችላል፡፡ ውጤቱ መልካም ነገር እስካልሆነ ድረስ መነሻው ጥሩ መሆኑ በራሱ ዋጋ የለውም፡፡

## 78)ኢስላም አላህን ብቻ ማምለክና ወደ አንድነት የሚጋብዝ ሀይማኖት ነው፡፡

ኢስላም አሀዳዊነትን እና ወደ አንድነት የሚያስጠጋ ዲን ነው፡፡ ሙስሊሙ ዑማ አላህ (ሱ.ወ)በሰማዩ የሚያመልክ የአላህ ምድር ላይ በሚደረገው ዳዕዋ ጥሪ አንድነትን የሚሰብክ ዲን ነው፡፡ ስለዚህም የዳዕዋ ጥሪ ከፍተኛ ጥረት ሊሆን የሚገባው ወደየ አስተሳሰብ የስሜት የተግባር አንድነት መጥራት ነው፡፡ከልዩነት ከአስተሳሰብም ከስሜትም በተግባርም ማስጠንቀቅ አለበት፡፡ አንድነት ሀይል እዝነት፣ በረከት እንዲሁም ለስራ ብርታትና ንቃት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩልም አንድነት የአላህ እገዛ እና እርዳታ ለማግኘት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ግጭትና ጥላቻ የተቃራኒ ውጤት ያመጣሉ፡፡

የዳዕዋ ስራ ጥረትና ልፋት ለሙስሊሙ ዑማ ያበረከተው አስተዋፅኦ ጋር የሚመጣጠን አይደለም፡፡ የዳዕዋ እንቅስቃሴ ህዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ያለው ከፍተኛ አክብሮትና ፍቅር የዑማውን ትክክለኛ ተስፋና ጭንቀት በትክክል መግለፅ መቻላቻ ሁሉ ተደምሮ የዳዕዋ መስክ ዘዋሪዎች እነርሱ ላይ ተስፋውን እና መጪውን ዘመኑን ያስተሳሰረውን ህብረተሰብ ማርካትና የጠበቀውን ያህል ውጤት ማስገንዘብ አልቻለም፡፡

የዚህ ችግር መንስኤዎች ብዙ ቢሆኑም እንቅስቃሴውን ሰንጎ የያዘውን ግንባር ችግር ኢስላማዊ) እንቅስቃሴዎች ዘንድ ያለው ልዩነትና አብሮ አለመስራት አልፎ አልፎም መጠላለፍና መጋጨት መኖሩ ነው፡፡ የሚፈጠረውን የአንድነት ለመቀራረብና ለአላህ (ሱ.ወ) ብሎ መስራት ፣ የፍቅርና የውዴታን መንፈስ መርጨት ቅርንጫፋዊ በሆኑ የአቂዳ ነጥቦች ምክንያት ሙግትና ጭቅጭቅን መሸሽ ፣ ቀደምቶች አበዎች በተለያባቸው ተከታዮቸው በተነታረኩባቸው ዝርዝር የፊቅህ አጀንዳዎች አለመሟገት

ትክክለኛ የጥናት የምርምር ውጤትን ያስመዘገበ ሽልማት ያገኛል፡፡ የተሳሳተውም ውግዘት አይደርስበትም፡፡

## 79)<u>ጠቃሚ ተቃርኖዎች</u>

አንዳንድ የዳዕዋ ሰዎች ከተንሰራፉ ብዥታዎች ውስጥ ኢስላምን የሚቃወሙ ሰዎች በአንድና አቅጣጫና ሰልፍ ኢስላምን በተከታይነት ይዋጋሉ የሚል አስተሳሰብ ነው፡፡ እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ኢስላምን የሚቃወሙ ሀይሎች ሁሌም አይሰማሙም፡፡ ሁሌም አንድ አይሆኑም፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ ኢስላምንና ሙስሊሞችን የሚጠቅሙ አቋሞችን ሊይዙና ሊያራምዱ ይችላሉ፡፡ ጠቃሚ አቋም የሚያዝባቸውን ምክንያትና አላማዎች ነገር ሳንመለከት፡፡
ስለዚህም ሙስሊም ሰው የኢስላም ጠላቶች ማወቅ ማጥናት አለበት ፡፡ በመሀከላቸውም ያሉ ልዩነቶችና ተቃርኖዎች መለየት ይገባዋል፡፡ ይህን ተቃርኖና ግጭት ለሰዎችና ለአገር በመጠቀም መልኩ ሊገለገልበት ይገባል፡ ፡ በአንፃሩ የጠላቶችን ሀይል አንድና የማይነቃነቅ አድርጎ ማየት የአላህን (ሰ.ወ) የምድር ህግ እውነታዎች መፃረር ነው፡፡ ቀደምትና አዳዲስ የታሪክ ጭብጦች መቃወም ይሆናል፡፡ ይህ አስተሳሰብና የእይታ የአእምሮ ስንፍና ሽንፈት ውጤት ነው፡፡ የዚህ አቋም ባለቤቶች አእምሮዋቸውን አልፍተውና አሰርተው በተቃርኖዎች ውስጥ የሚታዩ ቀዳዳዎችን ለይተው መፍትሄዎችን ለማፈላለግና ግልጋሎት ላይ ለማዋለወ አቅም ያጡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እራስን የማታለያ አቅጣጫ ነው፡፡ እነርሱ እራሳቸውን ከስርና ከትግል አውድማ አሸሽተው የበላይ ሀይልን የመግጠም አቅም የለንም የሚል ከንቱ ምክንያት ለመያዝ እየተጠቀሙበት ነው፡፡

## 80) <u>የአላህን ህግጋት መፈፀም</u>

መሰረታዊ ጥያቄ አለ፡፡ እርሱም እንዴት የአላህ (ሱ.ወ) ህግጋት ድሮ ወደነበረበት የገዢና የአስተዳደር ሚናው በየ ሀገሪቱ
እንዴት ይመጣል፡፡በመጀመሪያ ለሁሉም ሁኔታዎች ተስማሚ የሚሆን ብቸኛ መፍትሄ አለ ብሎ የሚሞግት አእምሮ ጤነኛ ሰው አይገኝም፡፡ ምናልባትም ቀጣዩ መፍትሄ ለብዙዎቹ ተስማሚ ሊሆን ይችላል፡፡የዳዕዋ ሰዎች የአላህ (ሱ.ወ) ህግጋት በተግባር ለማዋል የማያቋርጥ ትጋት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ጥረታቸውም ሰላማዊ ይፋዊ ፣ ቀጣይነት ያለው መሆን አለበት፡፡ የእነርሱን በአላህ ህግጋት የመተዳደር ፍላጎት ጠቃሚነት አዋጭነት ሁሉንም ለማሳየት መሞከር ፤ እነርሱም ላይ ያለውን ሀላፊነት ለማሳየት መግለፅ አለባቸው፡፡ ይህ አካሄድ ከሚያመጣቸው ፍይዳዎች ውስጥ የመንግስት ባለ ስልጣናት ዘንድ ያለውን የሸሪአ ስጋትና ፍርሀት ያጠፋዋል፡፡ ወይም ይቀንሰዋል ፡፡ ይህ አካሄድ ለመንግስት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም ለዳእዋ ሰዎች በጣም ጠቃሚ ነው፡፡በተጨማሪም በሸሪአ ህግ ለመስራት አቅም ያጣውን ፍርሀት የሸበበውን ስሜቱን ያልተገራውን የመንግስት ሀላፊ የዳዕዋ ሰዎች የሚያቀርቡለትን የሸሪአ ህግጋት የመተግበር አቅጣጫ የእርሱን ውስጥ ሊያነሳሳና ወደ ተግባር እንዲመጣ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ሌላው ከዱአቶች የሚጠበቅ ነገር የሸሪአን ህግጋቶች ደረጃ በደረጃ መፈፀም በአንድ ጊዜ ሁሉንም ከመፈፀም የተሻለ ነው፡፡ ሌላው ነገር የሸሪአን ህግጋት የመፈፀም ጥያቄ መቅረቡ መልካም ነገሩ፤ ከሰርጎ ገብ ፣ ከተንኮለኛና ከግብዝ አልያም ከምር ተቆርቋሪ መሳይነት እንዲገታ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የሸሪአን ጥያቄ በአግባቡ የማንሳት ጉዳይ ሰላማዊነት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ስህተቶችን ለማረቅ ያግዛል፡፡ በግልፅ ጥያቄዎን ማቅረብ ስህተትና ድክመትን በአደባባይ የማግኘት እድልን ያሰፋልለጥሪው አያገኝም፡፡ ሌላው የዳዕዋ ሰዎች ዘንድ ትልቅ ቦታ

ሊያገኝ ሚገባው ጉዳይ የዳዕዋ ሰዎች ውስጣቸወን ከስልጣን ጥማት ፣ ገዥ ለሞሆን ከመ፟ቋቋጥ ፤ እራሳቸውን ሊያፀዱ በግልፅና በይፋ ሊያውጁ ይገባል፡፡ የማስመሰያ ሳይሆን የእውነታቸውን እነርሱ ስልጣን ለራሳቸው እንደማይፈልጉናየአላህ ህግጋት እንዲፈፅሙ እንደሚፈልጉ እነርሱ ይህንን የአላህ ህግጋት ለመፈፀም ለሚሻ ወገን አገልጋዮች መሆናቸውን ማሳወቅ አለባቸው፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ጥበብ የተሞላ ምክር መለገስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም አቡልሀሰን አነዳዊ በተደጋጋሚ የገለፁትና እርሳቸው የመረጡትን "ኢማን ስልጣን ያላቸው ሰዎች ዘንድ መሄዱ የኢማን ሰዎች ወደ ስልጣን ከሚሄዱ የተሸለመሆን" ነው፡፡ ይህ ምክር የአላህ ስጦታና እድል ነው፡፡ የዳዕዋ ሰዎች ሁሉም አይናቸው ፊት ለፊት ሊያደርጉት የሚገባ ቋሚ ሀሳብ መሆን አለበት፡፡ በሁሉም ሁኔታ የአላህን ህግ የመፈፀም ጉዳይ በየትኛውም አገር እንዲሳካ ብዙሀን ህዝብ ያለምንም ማስፈራሪያና ግዴታ ምርጫ ሲሆንና ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## 81) <u>ተጠያቂነት</u>

ብዙ የዳዕዋ ሰዎች ዘንድ የተስፋፋ ነገር አለ፡፡ ይህም የዳዕዋ ሰዎች ያደረጉት የዳዕዋ ስራና ጥረት የሚያመጣው ውድቀት ተጠያቂነት የእኛ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ሊገዛው ሊዳኘው የሚገባ ነገር ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ጉዳዩ ዝም ተብሎ ልቅ ተደርጎ ከተተወ ታላቅ አደጋ አለው፡፡ በትንሹ ተጠያቂነትና ግምገማ አለመኖር ጠንካራ ሰራተኛና አጥፊ ሰራተኛን እኩል ማድረግ ነው፡፡ የዳዕዋ ሰዎች ለአላህ (ሱ.ወ) ብለው ከሰሩ አዋጭና ለስኬት የሚያበቃ መንገድን ከመረጡ የአቅማቸው የፈቀደን ያህል ጥረት ካደረጉ ግባቸውን ከመቱ ይመሰገናሉ፡፡ከወደቁ ከጥረትና ከትጋት በኋላ ስለሆነ ምክንያታቸው ተቀባይነት አለው፡፡ ከላይ ካየናቸው ሶስት

ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከዛ በላይ ከጎደለ መጨረሻቸው ውድቀትና ስኬተ ቢስ መሆን ነው፡፡ እነርሱ ለደረሱበት ደረጃ ተጠያቂ ናቸው፡፡

## 82)<u>የመንፈስ ልዕልና</u>

ሙዕሚን ውሸት ላይ ሚያሳየው የበላይነት የሚመሰገን ነው፡፡ ቀልቡና አእምሮው ላይ ያለውን በአላህ የመተማመን እርሱ የሚያስታውቀውን ዲን የበላይና ታላቅ መሆኑ የሚፈጥረው የመንፈስ ልዕልና ነው፡፡ግና ሙዕሚን ከባድ ስህተት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ይህም ለውሸት ያለው ንቀት ወደ ሚጠራቸው ሰዎች ንቀት እንዳይራመድ ይህ ከተከሰተ ዳዕዋ ላይ የሽንፈት ከሚያመጡ ውጤቶች አንዱ ይሆናል፡፡ ማለትም ሰውየው ከሌሎች የተሻልኩኝ ነኝ የሚል ብዥታ ይሆናል በሂደቱም ከሰዎች ጋር መቀላቀል ይከብደዋል፡፡ የእነርሱ ቆሻሻ መሀይምነት ወደ እርሱ እንዳይራመድ ይሰጋል፡፡ እንዲህ አይነት ደረጃ ላይ ከደረሰ እርሱ ለትንሽም ሆነ ለትልቅ የዳዕዋ ተልዕኮ አይሆንም፡፡ ዕንደውም እራሱ የዳዕዋ መሰናክልና ሸክም ይሆናል፡፡ የዳዕዋ ሰው ከንቱ ነገርን እንጂ የሚጠራቸውን ሰዎች ሊንቅ አይገባቸውም፡፡ እንደውም አላህ (ሱ.ወ) እነርሱን የመጥራት እድልና ስጦታ ስለለገሰው ሊያመሰግነው እነርሱን ሊወድና ሊያከብር ሊታገሳቸውና እነርሱ ዘንድ የሚገኘውን መልካም ስራ የመስራት ስሜት ሊቀሰቅሰው ሊያነሳሳው ይገባል፡፡ ይህን ካደረገ የመንፈስ ልዕልናውን የውሸት ንቀቱን በተገቢው ቦታ አውሏል፡፡ የማይረባ ከሆኑ የውስጥ ማታለያና ሽንፈት ወጥቷል፡፡ በዕርግጥ ይህ የመንፈስ ልዕልና መሰረታዊ እና እውነተኛ ነው፡፡ የግለሰብን አልያም የቡድን የበላይነት ለማሳየት የተመረጠ ንቀት አይደለም፡፡

## 83)<u>ዋጋ ቢስ አላስፈላጊ ግንኙነቶች</u>

አንዳንድ የዳዕዋ ሰዎች አንድ ጉዳይ መተከር በተለያዩ ስያሜዎችና ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ይህ ግንኙነት ምንም ፋይዳ ያለው ጉዳይ ሳያመጣ በወሬ እዚያና እዚህ በመዳዝ ይህንን አልያም ያንኛውን ሰው ተቋም በመተቸት ቁጣቸውንነዘ ንዴታቸውን በአንድ ወይም በሌላ ጉዳይ ላይ በማሳረፍ በምኞትና ልክ በሌለው ተስፋ ጊዜዎችን ያጠፋሉ፡፡ከዚያ እነርሱ ጌታችን ዘንድ አንድ መልካም ነገር ሰርተናል በማለት የአላህ ዲን በአቅማቸው እንዳገለገሉና እንደረዱ ይሰማቸዋል፡፡ እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ እራሳቸውን የማይረባ ከንቱ በሆነ ወሬ ሸብበው ደግሞ በሌላ ቀጠሮ ይለያያሉ፡፡ ይህ ድርጊታቸው የእነርሱን ክፍተት ለመድፈን የወሬ ሱሳቸውን ለማርካት ነው፡፡ ይህ ድርጊታቸው የሚሰማቸውን ዲን ለማገልገል ሰሜት የሚያስተነፍሱበት የቅጥፈት ስራ እራሳቸውን የሚያታሉበት እርስ በእርስ የሚሸነጋገሉበት ነው፡፡ እርስ በእርስም እጅግ የበዛ የማይጨበጥ ተስፋና የምስጋና ጋጋታ ይቀያየራሉ፡፡
እውነተኛና ተጨባጭ የሆነውን ሀላፊነታቸውን በማምለጥ ለእራሳቸው ስንፍና ጨለምተኝነትና ወረኛነት በትንሹም ሆነ በትልቁ የማይገባቸውን የዲነኝነት ተቆርቋሪነት ካባ ያጠልቃሉ፡

## 84) <u>ልከኝነትና ሚዛናዊነት</u>

ኢስላም ልከኛና ሚዛናዊ ዲን ነው፡፡ ከሁለት የተራራቁ የተወገዙ ጠርዘኝነት የራቀ ነው፡፡ ኢስላም ከፅንፈኝነትም ሆነ ከግትርነት የፀዳ ሀይማኖት ነው፡፡ አላህ እዲህ ብሏል፡-

وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَٰكُمْ أُمَّةً وَسَطًا ﴿١٤٣﴾سورةالبقرة:143

‹‹ ሚዛናዊ ‹‹ኡምማህ›› አደረግናችሁ፡፡ ›› አል በቀራህ፤ 143

ማለትም ፍትሀዊ በላጭ ማለት ነው፡፡ የነገሮች ሁሉ ምርጥ መሀከለኛው ነው፡፡ ድንበር ማለፍና ግትርነት ሁለቱም የተወገዙ ናቸው፡፡ የኢስላም ሚዛናዊነት በሁሉም የህይወት ሜዳዎች ውስጥ በይፋ ይታያል፡፡ ኢስላም ሁሉን አቀፍና ዘላለማዊ ዲን ስለሆነ በእርሱ ውስጥ ያሉ ትዕዛዛትም ሚዛናዊ ናቸው፡፡

ለምሳሌ ሙስሊም ሰው ለዱንያ ያለው ንቃት ምድር ላይ ከመትጋትና ምድር ላይ ከተጣለበት ግዴታ ከመወጣት አያቅበውም ለማልማት ከሚደረግ ትግል አያፈገፍግም ፡፡ የሰው ሸክም የአገር እዳ መሆን የለበትም ፡፡ በሌላ ጎንም ዱንያ ላይ ያለው እይታ የስግብግብና ልክ ያጣ ሊሆን አይገባም፡፡ ሙስሊም ከዱንያ ጋር ያለው ግንኙነትና ልከኝነት ምድር ላይ እንጀራን ለማግኘት በሚረግ ጥረት ላይ እንደተመለከትነው እና እንደደረስንበት ሁላ በሌላ በኩልም ሙስሊም ኢባዳ ሊፈፅምና ገንዘቡን ሊለግስ ከሰዎች ጋር ሲዋዋልና ሲሻሻጥና ሲለብስ ሚዛናዊነቱን ይጠብቃል፡ ፡በግለሰብና በቡድን በሙብትና በግዴታ በአካልና በመንፈስ በአእምሮና በቀልብ መካከል ያሉ ግንኙነቶችና ፍላጎቶች ልክ ከማለፍም ሆነ ደንታ ቢስ ከመሆን ርቀው ሚዛናዊ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

ግድየለሽነት የግለሰብና የቡድን ጥቅሞችና ትርፎች ስለሚያስወስድ የተወገዘ ነው፡፡ ድንበር ማለፍ የሰው ልጅን ተፈጥሮ ስለሚፃረርና ተፈጥሯዊ በህሪ ስላልሆነ የተጠላ ነው፡፡ ስለዚህም ፅንፈኝነት እድሜው አጭር የሚጠፋበትን ፍሬ በውስጡ ተሸክሞ ይጓዛል፡፡ስለዚህም አላህ (ሱ.ወ) ኢስላምን ሚዛናዊና ልከኛ ዲን አደረገው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዲን አላህ የሰው ልጅ የተፈጠረበትና የታዘዘበት ዲን ነው፡፡ አላህ የሰው ልጆችን ሲያዝ የሰውን ተፈጥሮ አቅም ድክመትና ጥንካሬ ያውቃልና ነው፡፡

## 85)መልከ ብዙ ልዩነቶች

ኢስላም የአንድነት ደረጃን አልቋል፡፡ ወደ እርሱም ሰብኳ፡፡ ግጭትን አውግዟል፡፡ ሆኖም ግን የሰው ልጆችን የማይቀር ልዩነቶችን ተቀብሏል፡፡ ይህም የአላህ ሱንና ከሆኑ የፍጡራኑ የማይቀሩ እውነታዎች ነው፡፡ ልዩነት ሁለት አይነት ነው፡፡ ጠቃሚና ጎጂ ይባላሉ፡፡ ጠቃሚ የሚባለው ልዩነት የአስተያየት ልዩነት ነው፡፤ ይህ ልዩነት የሰውን ልጅ ልዩነት ያካብተዋል፡፡ ከሰው ልጅ ባህሪ ጋር ይጣጣማል፡፡ ይህም የአምላክ ጥበብ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጆችን የተለያዩ አድርጎ ፈጠራቸው፡፡ በአስተሳሰባቸው በግንዛቤያቸው ፤ የሚያስቡባቸው መንገዶች ልክ እንደ ባህሪያቸው እንደ መልካቸው እንደ ግዝፈታቸው እንደ መልካቸው ልዩነት አላቸው፡፡
በአንፃሩ ጎጂ የሚባለው ልዩነት የውስጥ የቀልብ ልዩነቶችን ነው፡፡ ይህ የቀልብ የመጠላላት ልዩነት በቁርአን አንቀፆች ተወግዘዋል፡፡ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)ሀዲሶች እርም ተደርገዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ ይህ የአላህ (ሱ.ወ) ንግግር ይገባል፡፡

وَٱعۡتَصِمُواْ بِحَبۡلِ ٱللَّهِ جَمِيعٗا وَلَا تَفَرَّقُواْۚ ﴿١٠٣﴾سورة آل عمران:103

« በአላህ (የእምነት) ገመድ ተሳሰሩ፡፡ አትለያዩ፡፡ » አልኢምራን፤103

ጥቅም ያለው አዋጭ ልዩነት የአይነት የዘርፍ ልዩነት ነው፡፡ ይህ ልነት ልክ ብዙ ሻማዎች ማብራት ብርሀኑን እንደሚጨምርለት እንዲሁም የሻማው ብዛት የብርሀኑን ድምቀት እንደሚጨምረው ነው፡፡ በአንፃሩ አንዱ ሌላውን አያጠፋውም፡፡
ጎጂ የሆነው ልዩነት የማይስተናገድበት ዝግ ቦታዎች አሉ፡፡ ልዩነት ወደ እነርሱ ሊሄድ አይገባውም፡፡ ምክንያቱም ዑማውን የሚጠብቁ መሰረታዊ የማይነቀነቁ ጉዳዮች ስለሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ነጥቦች የዑማውን ማንነት መንፈስ ተልዕኮ ዋና አስኳል ናቸው፡፡ የእምነቱ አንድነት የባህሪንና የስሜት

ህብረት የሚያብራሩ ናቸው፡፤ እነርሱም (እምነቶች ፣ ኢባዳዎች ስነምግባሮች በግልፅ የተቀመጡ ድንጋጌዎች) ናቸው፡፡
ስለዚህም ልዩነት የማስተናገድን ጥበብ ስርአትን መማር ልዩነት መኖሩን መቀበል፡፡ የሸሪአ ሜዳ ውስጥ መስተናገድ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ የሌሎችን መብትና ግንዛቤ መረዳትና መቀበል፡፡
እንዲሁም እንደየጊዜውን እንደዘመናቱ ሁኔታዎች ልዩነት የሚከሰቱባቸው ሊቀየሩና ሊለወጡ የሚችሉ የአካሄድ የስልት የዘዴዎችን መቀበል ያስፈልጋል፡፡

## 86) <u>ሽሽትና በታሪክ መባዘን</u>

ከዳዕዋ ሰዎች ውሰጥ ያለፉ ድንቅ ታሪክ ውስጥ የሚሰወር ስለዚያ የሚያወራና የዚያ ታሪክ አባልነት የሚሰማው የሚኩራራ ሰው ብዙ ነው፡፡ በአንፃሩ ሊፈፅመውና ሊያደርገው ከሚችለው ውስጥ ትንሽ እንኳ ለመጣር አጥሞክርም፡፡ በታሪክ ትውስታ ውስጥ መሰወሩ ከባድ ስራ የመስራት ግዴታውን የመወጣት ስሜት የሚሰማው ወገን አለ፡፡ በሌላ በኩል የዛሬውን አሰቃቂ አስቸጋር የኡማ ፈተና ውስጥ ተወሽቆ ፤ አቤቱታ ለቅሶ ወቀሳ የሚያበዛ የሰቆቃውን ሀላፊነት (በእውነትም በውሸትም) በዚህ ወይም በዚያ ቡድን ላይ የሚደፈድፍ ገለልተኛ ህጎችንና ቀጣይ ልምዶችን ረስቷል፡፡ ቲኒሽ በቲኒሽ ላይ ብዙ ይሆናልጠብታ በጠብታ ላይ ሲጨምር ጅራት ይሆናል፡፡ በዚያ ድርጊቱም ሀላፊነቱን የተወጣ የሚመስለው ብዙ ነው፡፡ ሌላ ደግሞ ሶስተኛ ቡድን አለ፡፡ ይህ ቡድን መጪው ዘመን ጉያ በዝቶ ይባትላል፡፡ ምንም አይሰራም፡፡ የህዳሴ ለውጥ የሚመራ የለውጥ ሀዋሪ ይጠብቃል፡፡ ወይም መጪውን መሀዲን ይመኛል፡፡ አሊያም አምሳያ የሌለው መሪ ይጠብቃል፡፡ ከአደጋ የሚያወጣ ጀግና ይስላል፡፡

ይህ አይነት መሪ መከሰት ሁሉንም መከራና ችግር የሚፈታ ፡፡ ሁሉንም ተስፋና የወደፊት ብስራት ሚጨብጥ ይመስለዋል፡፡ ይህንን ሁሉ ሲተልም ለተፈጥቆዊ ህግጋትና የአላህን የማይለወጡ ስርአቶች ይዘነጋል፡፡
እነዚህ ሶስት አይነት ሽሽቶች ሊሰሩት የሚችሉትን ሀላፊነት እየሸሹ ነው፡፡ ለተነሳናቸው ድርጊት ዋጋ ቢስ ምክንያቶችን እየደረደሩ ነው፡፡ እራሳቸውን በራሳቸው ይወዳሉ፡፡ ይህ አይነት አስተሳሰብ የዳዕዋ እንዲሁም የህይወት ትልቅ መሰናክል ነው፡፡ አንድ ሙስሊም ሊያውቀው የሚገባ ዋናው ነጥብ የዳዕዋ ተልዕኮ ፣ ዘመኑን እንዲሁም በአቅሙ ሊሰራው የሚችለውን ማወቅ ነው፡፡ በእርሱ ለአላህ(ሱ.ወ) ያለው ታማኝነት እንዲሁም በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያደርገው ጥረት የእርሱ አቅም ትንሽም ይሁን ትልቅ ለአላህ ብሎ ከሰራውና የራሱን ጥረት ካደረገ ትንሽ ጥቂቱንም ቢሆን ብዙ ይሆናል፡፡ ትናንሽ ህዝቦች በሂደት ባህር ይፈጥራሉ፡፡
አላህ (ሱ.ወ) ከባሮቹ ላይ ትጋትንና ኢኽላስን ከተመለከተ ስራውን ይቀበለዋል፡፡ መጠኑ ምንም ቢሆን አላህ ያፋፋዋል፡፡ የተሻለ ውጤትና ስራ ይሆናል፡፡

## 87)<u>ከፈተናዎችና ከችግሮች ጋር</u>

ከተለያዩ ጊዜያት ችግሮች ፕሮፖጋንዳዎች ፈተናዎች በሙስሊሞች መሀከል ይከሰታሉ፡፡ አላህን ማንቋሸሽ የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መስደብ የሙስሊሞችን ስብስብ ማጥቃት አልያም ሙስሊሞች ዘንድ በጣም የተቀደሱ ቅዱሳንን መንካት የዑማው ቋሚ መሰረታዊ ምሰሶዎችን መልከፍ ሊሆን ይችላል፡፡
እነዚህን ድርጊቶች ለመፈፀም የሚያነሳሱ ነገሮች ብዙ ናቸው ፡፡ ጥላቻ ፣ ማን አለብኝነት ፣ አለማወቅ ዝነኛ ለመሆን መፈለግ ፤ እንዲሁም የኢስላም ታማኝና ጠንካራ ልጆች የተሰማሩበትን ትክክለኛና ስኬታማ መስመሮች

ለቀው አተካራ ውስጥ እንዲዘፈቁ ለማድረግም ይሆናል፡፡ የዳእዋ ተልዕኮ ያለው ሰው ችግሮችና ፈተናዎች እነዚህ ችግሮች የተነሱባቸውን ዋና ምክንያቶች ነጥሎ ለማወቅ መጣር አለበት ፡፡እንዲሁም ውጤትንና ጥቅምና ያማከለ አዋጭና መልካም ነገር መፈፀም አለበት፡፡ አንዱን በዝምታ ያልፋል ፣ ሌላው ስያሜ ሳይሰጥ መልስና ማጋለጫ ቀርባል ያኛውን በመጋፈጥና ስም በመግለፅ ይዋጋል፡፡
የዳዕዋ ሰው መጋፈጥንና ፊት ለፊት መጋጠምን ሲመርጥ የሚያመጣውን ውጤትና የሚያስከትለውን መስዋዕትነት በትክክልናበጥንቃቄ መለካት አለበት፡፡ ድንበር ሊያልፍ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ልኩን ካለፈ ደግሞተንኮለኞች የቆፈሩለት ጉድጓድ ውስጥ ገባ ማለት ነው፡፡ ይህ እነርሱን ያስደስታል፡፡ በተጨማሪ እና አዲስ የተንኮል መረብ እንዲያዘጋጁለት እና እነርሱ በቀየሱት ጎዳና እንዲጓዝ ያመቻችላቸዋል፡፡

## 88) <u>የተሸለ አካሄድ</u>

የፊቅህ እና የዳዕዋ ምርጫዎች ከሰው ሰው እንደየሁኔታቸው እንደባህሪቸው ፣ እንደ የግንዛቤያቸው እንደየእውቀት ደረጃቸው ይለያያሉ፡፡አንዱ የራሱን ምርጫ በሌላው ላይ መጫን እኔን ተከል ማለት ብልህትም ጥበብም አይደለም፡፡ ምንም እንኳ የእርሱ እይታ በጣም ትክክልና እጅግ የተሸለ እንኳን ቢሆን በጣም ትክክል በሆኑ ሀሳቦች ምክንያት ከመለያየት ትክክል በሆኑ ነጥቦች መስማማትና አብሮ መስራት የተሸለ ነው፡፡ በጣም አዋጭና ስኬታማ በሆነ ጉዳይ ከመጋጨት አዋጭና የተሻለ በሆነ ነጥብ መተጋገዝ ለስኬት ያቀርባል፡፡

## 89) ከህዝቡ ጋር

ህዝቡን የሚመለከት ዳዕዋ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉም የሚስማማበት እውነታዎችና ጭብጦች መግለፅ የፊቂህ ሊቃውንት የደረሱባቸውን የዝርዝር ህግጋት ልዩነት መንካት አያስፈልግም ፡፡ በተለይም ጥራዝ ነጠቅ የሆኑ ሀሳቦችን ፣ እሩቅ የሆኑ ትርጉሞችን፤ ብዙ የራቁ ራዕዮችን ፅንሰሀሳባዊ ንትርኮችን መራቅ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ርእሶች የሚያስተናግዱባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ ለዚህ ትምህርት የቅርብ ሰዎች እንደየአስገላጊነቱ እና በጥንቃቄ ይመረመራል፡፡ግና ህዝቡ ጀማሪ ተማሪዎች ለነርሱ ተግባራዊና ጠቃሚ በሆኑ አጀንዳዎች እራሳቸውን ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡

## 90) አጠቃላይ ሁኔታዎችና መለያዎችን ቦታ መስጠት

የዳዕዋ ሰዎች ዑለሞችንና ቀደምትና ነባር የለውጥ መሪዎችን  መውደዳችን የማይቀር ነው፡፡ ለእነርሱ ዱአ እናደርጋለን፡፡ እነርሱንም ለአርያነት እንወስዳለን፡፡ ግና እነርሱን ፍፁም አድርገን መመልከት የለብንም፡፡ የነርሱን ልምድና የስራ ትጋት ሙሉዕ ለሙሉ መኮረጅና መገልበጥ የእኛን መለያዎችና እውነታዎች መዘንጋት የለብንም፡፡ የዘመናት የስፍራዎችን የሁኔታዎችን እውነት
ቦታ መስጠት እነርሱ እንደጣሩ መጣር እንዳስተዋሉና እንደተጠነቀቁ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

## 91) <u>ዲን እና ባህል</u>

አልፎ አልፎ አንዳንድ ባህሎችና ወጎች ከባድ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። ባህሎችና ወጎች ዲን ይመስላሉ። ዲን ግን በጭራሽ አይደሉም። ይህንን በደስታና በሀዘን በአጠቃላይ ማህበራዊ ግንኙነቶች ማስተዋል ይቻላል። በተለይም በሴት ዙሪያ የሚወሰዱ አቋሞች አሉ። ስለዚህም እኛ ባህልንና ዲንንመለየት አለብን። ባህልን ለመቃወምም ሆነ ለመቀበልና ለማስተናገድ በዲን ሚዛን መለኪያ መለካት አለብን።

## 92) <u>ብርቱ ሙዕሚን</u>

እኛ ብርቱ ሙዕሚን የማዘጋጀት ጥረት ልናደርግ ይገባል። ምክንያቱም ብርቱና ጠንካራ ሙዕሚን ከደካማ ሙዕሚን አላህ ዘንድ የተሸለ እና በላጭ ነው በሀዲስ እንደተገለፀው።
ይህ ብርታትና ጥንካሬ የኢማንን ትክክለኛነት ጥንካሬና ጥልቀት የስብዕና ፅናትና ዘውታሪነትን የአእምሮን አስተዋይነትንና ንቁነትን ፣ የአካላዊ ብርታትና ቅልጥፍናን ይመለከታል። ይህ የሚነግረን ነገር ለአካላችን ትኩረት እንድንሰጥና ጤንነታችንን እንድንጠብቅ ፣ ሚዛናዊ እንድንሆን ያደርገናል። ይህ ሚሰምረው አካልን የሚጠቅም ምግብ ስፖርት ንፅህና በመከታተል ነው።
አካልን የሚያውክ አደንዛዥ ዕፅ፣ ሲጋራ ፣ መጠጥ ወዘተ....... መታቀብና መራቅ ያስፈልጋል። ይህ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ዋናው ጥቅምም ይህ አካል የዳዕዋ ስራን ሀላፊነት የመሸከም ብቃትና ብርታት እንዲኖረው ያደርገናል።

## ማጠቃለያ

ሶሻሊዝም ከሁለት አስርተ አመታት በፊት ወድቋል፡፡ የምዕራቡ ካፒታሊዝም በከፍተኛ ምጥ ውስጥ ይገኛል፡፡ የካፒታሊዝም ምሰሶዎች ተነቃንቀዋል፡፡ የተገነባባቸው ዋና ዋና ማዕዘናት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገብቷል፡፡ በምዕራብ ሀገራት ዛሬ የሚታየው ነገር የካፒታሊዝም ጥንካሬ እና ከሌሎች የተሸለባቸው ነጥቦች ዛሬ ላይ እያፈገፈጉ ነው፡፡ የውድቀቱ መዘውሮች በየቀኑ አዳዲስ ችግሮችን እያመለከቱ ነው፡፡ የአላህ(ሱ.ወ) የምድር ህግ አይቀየርም ፡፡ ማንንም አያባብልም፡፡ የሰው ልጅን ለማዳን ብቃትና አቅም ያለው ማንም የለም እናንተ የኢስላም የዳዕዋ ሰዎች ብቻ ናችሁ ያላችሁት፡፡ እናንተ ዲናችባስቀመጠላችሁ ደረጃ ላይ ሁኑ፡፡ በዘመናችሁ ልክ ሁኑ፡፡ የመርከቡ ቀዛፊዎች እራሳችሁ ላይም መልካም ለሌሎች ሙስሊምም ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎችም ምርጥ መሆን አለባችሁ እና፡፡

የናንተ አጠቃላይ ሀላፊነት በዘመናት በአካባቢዎች በሰው ልጆች ላይ ሁሉ የተዘረጋ ነው፡፡ የእናንተ ጥሪ የእዝነትና የርህራሄ ተልዕኮ ነው፡፡ ምቹ እና ቀላል ችግርና መከራን አለቃቂ ሸሪአ ነው፡፡ በሁሉም ምድር ላይ ላሉ ሰዎች በሙሉ ምቾትና ድሎትን የሚያጎናፅፍ ዲን ነው፡፡ ስለዚህም ሀላፊነታችሁም በትክክል ልትገነዘቡ ይገባል፡፡ እናንተ ወደ አላህ የምትጠሩ አበሳሪዎች እንጂ ዳኞች ፤ የለውጥ አራማጅ እንጂ አቢዮተኛ ገንቢዎች እንጂ አውዳሚዎች መልካም ተመኘዎች እንጂ ምቀኞች አይደላችሁም፡፡ ስትሰሩ አባት ለልጆቹ ሀኪም ለበሽተኛው እንደሚሰራ ስሩ፡፡ ግፉን እንደፈለገ ለሚፈፅም ጨካኝ ወይም በቀለኛ መሪ አይደላችሁም፡፡

እናንተ ይህንን ስታደርጉ ቅን መንገድ ጠቋሚዎች እንደውም መሪዎች ትሆናላችሁ፡፡ ቅኑን መንገድ የተጎናፀፈችው ኢቃኞች ትሆናላችሁ፡፡ ፍጡራን የአላህ ስሪቶች ናቸው፡፡ አላህ ዘንድ የሚወደደው ለአላህ ስሪቶች

የጠቀመ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ ወደ መልካምነት ወደ ብርሀን ወደ ሰላም የሚመሩበትን ልጓም ያስረከቧቸዋል፡፡

ይህ የማስታወሻ ፅሁፍ ለዕጨኔነት የቀረቡ ብዙ መሰረቶች አካትቷል፡፡ ይህም ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የረጅም ልምድ የቋሚ ንባብ፣ የአስተውሎት ፣ የምልከታ ፤ የስቃይና የክትትል ድምር ውጤት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሙስሊሞች ዘንድ ቢገኝ ጥሩ ነው፡፡በተለየ ደግሞመሪዎቻቸው ዘንድ መገኘቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የዳዕዋ ስራ መረጃ የሀሳብና የተግባር መተዳደሪያ እንዲሆን ይታሰባል፡፡ የአንድነትና የስምምነት የትክክለኛነትና የተግባር ሜዳው እንዲሰፋ የግጭት የስህተትና የስራ ፈትነት እርከን እንዲጠብ ይረዳልና ነው፡፡

ለኢስላም የሚሰሩ ሰዎች ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲታይ ፤ የሚታየው የሚጨመር የሚቀላቀል የሚስታከል ከፊትና ከኋላ የሚቀየር አዲስ ሀሳብ የሚጨመርበት የሚገመገም እንዲሆን ይፈልጋል፡፡
ወደ እኛ የሚፅፉልን የተከበሩ ወንድሞቻችንን ቃል የምንገባው ነገር የእነርሱ ፅሁፎች እኛ ዘንድ የተከበረ ትኩረት እንደሚያገኝና ምስጋናችንም የላቀ መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ማስታወሻ ከእነርሱ ወደ ራሳቸው እንደተላከ ማስታወሻ እንዲያዩት ያሻቸውን እንዲፈፅሙ ለዚህም የተመሰገኑና አላህ ዘንድም ሽልማት ያገኙበታል፡፡

ሀሳብን በይፋ ማቅረብ በግልፅ መወያየት ሀሳቡ ያለውን ስህተትና መልካም ነገር ለማግኘት በላጭ ዘዴ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የዳዕዋ ሰዎችን ወኔ ለመቀስቀስ በማሰብ ነው ይህ የተጀመረው፡፡ ከነርሱ ሀሳብ እንዳፈልቅ ለመጋበዝ ለማስተካከል በማሰብ ወደ ሙሉዕነትእንዲቃረብ፡፡ ይህም ይህ ማስታወሻ በተቋሞች በኢስላማዊ ማህበራት ዘንድ እንዲቃረብ፡ ፡ ይህ የእኛ ለነርሱ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡

ሁሉም ተቋማትና ማህበራት ለእነርሱ የሚመለከታቸውንና የሚመቻቸውን ወስደውየራሳቸውን ጨምረው አጎልብተውና አሳምረው ይጠቀማሉ፡፡ ይህ በአላህ ፍቃድ ብዙ መልካም ነገሮችን ያመጣል፡፡

አላህ ሆይ! እገዛና መልካም የመስራት እድሉን ግጠመን የአንተን ውዴታ ለግሰን፡፡አንተን ለመታዘዝ አብቃን አንተ ሁሉን ቻይ ነህ፡፡

# ለደዕዋ አካሄድ የስምምነት ሰነድ

DF-E-TrBs-16/02


دار الفكر للترجمة والنشر والبحث العلمي في إثيوبيا

Dar Al-fiker for Translation Publication
and Scientific Research - Ethiopia
Addis Ababa - Ethiopia